**<u>የትግራይ ሕዝብ የሚያሳየው ሁኔታ፣ ይሁንታ? ወይስ መስቀለኛ መንገድ ላይ የቆመ ዝምታ?</u>**

**ኃይሌ መለሰ (ብ/ጄኔራል)**

<u>ሚያዚያ 2001</u>.

ስለ አገራችን የተወሳሰቡ ችግሮች አዘውትሬ በአብሰለሰልኩ ቁጥር ሁነኛ መልስ እያላቸው ሁነኛ መላሽ ያጡ አራት መሰረታዊ ጥያቄወች በህሊናየ ውስጥ አዘውትረው ይጉላላሉ፤ እነሱም፦

1. የትግራይ ሕዝብ የሚያሳየው ሁኔታ፣ ይሁንታ? ወይስ መስቀለኛ መንገድ ላይ የቆመ ዝምታ?

2. የአንድነት ኃይሎች ከድክመታቸው የሚማሩት መቸ ነው? የሚያስተምራቸውስ ማን ነው?

3. የብሔረሰብ ድርጅቶች ተጨቁነናል የሚሉት በሥርዓቱ ወይስ በአገሪቱ?

4. የወያኔ-አደር ባንዳዎች በእውን ተከፍሎ ለማያልቅ እዳቸው ወራሽ የሚሆኑ ቤተሰቦች አሏቸውን? የሚሉት ናቸው። ለዛሬ በዚህ ጽሑፌ ውስጥ ለመዳሰስ የምሞክረው ስለትግራይ ሕዝብ ይሁንታ ወይም ዝምታ ይሆንናል። በሌሎቹ ላይ ደግሞ ወደፊት ሁኔታው እንደፈቀደ በሌላ ጊዜ እመለስባቸዋለሁ።

ወደጥያቄው ዝርዝር ማብራሪያ ከመግባቴ በፊት በቅድሚያ በአርእስቱ ለጠቀስኳቸው ሁለት የሚሰመርባቸው ቃሎች የኔን ትርጉም ግልጽ ማድረግ አስፈላጊ ይመስለኛል። **ይሁንታ ስል** ወርቅ ከሆነ ሕዝብ ተወልደን በእሱ ሁለንተናዊ እንክብካቤ ያደግንና ለእሱ ነፃነት ታግለን በልዩ ሰውነታችንና በላቀ ጀግንነታችን ለጨበጥነው ሥልጣን የበቃን ጀግኖች ነን እያሉ ክህደት ባወረው ትምክህት እራሳቸውን የሚክቡት ወያኔዎች (ሥልጣኑና የኩበት ካባቸው ዘላቂነት ያለው ሕዝባዊ መሠረትና የእውነት ዋቢነት ባይኖረውም) በአገሪቱ ብሔራዊ አንድነትና በሕዝቧ ማህበራዊ ደህንነት ላይ እያደረሱ ያሉትን ሁለንተናዊ ማናጋትና ውድመት ሁሉ አሜን! ብሎ ተቀብሎትና ይሁን ብሎ ደግፎት ነውን? በሚያሰኝ ጥያቄ ውስጥ የወደቀውን ዝምታውን የሚያመላክት ነው።

**መስቀልኛ መንገድ ላይ የቆመ ዝምታ** ስል ደግሞ ከላይ በአጭሩ የተመለከቱትን በታሪክ ሲያፈራርዱና በትውልድ ሲያጠያይቁ የሚኖሩ ግፍና በደሎች መፈጸማቸውን እያወቀ በይፋ ቀጥሉበት ለማለትም ይሁን የእስካሁኑ በቃችሁ ብሎ ለማስቆም እንዳይችል መንገዱ ላይ ያቆሙበት ምልክት የእነሱ ብቻ አረንጓዴ የሌሎቹ ግን አደጋ ያለበት ቀይ ሆኖ እንዲታየውና ትክክለኛ አቅጣጫውን እንዳይለይ ህሊናውን የጋረደው አንድ የተቋጠረ ነገር መኖሩን ለማመልከት ስል የተጠቀምኩበት ቃል ነው። ለነገሩ ዝምታ ከገጠመኙ ጋር ተገጣጥሞ ከተተረጎመ መስማማትን ብቻም ሳይሆን በህሊና ማመጽንም የሚያመለክት ይሆናል። ከዚህ አንጻር ከተገናዘበ የትግራይ ሕዝብ ዝምታ (አውቆ የተደበቀ ቢጠሩት አቤት አይልም እንደሚባለው) ከይሁንታ ጋር የሚያገናኘው የሚስጥር በር፣የሚግባባበት ቋንቋና የሚደጋገፍበት ጎን አለው የሚያሰኝ ትርጓሜ ብሰጥ የተሳሳትኩ አይመስለኝም። በዚህ ጎራ አሰልፎ በአገሬ ጥፋትና በወገኔ እልቂት ላይ የሚያዘምት እምነትም ሆነ ድርጊታዊ ተሳትፎ የለኝም ብሎ እራሱን በታሪክ ከሚያስጠይቅ እዳ ነፃ የማድረጉን ሐላፊነት የምተወው ግን ለባለጉዳዩ የትግራይ ሕዝብ ነው።

በአሁኑ ወቅት ስለ ትግራይ ሕዝብ እንወለደዋለን ብቻም ሳይሆን ከጎኑ እንቆማለን በሚሉ ልዩ ልዩ ቡድኖችና ግለሰቦች ሁሉ ብዙ ይነገራል፤ በስሙም ብዙ ነገር ይሠራል፤ ብዙ ይነገዳል፤ ብዙ ይጨፈራል፤ ይፎከራልም፤ ብዙ ግፍም ይፈፀማል። እሱ ግን ስለ እኔ መናገር ያለብኝ እኔ እንጅ እናንተ አይደላችሁም ብሎ ተቃውሞውን ገልጾ አያውቅም። የዚህ ሁሉ ዘለቄታው ምንድን ነው? ብሎ እራሱን በመጠየቅ የተመራመረም አይመስልም። በተለይም ከእኔም አልፎ ለልጅ ልጆቼ ለሚተላለፍ የግፍ ወንጀል እዳ ተጠያቂ አይደለሁም ብሎ እምነቱን ሲገልጽና አቋሙን በተግባር ሲያረጋግጥ አይታይም፤ አይሰማምም። በዚህም ምክንያት በኢትዮጵያ ሕዝብ ዘንድ አነጋጋሪ ከሆነ ብዙ ዓመታትን አስቆጥሯል። አነጋጋሪ የሆነው ዝምታው ብቻም ሳይሆን በጋራ የሚያነጋግሩ ብዙ አገር አቀፍ ችግሮችና የሕዝብ እሮሮዎች እያስተጋቡ መሆናቸውን እያወቀ የጋራ ችግሩን አብሬ እየተጋራሁ የድርሻየን መወጣት አለብኝ ማለት ቀርቶ የእናት አገሬ እንባ



Document Produced by deskPDF Unregistered :: http://www.docudesk.com

እያራሰኝና የችግረኛው ወገኔ ጩኸት ሰላም እየነሳኝ ስለሆነ "**ለመሆኑ ምን እያደረጋችሁ ነው?**" ብሎ ይህን ሁሉ በክህደት ዓላማ የታጀበ ግፍና በደል በመፈጸም ላይ ያሉትን ልጆቹን አለመጠቁ ነው። በዚህም ምክንያት ለተለያዩ ትርጉሞች እራሱን አጋልጧል። ከነዚህም ውስጥ፦

- የተለየ ሁለንተናዊ ተጠቃሚ ስለሆነና ከኢትዮጵያዊነት ይልቅ ትግራይነት ስለበለጠበት?
- ከሌላው ወገኑ ጋር በኢትዮጵያዊነት መንፈስ አብሮ መኖርን ስለአልፈለገ?
- ከትግራይ ሕዝብ መወለዳቸውን በትምክህት የሚናገሩት ወያኔወችና ያሰለጡኑት ገዳይ ጦራቸው በሌላው ወገኑ ላይ ሲፈጽሙት የኖሩት ግፍና በደል የእሱን ቤተሰብ ጭምር ስለአላሳጣውና ሐዘን ላይ ስለአልጣለው?
- የእሱ ልጆች ገድለው ለመቅበር በዘመቱባቸው ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት መቃብር ላይ የምትገነባውን ታላቋን የትግራይ ሪፐብሊክ ለማየት ስለጓጓ? ወዘተ የሚሉ ናቸው።

ይህን ጥያቄ እንዳቀርብለት ካስገደዱኝ መሠረታዊ ነጥቦች አንዱም ይኸው ነው። እኔ ጥያቄውን በግልጽ ላቅርብለት እንጅ ጥያቄው ግን ቀደም ሲል እንደጠቀስኩት በመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ህሊና ሲጉላላ የኖረና የሆድ አልሻ (ህመምም) ሆኖ ሲያፍተለትለው የኖረ ጥያቄ መሆኑ የሚያከራክር አይመስለኝም። ***የጥያቄው መሠረታዊ ዓላማ የችግሩን ዋነኛ ምንጭ ከነመነሻ ምክንያቱ በጥልቀት ከማዎቅ ጀምሮ (ከአተረጓጎም አኳያ ለማለት እንጅ እስከአሁን አይታወቅም ነበር ለማለት አይደለም) ለኢትዮጵያና ለኢትዮጵያዊነት ዘብ የቆሙ ኃይሎችንና የታሪካዊ ጠላቶቻችን እቅድ አስፈጻሚ ሆነው በሁለቱም ላይ የዘመቱትን ቅጥረኛ ባንዳዎች ከእምነትና ግብራቸው ጎራ አኳያ አሰላልፎ በማፋለም በምሺግነት የሚገለገሉበትን የትግራይን ሕዝብ አራግፈውበት ሊሾልኩ ካከማቹበት ባለብዙ መልክ የችግር እዳ ነፃ ለማድረግ ነው። ስለዚህ ጠቃሚ እንጅ ጎጅ ጎን ያለው አይመስለኝም።*** ይኸ ሐሳብ በእኔ ቅን ሕሊና የታየ የጋራ መፍትሄ ማፈላለጊያ ስልት ቢሆንም ቅሉ የእኔን ጠቃሚ ሐሳብና ግልጽ መልዕት አስተካክሎ ለማየት በማይችል የመንደርተኝነት ዓይነ-ማዝ በሽታ በበከለው ሸውራራ አመለካከት እያዩ እኛ እያለን አንተ ለትግራይ ሕዝብ ምን ሆንክና ጥያቄ አቅራቢና ነፃ አውጭ አደረገህ ብለው የሚደነፉ እንዳሉ ልምዳቸው አለኝ። ይጠቅመዋል ብየ የአቀረብኩለትን ጥያቄም በተቃራኒው ተርጉመው ለጉዳት እንደደረግሁት አድርገው ለማየት የሚፈልጉ ግለሰቦች (ቡድኖች) ሊኖሩ እንደሚችሉም አላጣሁትም። እንደ እኔ በቅን ሕሊና የታገዘ ግምጋሜ ግን **ከእኔ በግልጽ ከቀረበ ጥያቄ ይልቅ የትግራይን ሕዝብ በብዙ ጎኑ ሊጎዳው የሚችለው ኢትዮጵያዊነቱን ለማሳጣትና በልዩ ገነት የሚያኖሩ ልዩ ፍጡር የሆኑ ልጆች እንዳሉት አድርጎ ለማሳየት ሲባል በመደረግ ላይ ያለው ነባራዊውን ጠንካራ መሠረት ንዶ ጥበት ብቻ ግድግዳና ማገር ሆኖ ያውሸለሸለው ስንኩል የእንቧይ ካብ ጨዋታ ነው።**

ይህን ስል ግን በጋራ ከሚያገናኙን የኢትዮጵያዊነት መንፈስ በተጨማሪ ለአጭር ጊዜም ቢሆን አብሬው የሠራሁ ከመሆኔ ጋር ተዳምሮ ከታየ እኔም ብሆን እራሴን ከትግራይ ሕዝብ እሩቅ አድርጌ ባላየውም ከራሱ ልጆች እቀርበዋለሁ ግን አልልም። ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ጥያቄውን እንዲያይልኝ የምፈልገው ግን "***አጥፊ ከእናት ሆድ ይወጣል፣ አልሚ (አዳኝ) ደግሞ ከእየሩሳሌም ይመጣል***" እንደሚባለው በክህደት ታውረው እሱንም አብረው በማወር ወደ ጥፋት ገደል ይዘውት ለመግባት ከሚያጣድፉት ልጆቹ ነን ባይ የጥፋት መስተንግዶ አስተናጋጆች ይልቅ የሚጠቅመውንና የሚጎዳውን አመዛዝኖ የወደፊት እድሉን እንዲወስን አማራጭ መፍትሔ ይዞለት የቀረበው የእኔ ጥያቄ ከእነሱ እውር አስተሳሰብ በእጅጉ የበለጠ ነው ብየ ብናገር የተሳሳትኩ አይመስለኝም። ሌሎቹ ይህን ይሉኝ ይሆን የሚያሰኝ ስጋት ሳይኖርብኝ ጥያቄውን በግልጽ ያቀረብኩለትም ለዚህ ነው።

የትግራይ ሕዝብ ለእናት አገሩ የድረሱልኝ ጥሪ ተግባራዊ ምላሽ እንዲሰጣት ጥያቄ ሳቀርብለት ይህ ለሁለተኛ ጊዜ መሆኑ ነው። የመጀመሪያው የኢዴአአህግ እንደተመሠረተ የኢትዮጵያ ሬጅስተር መጽሔት አቅርቦልኝ ከነበሩት ልዩ ልዩ ጥያቄዎች አንዱ የትግራይን ሕዝብ የሚመለከት ነበር። ዝርዝሩን ከመጽሔቱ እትም vol. 5 no.5 May l998 ገጽ61 እና63 መመልከት ይቻላል። በዚያን ወቅት በሚሠመርበት አባባል የገለጽኩት ቢኖር ወያኔዎች የትግራይን ሕዝብ መሳሪያ አድርገው ተጠቅመውበታል እንጅ መሳሪያ ሆኖ አላገለገላቸውም የሚል ነበር። በአሁኑ ወቅት ያለኝ ግምጋሜ ግን ካለፈው የተለየ ነው። ምክንያቱም በአሁኑ ወቅት ብዙ ነገሮች ተለውጠዋል፤ ብዙ ሚስጥሮችም ይፋ ሆነዋል፤ በብኽርታ ተከልለው የነበሩት ብዙ ድብብቆሾችም ምንነታቸው ተጋልጦ ዓላማና ግባቸው በማያጠራጥር ሁኔታ ታውቋል። ለማስረጃም ያህል፣



Document Produced by deskPDF Unregistered :: http://www.docudesk.com

- የታሪካዊ ጠላቶቻችን ቅጥረኞች ስለመሆናቸው የአባቶቻቸው ጌቶች ከሆኑት ኢጣሊያኖች ሙዝየም አውጥተው በድርጊት ላይ እያዋሉት ካለው ካርታ ጀምሮ በቅርቡ ደግሞ የሱማሊያን ሕዝብ እንዲወሩ ታዘው ሄደው በዘመቱት ኢትዮጵያውያን ላይ ያደረሱትን እልቂትና የገዙብንን ጠላትነት፣

- ኤርትራን ለማስገንጠል 60000 ጦር አዝምተው ከማስገንጠላቸው በተጨማሪ ወደፊትም እንደፍራታለን የሚሉ ቢኖሩ ምን እንደሚጠብቃቸው ስብሐት ነጋ የሰጠውን ትምክህታዊ ዛቻ፣

- ባለሐገረ-ብዙው መለስ ዜናዊ በሊቢያዊ አረብነቱ ኢትዮጵያን ለማጥፋት የእቅዱ አካል የሆነውን የባህር በር አያስፈልጋትም ብሎ መዝጋቱን ሚስተር ጂሚ ካርተር የሰጡትን ምስክርነት፣

- በሕዝባዊ ወያኔ ሐርነት ትግራይና በትግራይ ሕዝብ መካከል ስለአለው መስተጋብራዊ ግንኙነት እነ ዶክ/ር ኪርስ ስልጣንና ሌሎችም አባሎች **ወያኔ ማለት የትግራይ ሕዝብ፣ የትግራይ ሕዝብ ማለት ደግሞ ወያኔ** ማለት መሆኑን እያስረገጡ በመስጠት ላይ ያሉትን መግለጫ በውል ማገናዘቡ በቂ ይመስለኛል። ስለዚህ የትግራይ ሕዝብ እነዚህን ሁሉ እያወቀ ዝም ብሎ መቀመጡ መሳሪያ ሆኖ ቢያገለግላቸው እንጅ መሳሪያ አድርገው ቢገለገሉበት አይደለም ከሚያሰኝ መደምደሚያ ላይ ቢደረስ ስህተት ያለው አባባል አይመስለኝም። ለሁለተኛው ጥያቄየ ዋነኛ ምክንያት የሆኑኝም እነዚህ ሁሉ ተዳምረው ነው።

ጥያቄየን ለትግራይ ሕዝብ አቀረብኩ ስል በቦታ ከልየ አይደለም። የትም አገርና ዓለም የሚኖሩትን የትግራይ ተወላጆችና የትግራይን ሕዝብ ችግር እንጋራለን የሚሉትን ኢትዮጵያውያንን ሁሉ የሚመለከት በመሆኑ ለእነዚያ ሁሉ ሊደርስልኝ ይችላል በሚል እምነት ተደግፌ ነው። ስለዚህ የትግራይ ሕዝብ ኢትዮጵያዊ ሐላፊነት የሚሰማው ታላቅ ሕዝብ በመሆኑ እንደትልቅነቱ ጥያቄውን በሰፊ አድማስ አይቶ ለእኔ ሳይሆን የጥያቄው ባለቤት ለሆነው ለኢትዮጵያ ሕዝብ ሁነኛ መልስ ይሰጠዋል ብየ ተስፋ አደርጋለሁ። ከዚህ በተቃራኒው በአንድ በኩል የሥጋ ቆጠራና የቋንቋ ቃና ሰለባ፣ በሌላ በኩል ደግሞ የጊዜያዊ ሁኔታወች ምርኮኛ ሆኖ ካየው ግን የኢትዮጵያ ሕዝብ ያቀረበለት **የእናታችንን ችግር በጋራ እንፍታ ጥሪ (ጥያቄ)** የሚመረው እንጅ የሚጥመው ላይሆን ይችላል። ይኽ ደግሞ የበለጠውን እየመረረ ሄዶ ከመማረር ደረጃ ላይ ስለሚያደርስ በእጅጉ አዝናለሁ ከማለት በስተቀር ከዚያ ጋር ተያይዞ ሊመጣ ስለሚችለው ባለብዙ መዘዝ ችግር የምገልጽበት ተመጣጣኝ ቃላት አላገኝለትም።

በዚህ ጥያቄ ላይ ኢትዮጵያውያን በተለይም ከትግራይ ተወላጆች ቀድመው ሊነሱ ይችላሉ ብየ ከምጠብቃቸው ተቃውሞዎች (ጥያቄወች) አንዱ የትግራይ ሕዝብ ስለታፈነ እንጅ ከመታገል መች ቦዘነ የሚል ሊሆን ይችላል። እኔም ብሆን ጥያቄውን ሳቀርብ ይኽን ሁሉ ሳላገናዝብ ቀርቸ አይደለም። አዎ! በኢትዮጵያዊነታቸው ለኢትዮጵያዊነታቸው እየተናነቁ የወደቁና ብዙ መከራና ስቃይ ያዩ የዚያ አካባቢ ሰወች መኖራቸውን አውቃለሁ። በአሁኑ ወቅትም ምንም እንኳን በጣት የሚቆጠሩ ቢሆኑም ከኢትዮጵያውያን ወገኖቻቸው ጋር ሆነው በየመታገያው መስክና መድረክ አብረው የሚታገሉ እንዳሉም አውቃለሁ። ለኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት በጽናት ቁሞ መታገለን በሚመለከት በእርግጥም በአርዓያነት ከማያቸው ዶ/ር ኃይሉ አርአያ ጀምሮ፣ እሥር ቤት የሚማቅቁት አቶ አበራ የማነ አብ፣ ዶ/ር ግደይ አሰፋ እና አቶ አብርሃ በላይ በምሳሌነት የሚጠቀሱ ናቸው።

ስለሆነም በዚህ እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ኢትዮጵያ መወለዱን ብቻም ሳይሆን ኢትዮጵያዊ እምነቱንና ተግባራዊ ሰውነቱን በገሀድ እያስመሰከረ እንዲያልፍ ወደሚጠየቅበት ከባድ የመፈተኛው መስክና ጎራ በምታስገባው ጠባብ በር ፊት ለፊት ተሰልፎ ምን ያህል እራሱን ሆኖ እንደተገኘ እራሱን ተመልሶ በሚጠይቅበት በዚህ አስተዛዛቢ ወቅት እንደነዚያ ክቡር ጀግኖች አባቶቻቸው ክቡር መስዋእትነት ከፍለው ያለፉት ብቻም ሳይሆን በሕይወት ኑረው በመፋለም ላይ ያሉትን ባለማተብ ጀግኖች ሁሉ በኢትዮጵያ ሕዝብ ቀርቶ በእግዚአብሔርም መንግስት ዘንድ የቅዱስነት ዋጋና የክቡርነት ማእረግ ያላቸው ናቸው ብየ ብናገር አጋንኘ ያቀረብኩት አይመስለኝም። ይህ እንድተጠበቀ ሆኖ አጠያያቂ የሆነው ግን ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን ለማዳን በቁርጠኛነት ከሚዋደቁት ይልቅ ሊያጠፏቸው አቅደው የተነሱትና ተደራጅተው የዘመቱት በእጥፍ ድርብ ከመሆናቸው በተጨማሪ የትግራይን ሕዝብ ሙሉ ድጋፍ አግኝተው ያን ሁሉ ውድመትና እልቂት ማድረሳቸው ነው። ከእኛ ተወልዳችሁ የእኛን ወላጅ እናት አገር አታጥፉብን ብሎ ለምን አምርሮ አልተቃወማቸውም የሚያሰኘውም ይኸው ነው። ከዚህ ይልቅ የኛ ጀግኖች ብሎ አበረታቷቸዋል፣ በጅምራችሁ ግፉበት ብሎም ደግፏቸዋል የሚያሰኙ ብዙ መረጃዎችን መጥቀስ ይቻላል።



Document Produced by deskPDF Unregistered :: http://www.docudesk.com

በመሠረቱ የትግራይ ሕዝብ የአንድነት መሠረት፣ የሥልጣኔ ምንጭና የረጅም ዘመናት የተጋድሎ ታሪክ ያለው ሕዝብ መሆኑን ማዎቅ የቻልኩትን ያህል አውቃለሁ። ይኸም ብቻ ሳይሆን የእነዚያ ክቡር ታሪክ ሠርተው ያለፉ ክቡር ሰዎች የአደራ ታሪክ ተረካቢ መሆኑንም አውቃለሁ። ይህንን ጥያቄ እንዳቀርብለት ከገፋፉኝም መሠረታዊ ነጥቦች ዋናው ይኸው የትላንት ጀግኖች አባቶቹ የጣሉት የብሔራዊ አንድነት መሠረትና የገነቡት አኩሪ ታሪክ በዛሬዎቹ ከእሱ ጽኑ እምነትንና ኢትዮጵያዊ ሐላፊነትን ባልወረሱ ከሀዲ ልጆቹ ሲናጋና ሲናድፍ በገሐድ እያየ ለምን በይሁንታ ደገፋቸው? ወይም በዝምታ አያቸው? የሚል ከፍተኛ ቅሬታ ስለአሳደረብኝ ነው። ይህን ያደረገው ዓላማቸው ስለአልገባው ወይም የሚያደርጉትን ስለማያውቅ ነው የሚል ተቃውሞና ተቃዋሚወች መቸም ቢሆን ይኖራሉ ብየ አልጠብቅም። ካሉም በዋቢነት ከማቀርባቸው ማስረጃዎች በኋላ የምንገመግመው ይሆናል። እኔ እንደገምትኩት ፍጥጫው ሊኖር የሚችለው ከይሁንታው ጋር በተያያዘ ነው። በዚህ ችግር ላይ ግን የኔን ጥያቄ በመቃወም አራት ወገኖች የየራሳቸውን አቋም ወክለው ሊሰለፉ ይችላሉ የሚል ግምት አለኝ። እነርሱም፦

1. የሕዝባዊ ወያኔ ሐርነት ትግራይ አባሎችና በጥቅም የደለቡ ደጋፊወች፣
2. አዲሶቹ ምልስ ኢትዮጵያውያን ለአከማቹት የችግር ጥሪት መፍቻ ብለው ያቀረቡት አዲሱ ስልት፣
3. የትግራይ ሕዝብ እንደሌላው አካባቢ ሕዝብ ታፍኖዋል የሚል አመለካከት ያላቸው ወገኖች እና
4. ለትግራይ ሕዝብ የተለየ ጥያቄ ማቅረብ ለወያኔዎች ፕሮፓጋንዳ ያመቻል የሚል ስጋት የሚኖርባቸው ኢትዮጵያውያን ሊሆኑ ይችላሉ። የለየላችውን የወያኔ አባሎች ሳይጨምር የሌሎቹ (3ና4) አቋም በአገሪቱ ላይ እየተካሄደ ያለው ማናጋትና በሕዝቧ ላይ እየተፈጸመ ያለው እልቂት ወደፊትም ይቀጥል ለማለት ካልሆነ በስተቀር በእኔ ጥያቄ ላይ አለ የሚሉትን ጎጅ ጎን ለይተው ማሳየት የሚችሉበት ዋቢ የሚጠቅሱልኝ አይመስለኝም። እኔ ግን የአባባሌን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ የምፈልገው አልተደረገም ብሎ ለማስተባበል ቀርቶ የሚያሻማ ትርጉም ሰጥቶ ይኸን ይመስላል ለማለት እንኳ የማያመቹ ብዙ ተጨባጭ መረጃወችን በመጥቀስ ነው።

ሀ/ <u>ማገናዘቢያ መረጃዎች</u>፣

በመጀመሪያ የትግራይ ሕዝብ ወያኔዎች የሚያካሂዱትን ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን የማጥፋት ዘመቻ ደግፎዋል ብሎ ለመቃወምም ይሁን ተቃውሟል ብሎ ለመመስከር የሚቻለው ሁለቱን ተቃራኒ ሐሳቦች ሊዳኙ የሚችሉ ተጨባጭ መረጃዎች በመካከላቸው ቁመው እንዲመሰክሩ ማድረግ ሲቻል ነው። ከዚህ አንጻር የ18 ዓመቱን ቃላት ሊገልጸው ከሚችለው በላይ የሆነ ግፍና በደል በዝርዝር ለመግለጽ ስለሚከብድ የማተኩረው ለዋቢነት በሚሆኑኝ ዋና ዋና ነጥቦች ላይ ብቻ ነው።

በመሠረቱ ስለወያኔዎች ሁለንተናዊ የውድመት ዘመን ትክክለኛ ታሪኩን ለመግለጽ ብቁ ባለሞያ መሆንን ይጠይቃል። ይህን በሚመለከት ከአቻ የለሽ ክህደታቸው፣ ከእኩይ ግብራቸውና ከአስከፊ ድርጊታቸው አኳያ ተመጣጣኝ የግብር ስም እንዲያወጡላቸው በአንድ ወቅት ባለሞያወችን ማሳሰቤን አስታውሳለሁ። እኔ ግን በተረዳኋቸው መጠን **ግብረ-አራዊት** ቢባሉ በመጠኑ ይገልጻቸዋል ብየ አምናለሁ። ምክንያቱም እንደሚታወቀው አውሬ ያየውን ሁሉ ገድየ መጨረስ አለብኝ ብሎ የሚቅበዘበዘው እውን የገደለውን ሁሉ በልቶ ለመጨረስ የሚያስችል አቅም ኖሮት ሳይሆን ማጥፋት የተፈጥሮ ባህሪው በመሆኑ ነው። ስለዚህ የወያኔዎችም ሁለንተናዊ ባህሪና ግብራቸው ሲገናዘብ ከቅርጽ ጥያቄ በስተቀር ከአራዊት የሚለዩበት አንዳችም ነጥብ የለም።

እንደሚታወቀው 18 ዓመት ቀላል እድሜ አይደለም። በሰለጠነው ዓለም አንድ ልጅ ተወልዶ በየእድሜ ደረጃው መማር የሚገባውን ትምህርት አጠናቅቆ እራሱን ለመምራት የሚችልበትና ለሐላፊነት የሚታጭበት የእድሜ ደረጃ ነው። በእኛ አገር ግን ሕዝቡ የወለዳቸውን ልጆች አስተምሮ ለቁም ነገር ከማብቃት ይልቅ በኤድስና ከኤድስ በባሱ ጠላቶቹ የሚገደሉትን መቅበርና ተነቅለው የሚሰደዱትን እያለቀሰ መሸኘት፣ በየእስር ቤቶቹ ታጉረው ለሚሰቃዩት ደግሞ ስንቅ ይዞ ለመጠየቅ የሚችልበት አቅም ባይኖረውም ቢያንስ እግዚአብሔር ያስፈታችሁ ብሎ መመለስ የዘወትር ሥራው ሆኗል። ከእነዚህ ሁሉ በይበልጥ ከባድ ሸክም ሆኖ ያጎበጠውና መሪር ሐዘን ሆኖ ያስጨነቀው ግን ለሚያጋጥሙት ችግሮች ሁሉ ማስተናገጃና የሐዘኑ መክሊያ፣ የመረረ ሕይወቱ ማጣፈጫና የተስፋ ራዕዩ ማለምለሚያ፣ ከሞት ለተረፉት ልጆቹ ማሳደጊያና የእሱም የክብር ማረፊያ፣ በአጠቃላይም የሰው ልጅ መፈጠሪያ የሆነችው እናት አገሩ ጭምር በእነዚሁ መግደልና ማጥፋትን



Document Produced by deskPDF Unregistered :: http://www.docudesk.com

የሕይወታቸው ምግብ አድርገው በሚኖሩ አራዊቶች እየተገደለች በመሄዱ በየቤቱ ድንኳን በመትከል ሐዘን ተቀምጦ እያለቀሰ ያሳለፈበት ዘመን ነበር ቢባል ከዚህ ችግር ላይ ከጣሉት ጣምራ ጠላቶቹ በስተቀር እንዲህ ያለው መሪር ሐዘን አልደረሰብንም ብሎ የሚያስተባብል ኢትዮጵያዊ የሚገኝ አይመስለኝም። በዚህ ለዘመናት ደርሶበት በማያውቀው የጥፋት መልእክተኞች ዘመን የእስከ አሁኑ ብቻም ሳይሆን ወደፊትም ቢሆን የእኛ ዝግጁነት እስከ አልገታቸው ድረስ ሊቀጥል በሚችለው ውስብስብ ችግር ላይ ተመሥርቶ መነሳት ያለባቸው ተዛማጅ ጥያቄዎች ወያኔዎች የማጥፋት ዘመቻቸውን የሚያቆሙት መቼ ነው? የሚያስቆማቸውስ ማንነው? እስካሁን ያደረስነው ጥፋትና የፈጸምነው እልቂት አልበቃንም ብለው በጅምራቸው የገፉበት ዓላማና ግባቸው ምን ቢሆን ነው? ወዘተ መሆን አለባቸው። እነዚህን ጥያቄዎች መሠረት አድርጌ ወደ ትግራይ ሕዝብ ይሁንታም ይባል ዝምታ ልሸጋገር።

1/ በመጀመሪያ መጠሪያ ስማቸውንና ይዘውት የተነሱትን ዓላማ ብንመለከት "**ሕዝባዊ ወያኔ ሐርነት ትግራይ**" ማለት የትግራይ ሕዝብ ነፃ አውጭ ድርጅት ማለት መሆኑ ለማንም ግልጽ ነው። ይኸም ማለት ድርጅቱ የሕዝቡ፣ ሕዝቡም የድርጅቱ መሆኑን እነ ዶክ/ር ኪሮስ ስልጣንና ሌሎቹ የወያኔ ካደሬዎች አራጋግጠውልናል። እንዲያውም እያንዳንዱ የትግራይ ተወላጅ በቤተሰብ ደረጃ አንድ ብቻም ሳይሆን ከአምስት እስከ ስድስት የሚደርሱ ልጆቹን የገበሩለት ድርጅታቸው መሆኑን አባሎቹ አዘውትረው በኩራት የሚናገሩት ነው። ይህን ሁሉ መስዋእትነት ከፍለው ከማን ነፃ እንደሚወጡ ወይም የነበራቸውን ነፃነት እንደሚያጡ አብረው ቀምመው ከቋጠሩት ድብቅ መርዝ ጋር ተዳምሮ ብዙ የሚያጠያይቁ ጥያቄዎች በውስጡ ቢኖሩበትም ጊዜ ይፍታው ብየ አልፌዋለሁ።

<u>*2/ የትግራይ ወያኔዎች ቡድን ማለት ከትግራይ ሕዝብ፣ በትግራይ ሕዝብ፣ ለትግራይ ሕዝብ ነፃነት ቁመናል በሚል ከለላ የተሸፈኑ የብሔራዊ አንድነት ጠላቶች፣ የአኩሪ ታሪክ አጉዳፊወች፣ የኢትዮጵያዊነት ትውልድ ገዳዮች፣ ኢትዮጵያዊነት እምነትና የወንድማማችነት ፍቅር ጨርሶ ያልፈጠረላቸው አንጡራ ባዕዶች ስብስብ ማለት ነው።*</u> ዓላማቸውም ታላቂቱን ታሪካዊት አገር አጥፍተው በቆዳ ስፋቷም ሆነ በሕዝብ ብዛቷ ከሌሎች ክፍለ-ሐገሮች የማትበልጠውን ትንሿን ትግራይ ወደ ትልቅነት መለወጥና የእኛ ብቻ ነው የሚሉትን የአክሱም ሥርወ መንግሥት መልሶ ለማቋቋም ነው። ለዚህም ነው ከጎንደር፣ ከወሎና ከአፋር የአስተዳደር ክልል እየተቆረጠ የሚለጠፍላትና በብሔራዊ የሕዝብ ቆጠራ ወቅት ከአማራው ሕዝብ ቁጥር ላይ እንደ ቆሎ እየዘገኑ የሚጨምሩላት።

በመሠረቱ በሰይጣናዊ ሥራ የገነት ጌታ መሆን እንደማይቻል በውል ቢገባኝም እንችላለን እስከ አሉ ድረስ በትግራይ ገነት መሆን እኔም ሆንኩ መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ምንም ዓይነት ተቃውሞ የለንም። በጽኑዕ የምንቃወመውና በቁርጠኛነት የምንታገለው ግን ትግራይን ትልቅ ማድረግ የምንችለውና ልማቷን ገነት የምናስመስለው ኢትዮጵያን አስቀድመን ስናጠፋት ነው ብለው በማካሄድ ላይ ያሉትን መዘዘ ብዙ ዘመቻ ነው። ከማሳዘንም አልፈው የማይሽር ቁስል ሆነው ሲያመረቅዙ ከሚኖሩት የግፍ ድርጊቶቻቸው አንዱን በዋቢነት ብጠቅስ በወረሩዋቸው አካባቢዎች የሚኖረውን የአማራ ሕዝብ በግዞት አግደው ይዘው በግድ ትግሬ ለማድረግ የቁም ስቃይ ከማሳየታቸውም አልፈው በእምነትና ባህላቸው ተጋብተው በሰላም የሚኖሩትን የቃል-ኪዳን ባልና ሚስቶች በግድ እያፋቱ ባሎቻቸውን ለግድያና እስራት በመዳረግ ሚስቶቻቸውን ደግሞ ለእነሱ ዲቃላ መፈልፈያ ባዝራ አድርገው በመገልገል የሚፈጽሙት ታላቅ የዘር ማጥፋት ወንጀል ነው። (በወልቃይትና ጠገዴ ወገኖቻችን ላይ የሚፈፀመውን ግፍ ልብ ይሏል።)

3/ ውያኔዎች ከቃል-ኪዳን ጌቶቻቸው በወረሱት ልምድ በመታገዝ የኢትዮጵያን የዘመናት አኩሪ ታሪክ ማጉደፍና የጀግኖች ልጆቿን አጽም ማፍለስ ሥራየ ብለው የተያያዙት ዘመቻ በመሆኑ፣

3.1 ከሦስት ሽህ ዘመናት በላይ የመንግሥትነት ታሪክ ያላትን አገር በመቶ ዓመት ገድበዋታል። የቃል ኪዳን ምልክት፣ የአንድነት ማተብና የነጻነት ሰንደቅ ሆና የኖረችውን ክቡርና ብርቅ ሰንደቅ ዓላማችንን ደግሞ ተራ ጨርቅ ናት ብለው የዱቄት መቋጠሪያ አድርገዋት ነበር።

3.2 ኤርትራ የኢትዮጵያ አካል መሆኑዋን ክደው በቅኝ ግዛት ስትገዛት ኑራለች ይላሉ። አጼ ዮሐንስና ራስ አሉላ ወደኤርትራ ዘምተው ከቱርኮች፣ ከግብጾችና ከጣሊያኖች ጋር የተዋጉትም እሷን በቅኝ ግዛት ለመግዛት ነው ብለው ደምድመዋል። በዚያን ዘመን በተካሄዱት ጦርነቶች ግንባር ቀደም ገፈት ቀማሽ ሆነው የዘመቱትና ክቡር መስዋዕትነት ከፍለው ያለፉት የትግራይ ሕዝብ ልጆች መሆናቸው ግን አያጠያይቅም። ከእነዚያ ጀግኖች ተወልደናል የሚሉት የአሁኖቹ የእንግዴ ልጆች ግን የታላቁን ንጉሥና ክቡር ታሪክ ሠርተው ያለፉን ጀግኖች አጽምና ታሪክ እያረከሱትና የክህደት አረም እያለበሱት ናቸው።



Document Produced by deskPDF Unregistered :: http://www.docudesk.com

3.3. ታላቁ ንጉሥ አጼ ዮሐንስ አንገታቸውን የተሰየፉበትንና ንጹህ ደማቸውን ያፈሰሱበትን በልዩ ልዩ ማእድናት የበለጸገ ለም መሬት ለታሪካዊ ጠላቶቻችን ለማስረከብ የሚያስችላቸውን ዝግጅት ጨርሰው እየተጠባበቁ ነው። (እንዲያውም በቅርቡ ከአፄ ዮሐንስ አንገት ሰያፊ ድርቡሾች ጋር ከኢትዮጵያ ሕዝብ ደብቀው በተፈራረሙት ውል ይህንኑ ታሪካዊና በማዕድን የደለበ መሬታችን አስረክበዋል የሚል ዕምነት አለኝ።) አገር ሲያረጅ ጃርት ያፈራል እንደሚባለው ሆኖ እንጅ ከእኒያ ታላቅና ክቡር ንጉሥ በመወለዳችን ጋሻቸውን አንስተን ክብራቸውን መውረስ አለብን ማለት የሚገባቸው ዘመን አፈራሽ አፈሪያቶች አንገታቸውን ቆርጠው ወስደው ሙዚየማቸው ውስጥ በማስቀመጥ የአንገት ሠያፊ ጀግንነታቸው መፎከሪያና የእረፍት ጊዜያቸው መዝናኛ ካደረጓቸው የአባት ገዳይ ባለደሞች፣ የጎንደርን ከተማ ወርረው ያን ሁሉ አረመኔያዊ (ናቸውም) እልቂት ከፈጸሙ ታሪካዊ ጠላቶች ጋር ግንባር ፈጥረውና እምነትና ፍቅራቸውን አድርተው የኢትዮጵያን የተፈጥሮ ሐብት አሳልፈው መስጠታቸው ብቻ ለትግራይ ሕዝብ በቂ ማረጋገጫ ነበር። የትግራይ ሕዝብ ግን ባድሜን ብቻም ሳይሆን እነዚህ ሁሉ የእኔም ናቸው ብሎ ካልተከላከላቸውና አሳልፈው ከመስጠትና እየቆረሱ ከመሸጥ የማይመለሱትን  ልጅ መሰል ጠላቶች  ካልተጋፈጣቸው  ዘብ ቁሞ የሚጠብቃቸው የትኛወቹንና መቸ ሊሆን ነው?

4/ ቀደም ሲል እንደገለጽኩት ኢትዮጵያ በቅኝ ግዛት እየገዛቻት ነው የሚሏትን ኤርትራን ነፃ ለማውጣት 60000 አስገንጣይ ጦር አዝምተው ኤርትራን ማስገንጠላቸው ለትግራይ ሕዝብ ድብቅ አይደለም። ሌላው ቢቀር ለማስገንጠል ከአዘመቱት ጦራቸው ውስጥ በወጡበት የቀሩት የ15000 ወጣቶች ቤተሰቦች መርዶ ሲቀመጡ ልቅሶ ሳይደርሳቸው እንደማይቀር እርግጠኛ ነኝ። እንዲያውም ሻቢያዎች ከደርግ ጋር ተደራድረው ሊገቡ የነበራቸውን እቅድ አክሽፈው ኤርትራ እንድትገነጠል ያደረጓትና ወደፊትም በኤርትራ ላይ ለሚቃጣው ማናቸውም ሙከራ ቀድመው የሚሰለፉላት እነሱ መሆናቸውን ያለምንም ሐፍረት እየነገሩን ናቸው። የባህር በሯንም ለኢትዮጵያ አያስፈልጋትም ብለው ማስረከባቸው ከዚሁ ጋር በተያያዘ ነው። ይድረጋል ብሎ ለማመን ቀርቶ ይታሰብ ይሆን ብሎ ለመጠራጠር እንኳ በእጅጉ የሚከብደው ተቆራርጣ የቀረችውን ግዙተኛ አገር ደግሞ እነሱ እስከ አልገዟት ድረስ ጨርሰው እንደሚያጠፏት እየዛቱባት መሆናቸው ነው። እንዲህ ያለው ኢትዮጵያን ጨርሶ የማጥፋት አዋጅ የትግራይ ሕዝብ በተለይ እንዲያውቅ የተነገረው ደግሞ በጠላትነት በተፈረጀው አማርኛ ቋንቋ ሳይሆን የራሱ በሆነው በትግርኛ ቋንቋ ነው። የትግራይ ሕዝብ ግን አዋጁን እንደ መርዶም ይስማው ወይም እንደ ከፍተኛ የጀግኖች ድል ይቁጠረው ያሰማው ድምጽና ያሳየው ለውጥ የለም።

5. በባድሜ ግንባር ለተካሄደው ጦርነት ከ100000 ያላነሱ ኢትዮጵያውያን እንደ ብረት ለበስ ተሽከርካሪ የፈንጅ መጥረጊያ ሆነው እንዲያልቁ እንዳልተደረገ ሁሉ (የትግራይ የአስተዳደር ክልል ስለሆነ ማለት ነው) በምእራቡ የአገሪቱ ወሰን ግን ጠላቶቻቸውን ወዳጅ አድርገው ስለመረጡና ወገኖቻቸውን በጠላትነት ስለፈረጁ 1600ኪ/ሜ እርዝመትና 70 ኪ/ሜ ጥልቀት ያለውን እምቅ የማዕድን ሐብትና ለም አፈር ያለው ሰፊ መሬት እንደ ባህር በራችን ፈርመው ለታሪካዊ ጠላቶቻችን ለማስረከብ እየተዘጋጁ መሆናቸውን እያወቀ ለምንና እንዴት እንዲህ ይደረጋል ብሎ አልጠየቀም።

6. የኢትዮጵያ ሕዝብ ማህበራዊ ደሕንነቱ የተናጋውና በችግር አዘቅት ውስጥ ወድቆ የሚሰቃየው፣ ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቱ ተገፍፎ ለሐብትና ንብረቱ ቀርቶ ለሕይዎቱ እንኳ ዋስትና አጥቶ በግፍ የሚገደለው፣ እነዚህና ሌሎችም ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ቀውሶች በተቀነባበረ መልክ የሚካሄዱት እንደ ትላንቱ ከባህር ማዶ በመጡ (እንዲህ ያለውን የለየለት አረመኔያዊ ድርጊ ለማካሄድ እድልና ፋታ ባያገኙም) ታሪክ ያወቃቸው ጠላቶቻችን ሳይሆን ከእሱ በተወለዱ ልጆቹ መሆኑን እያወቀ በወንድማማችነት መንፈስ እየተሳሰብን፣ ደስታውንና ሐዘኑን እየተጋራን ከኖርነውና እየተጋባን ከተዋለድነው ወገናችን ጋር በቀላሉ ነቅለን ለማንጥለው ቂም በቅል፣ አጥበን ለማጽዳት ለማንችለው የንጹሐን ደምና ከፍለን ለማንጨርሰው በታሪክ ሲያስጠይቅ የሚኖር ባለብዙ መልክ እዳ ለምን ታመጡብናላችሁ ብሎ በመጠየቅ አልተጋፈጣቸውም።

## ለ. <u>የትግራይን ሕዝብ ከኢትዮጵያዊነቱ ለማቆራረጥ እየተደረገ ያለው ርብርቦሽ፣</u>

ወያኔዎች ኢትዮጵያዊነታቸውን ሽጠው በልተው የጨረሱ ሁለንተናዊ ድሐዎች በመሆናቸው እራቁታቸውን ቁመው ለቀሩበት እርቃናቸው መጠለያ ለማግኘት ሲሉ የትግራይን ሕዝብ ሞጭጨው ይዘው የሚያደርጉትን መማጸን በቀላል ምሳሌ ብገልጸው ደህና ይመስለኛል። ከሰው ልጅ መሠረታዊ ፍላጎቶች አንዱ መጠለያ መሆኑን የማህበራዊ ኑሮ ጠበብትና የፍልስፍና ሰወች ይናገሩታል። መጠለያ ስሙ እንደሚያመለክተው ጊዜያዊ መኖሪያ ብቻም ሳይሆን የጊዜ ወለድ ችግሮችም መከላከያ ስለሆነ ህይወት ያላቸው ፍጡሮች ሁሉ



Document Produced by deskPDF Unregistered :: http://www.docudesk.com

ይገለገሉበታል። ለምሳሌም አይጦች ከመጠለያ ጉድጓዳቸው ወጥተው እንደልባቸው መሆን የማይችሉበት ብዙ ችግሮች አሉባቸው። የአዝመራው ወይም የቁሳቁሱ ጌቶች፣ ድመቶች፣ ጭልፊቶች፣ ወዘተ። የትግራይን ሕዝብ መደበቂያ ምሽግና መግደያ መሳሪያ አድርገው በመገልገል ላይ ያሉት ወያኔዎችም በዚህ አባባል የሚገለጹ ናቸው። ከሕዝቡ ተለይተው ቀርቶ ለአፍታ እንኳ ፊቱን ቢያዞርባቸው ፀሐይዋ ጠቁራ ጨለማ የሚውጣቸውና ሰማዩ የሚደፋባቸው መስሎ ስለሚታያቸው እንዲህ ያለውን ከባድ ጭንቀት እየተከላከሉ የሚኖሩት ለእነሱ ጊዜያዊ እፎይታ የሚሰጥ ጭንቀት እየፈጠሩ የትግራይ ሕዝብ እንዲጨነቅ በማድረግ ነው። ይህን ለማድረግ ደግሞ ነፃ አመለካከቱን የሚጋርዱ ብዙ የሥነ-ልቦና ሰላባወችና ብሩህ እይታውን አደብዝዘው ትክክለኛ አቅጣጫውን እንዲስት የሚያደርጉ ከበባዎች ሲካሄዱ ኑረዋል። የቅንብራቸውን አጠቃላይ ሥዕል ለማሳየት የሚችሉትን አበይት ነጥቦች ከዚህ ቀጥሎ ለማመልከት እሞክራለሁ፦

1. የትግራይን ሕዝብ ከሌላው ኢትዮጵያዊ ወገኑ ጋር በጋራ መድረክ ተገናኝቶ በጋራ ጉዳዮች ላይ እንዳይወያይ፣ በማህል አገር ስለሚደረጉ ማናቸውም እንቅስቃሴወች መረጃወች እንዳይደርሱት፣ ለዘመናት አብሮት የኖረውንና ያኗኗረውን አብሮነቱን ግምት እንዲያሳጣው፣ በኢትዮጵያዊነት መንፈስ ሲገነባ የኖረውን የወንድማማችነትና የእህትማማችነት ፍቅር ከጥላቻም አልፎ በጠላትነት እንዲፈርጀው፣ በአጠቃላይም ኢትዮጵያዊነቱን እንደውርደት ትግራይነቱን ደግሞ እንደ ልዩ ፍጡርነትና ወርቅ ሕዝብነት አድርጎ እንዲያየው የሚያደርግ ርብርቦሽ ያለማቋረጥ በቀጣይነት እየተካሄደ ነው።

2. የአንድነት መሠረትነቱንና የዘመናት ታሪኩን ቆራርጠው ወደ መንደርተኝነት በመመለስ በሱ ብቻ ለሱ ብቻ የምትሆን ታላቋ የትግራይ ሪፐብሊክ ልትገነባልን ነው ብሎ በምኞት ባህር እንዲዋኝ እያደረጉት ናቸው። በዚህ ላይ ተመሥርተው በድርጊት ለማሳየት የጀመሩትን በፊደል "ሀ" ተራ ቁጥር 2 ከዚህም ጋር አብሮ ያገናዝቧል።

3. ከሌሎቹ ባይበልጥም ከሌሎቹም ሳያንስ የኖረበትን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ኑሮና ችግሮች የበለጠ አግዝፎ በማቅረብ በለም መሬቶቿ ብቻም ሳይሆን ከድንጋዩ ላይ ውሐ እናፈልቃለን እንደማለት በሚያስቆጥር ከገሀድ እውነታው በራቀ አቀራረብ ደን አልምተውና የተንጣለለ አዝመራ አዝምረው ምድራዊ ገነት የሆነች ትግራይን እንደሚገነቡለት አድርገው እየወተወቱት ናቸው። እቅዳቸውን በቅርጻዊ ለውጥ ለማሳየት ሲሉ ደግሞ፣-

3.1 መንግሥታዊ መ/ቤቶችን የብሔራዊ መግሥት የአደረጃጀት ቅርጽ እንዲኖራቸው አድርገዋል።

3.2 ታላቋን የትግራይ ሪፐብሊክ ዕድገት ለማፋጠን የሚያስችሉ ልዩ ልዩ ግንባታወችን በየመስኩ

በማካሄድ ላይ ናቸው።

- በሌላው አናትና ሕይዎት ላይ አቋርጠ የሚያልፍ አዲስ ከፍተኛ የኤሌክትሪክ መስመር ዘርግተውና ቀደም ሲል ሕዝብ ሲገለገልባቸው የነበሩትን ነቅለው ወስደው ትግራይ ላይ ብቻ እንዲያበራና ልማቷን እንዲያፋጥን እየተደረገ ነው።

- በሌላው አካባቢ ደረጃውን የጠበቀና ከትርምስ የጸዳ የትምህርት አሰጣጥ ሥርአት ሳይኖር በትግራይ ግን በኮምፒዩተር ቴክኒወሎጅ የሚታገዝ ሥርአተ ትምህርት እየተካሄደ ነው።

- በየደራጃው ከተገነቡት ዩኒቬሪስቲውች፣ ኮሌጆች፣ ሁለተኛና አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በተጨማሪ በየቀበሌው ለመገንባት የሚያስችል እቅድ ነድፈው እያካሄዱ ናቸው።

- ዘመናዊ የኮምፒውተር ቴክኔዎሎጅን በመጠቀም በየትኛውም የትግራይ ወረዳ ውስጥ የሚገኝ የትግራይ ገበሬ ዋና ከተማው መቀሌ ላይ በተሰየመ ከፍተኛ ፍ/ቤት ዳኛ መዳኘት የሚችልበት ሁኔታ ያመቻቹለት መሆናቸውን እኛ በስማ በለው የሰማነው ሳይሆን እነርሱ ራሳቸው ነግረውናል።

- በመገናኛና በሕክምና አገልግሎት፣ በከተማና ገጠር ልማት፣ በዓለም አቀፍ አውሮፕላን ማረፊያና በፋብሪካ ግንባታ ወዘተ እራሷን ለማስቻል እየተረባረቡ ነው።

- በትግራይ አካባቢ ለሚካሄዱ ሁለንተናዊ ግንባታወች ይጠቅማሉ የተባሉ ማናቸውም



Document Produced by deskPDF Unregistered :: http://www.docudesk.com

ተንቀሳቃሽ ንብረቶች ከየአሉበት እየታደኑ ከተተከለበት ተነቅለው፣ ከለሙበት ተመንጥረውና ከተቀመጠበት ተጭነው እንዲጓጓዙ እየተደረገ ነው።

- ለኢትዮጵያ የባህር በር አያስፈልጋትም ብለው እንዳልዘጉት ሁሉ ለታላቋ የትግራይ ሪፐብሊክ ግን ከውጭው ዓለም ጋር በየብስ፣ በአየርና በባህር ለማገናኘት የሚያስችል እስትራተጅካዊ ጥናትና የግንባታ ሥራ በማካሄድ ላይ ናቸው።

- የአካባቢው ሰወች ችሎታቸው በማይመጥን የሐላፊነት ቦታ ላይ እየተመደቡ በሥልጣን እንዲባልጉ፣ የሌሎችን መብት እንደፈለጉ እየረገጡ በአጭር ጊዜ ውስጥ ክፍተኛ የሐብት ክምችትና የማህበራዊ ኑሮ ለውጥ እንዲኖራቸው በመደረጉ መረን የለቀቀ ትምክህት እንዲያተብታቸው እየተደረገ ነው። በአጭር አባባል በአገሪቱ ውስጥ አካባቢም ሆነ የሥራ መስክና የሞያ ዓይነት ሳይገድባቸው ቁልፍ በሆኑ የሐላፊነት ቦታወችና ዋና ዋና የገቢ ምንጭ መገኛ በሆኑ መ/ቤቶች ከላይ እስከታች ተሰግስገው እንደፈለጉ የሚያዙትና ሚናዝዙት እነሱ ብቻ ናቸው። በአሁኑ ወቅት የማይፈልጓቸው ወይም ለሊዝ ሺያጭ የማያቀርቧቸው ቦታወች ቢኖሩ እስር ቤቶች፣ የመለመኛና የመቃብር ቦታወች ብቻ ናቸው። የጊዜ ጉዳይ እንጅ እነዚህንም ቢሆን ተረክበው እነሱ ብቻ የሚኖሩባቸው መሆናቸው እንደማይቀር ግልጽ እየሆነ የመጣ ይመስለኛል።

- የሌላው አካባቢ ሕዝብ ደግሞ ሁልጊዜም ቢያልቡት የማይደርቅ፣ ቢጋልቡት የማይራገጥና ሲነዱት ውለው ሲነዱት ቢያድሩ ደክሞኛል ብሎ የማይቁነጠነጥ ወኔ የለሽ እንደሆነ አድርጎ በማየት ጀግና ነን ባይነታቸውን ብቻም ሳይሆን ሰው መሆናቸውን እንኳ እስከ መርሳት የሚያደርስ ትምክህት እንዲያውራቸው እየተደረገ ነው።

4. የትግራይን ሕዝብ በከፍተኛ ስጋት አስጨንቆ በመያዝ ሌሎች ጠቃሚ አማራጮችን በትክክል እንዳያይ እያደረጉት ናቸው።

4.1 እኛ ከሌለን አንተም አትኖርም፣ የደርግና የኢሠፓ እርዝራዦችና ጦርነት ናፋቂ ፀረ-ሰላም ኃይሎች ዘምተው ያጠፉሀል እያሉ ከፍተኛ የሥነ-ልቦና ሺብር በመፍጠር እነሱን ብቻ እያመለከ እንዲኖር፣

4.2 በአንድ በኩል እቅዳቸውን ለማሟላት በሌላ ብኩል ደግሞ እንደፈለጉ ሲፈልጡና ሲቆርጡ ከኖሩበት ሥልጣን ድንገት አድጧቸው ቢወድቁ ወደ ምሺጋቸው ተመልሰው ገብተው ሕዝቡን እርስ በእርሱ ሲያጫርሱ ለመኖር የሚያስችላቸውን ከፍተኛ የጦርና የመሳሪያ ክምችት በአካባቢው በማከማቸት የትግራይን ሕዝብ ከሰላም ይልቅ ለጦርነት እንዲዘጋጅ እያደረጉት ናቸው።

5. የልጆቹ ጀግንነት ጦር በዓይናቸው ቢሰካ እንኳ የማያፈሰውና ግንባራቸውን ጥይት የማይበሳው፣ መግደል የሚችሉ እንጅ ሞትና መገደል የሚባል ነገር የማይደፍራቸው (እንደ ረቂቃን መላእክት ማለት ነው) በመሆናቸው ግዙፉን የደርግ ሠራዊት ደምስሰው ለመንግሥትነት የበቁና ሰውን ብቻም ሳይሆን ተራራውን ሁሉ እስከ ማንቀጥቀጥ የደረሱ ጀግኖች መሆናቸውን እጹብ ድንቅ ብሎ እንዲቀበለውና ዘላለማዊ እንደሆነ አድርጎ እንዲያየው ልዩ ፊልም አዘጋጅተው እየሰበኩ ናቸው።

5.1.ብዙ ስምና ልዩ ክብር የሰጡት ጦራቸው አገር አጥፊነቱንና ሕዝብ ጨፍጫፊነቱን በአስተማማኝ ዝግጅት እንዲቀጥል ለማድረግ ለሞቱት ሐውልት እንዲቆምላቸው፣ በሕይወት ለአሉት ደግሞ በሹመትና ሺልማት እንዲያሸበርቁ ተደርጓል። ከእነዚህም አንዱ ረጅም የአመሠራረት ታሪክ ያለውና ክመጀመሪያው የማይጨው ዘማቾች ጀምሮ ብዙ እውቅ መኮንኖችን ሲያፈራ የኖረው የሆለታ ገነት ጦር ት/ቤት በአንድ ተራ አገር አጥፊ ወንበዴ ወንድማቸውን ለገደሉበት ስውር ሴራ መሸፈኛ እንዲሆን ታቅዶ በእሱ ስም ተለውጦ እንዲጠራበት መደረጉን እጅግ በሚከነክን ህሊና አብሮ ማገናዘብ ያስፈልጋል።

5.2. ለአገሪቱ ብሔራዊ አንድነትና ዳር ደንበር መከበር ሲዋደቅ የኖረውና በዚያ እጅግ ከባድ በነበረ መራራ ሁኔታ ውስጥ አልፎ ሕይወቱ በታምር የቆየችው የአገሪቱ ብሔራዊ የመከላከያ ሠራዊት ግን እንደወንጀለኛ ተቆጥሮ እንዲበተንና ከጦርነት በባሰ ችግር ወስጥ ወድቆ ሁለት ጊዜ (በጦርነትና በረሐብ) እንዲገደል ተደርጓል። ይህን ያደረጉት እነሱ ለዘመቱባቸው እናት አገርና ሕዝብ እራሱን አሳልፎ መስጠቱን ወንጀል አድርገው ስለአዩበት ነው።



Document Produced by deskPDF Unregistered :: http://www.docudesk.com

6. የወያኔ መሪወች በኤርትራዊነታቸው  እነዚያን ሁሉ ኢትዮጵያንን ካስፈጁ በኋላ በድርድር ሰበብ ባድሜን ብቻም ሳይሆን ሌላውን ሁሉ ጨማምረው ለሻቢያ ለማስረከብ ፍላጎት ቢኖራቸውም የትግራይ ሕዝብ ያምጽብናል ብለው ፈርተው እንዳዘገዩት የአደባባይ ሚስጥር ነው። የወያኔ አባሎችም በበኩላቸው መለስ የትግራይ ሕዝብ ልጅ ስለሆነ እሱን ማውረድ የሚችለው የትግራይ ሕዝብ እንጅ ሌላው አይደለም ብለው አረጋግጠዋል። እንግዲህ የትግራይ ሕዝብ በወያኔወች ዘንድ ይህን ያህል የሚፈራ ከሆነ፣

6.1 መለስን ለማውረድ የትግራይ ሕዝብ እንጅ የኢትዮጵያ ሕዝብ ኃይልና አቅም እንደሌለው ሆኖ በወያኔ አባሎች ዘንድ መታየቱ ጠልቶ ፊቱን ሲያዞርም ሆነ ሰርጅቶ ሲጥል ወድቀው ከተንኮታኮቱ በኋላ እንጅ እስከሚወድቁ ድረስ በውል ለይቶ ማወቅ የማይቻለውን የኢትዮጵያን ሕዝብ የልብ ሽፍትነትና የትግል ታሪክ ገባ ብሎ ካለማወቅ የመጣ **የመንደር ተዛነብ የኃረደው የድኹሮች** አስተሳሰብ ስለሆነ ባያስደንቅም ያባባሉን ዝቅጠት ጊዜ ለሚገልጠው ፍርድ ትቶ፣ የትግራይ ሕዝብ ግን በእንሱ ዘንድ ይህን ያህል የሚፈራ ሆኖ ሳለ የሚያደርጉትን ሁሉ ዝም ብሎ ያያቸው በጅምራቸው እንዲቀጥሉ ፈልጎ ያደረገው መሆኑን የሚያረጋግጥ በቂ መረጃ ነው። ይህ ደግሞ በኢትዮጵያ ሕዝብ ዘንድ ያሳደረውን ከፍተኛ ቅሬታና ትዝብት ትክክለኛነት የሚያረጋግጥ ይሆናል።

6.2. የትግራይ ሕዝብ በወያኔወች ዘንድ የሚፈራ መሆኑ ለአካባቢው ሰወች ቀርቶ ለሁላችንም ግልጽ ሆኖዋል። ታዲያ ከሌላው በባሰ ታፍኖዋል የሚባለው ከምኑ ላይ ነው? እንዲያውም የአንድ አካባቢ ሕዝብ የወረዳ (የዞን) አስተዳደር ጽ/ቤት ስለራቀብን ክልላችን ወደሚቀርበን አካባቢ ይለወጥልን ብሎ እስከ ወያኔወች ማእከላዊ አመራር ማመልከት እንደቻለ የብዙሀን መገናኛወች በዜና መልክ አቅርበውት አዳምጫለሁ። ለአቢቱታ አዲስ አበባ ድረስ ሄደው የነበሩ የጎጃም አርሶ አደሮችና ለዘመናት ከኖርንበት ባድማችን ተነቅለን እትብታችን የተቀበረበት ጓሮአችን እንዴት ለታሪካዊ ጠላታችን ይሰጣል ብለው የጠየቁ የጎንደር አርሶ አድሮች ግን ሰው ለመግደል ሰልጥኖ ሰው በመግደል በደለበው የአጋዚ ጦር የተካሄደባቸውን ጭፍጨፋ አፈራራጅ ጊዜ ፍርድ ይስጥበት ብየ አልፌዋለሁ።

6.3.የአረና ትግራይ አመራር በመቀሌ ከተማ በቅርቡ ደማቅ ስብሰባ አካሂዶ ነበር። በዚያን ወቅት ከስብስባው ተካፋዮች አንዳንዶቹ ከስብሰባው መሪወች አመለካከት ለውጥ ጋር በተገናኘ ውርክብ እንደነበር ከመነገሩ በስተቀር በወያኔ ሹሞች በኩል ግን አንዳችም ተጽእኖ አልነበረባቸውም። አንድነት የፍትህና የዴሞክራሲ ፓርቲ አመራር አባሎች ግን የጀግናዋን መሪያቸውን ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳን መታየሰር በመቃወም ሰላማዊ ሰልፍ ለማድረግ ሕጋዊ ጥያቄ አቅርበው አልተፈቀደላቸውም። መኢአድ በየቦታው የከፈታቸውን ቢሮዎች እንዲዘጋና የሰቀላቸውን የኢትዮጵያ ሰደቅ ዓላማ እንዲያወርድ በአመራር አባላቱ ላይ እየደረሰ ያለው እስራትና እንግልትም ቀላል አይደለም። እነዚህ ሁሉ ተዳምረው የሚያረጋግጡት አንደ ሐቅ ቢኖር አለን የሚሉት ሕገ-መንግሥት እነሱ ብቻ አንብበው ለእነሱ ብቻ በሚስማማቸው አባባል የሚተረጉሙት እንደ አጋዚ ጦር ግዳጅ የተሰጠው ሌላው የመግደያ መሳሪያ እንጅ በሕግነቱ ሚዛን ኑሮት ሁሉንም በእኩልነት የሚያይ አለመሆኑን ነው።

7. ኢፈርት በትግራይ ስሙ የገነነ የልማትና የአገልግሎት ድርጅት ሆኖ የሚታይ ነው። ሐቁ ግን የኢትዮጵያን ሕዝብ እንደ አጋዚ ጦር በኢኮኖሚና ማህበራዊ አገልግሎት መስክ እያራቆተ በመሄድ እርቃኑን ለማስቀረትና በቁሙ እንዲደቅ ለማድረግ ታቅዶ የዘመተ ሌላው የወያኔወች የመግደያ መሳሪያ ነው። ኢፈርት ብዙ ድርጅቶችን አጠቃሎ በመያዝ ልዩ ልዩ የግንባታም ሆነ የልማት ሥራወችን እንዳካሄደ በሰፊው ይነገርለታል። ነገር ግን ሲጀምር የራሱ ሆነ መነሻ ጥሪት ኖሮትና በራሱ ጥረት ትርፋማ ሆኖ ሳይሆን ወያኔወች በሰጡት ሕጋዊ ሺፋን እየተጠቀመ፣

- የአገሪቱን ብሔራዊ የመጠባበቂያ ገንዘብ (ወርቅን በባሊስትራ ከመለወጥ ጀምሮ) ሌሎችንም ጠቃሚ ቅርሶችና (ጽላት ሳይቀር) ሐብቶች ሁሉ እየቀሰጠና እየዘረፈ የሚያጓጉዝ፣
- ከኢትዮጵያ ባንኮች ተበድሮ የወሰደውን መጠኑ ያልታወቀ ከፍተኛ ገንዘብ የማይከፍል፣
- የገቢ ማግኛ ምንጭ የሆኑትን መ/ቤቶችና የሥራ መስኮች በሞኖፖል ይዞ እንደፈለገው የሚያደርግ፣
- ለትግራይ ሪፐብሊክ ግንምባታ ይጠቅማል ብሎ እስከ አመነበት ድረስ ያለምንም ሐፍረትና ይሉኝታ ከተተከለበት እየነቀለ፣ ከለሙበት እየመነጠረና ከተቀመጡበት እየቀሰጠ የሚያጓጉዝ የወንጀለኞች ወንጀል ማስፈጸሚያ መሳሪያ ነው።



Document Produced by deskPDF Unregistered :: http://www.docudesk.com

የትግራይ ሕዝብ ይሁንታ የተባለለትን ዝምታን መርጧል የሚያሰኘውም በእነዚህ ሁሉ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጠቀሜታወች ተጠቃሚ ስለሆነ እንጅ በሌላው ላይ እየተካሄደ ካለው ግፍና በደል አኳያ የሚታይ አንዳችም ተጽእኖ ኑሮበት አይደለም። ከእንደዚህ ያለው አሳማኝ ያልሆነ ምክንያት ይልቅ የትግራይ ሕዝብ በውል ማወቅ ያለበት በአሁኑ ወቅት በልማትና ግንባታ ሺፋን ተከልሎ በእሱ ስም በመካሄድ ላይ ያለውን ይፋ ዘረፋና ድብቅ ሌብነት ጭምር ነው። ምክንያቱም ልጆቹ የሚፈጽሙት የግፍ ሥራና ዘረፋ ሁሉ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ እሱን የሚመለከቱ በመሆናቸው ነው። ታሪክ እራሱን ይደግማል እንዲሉ በገሐድ ሲካሄ የኖረውን ድርጊት አብሮ ለማገናዘብ ያህል፣ ምዕራባውያን ቅኝ ገዥወች ገንነው በነበሩበት ዘመን በቅኝ ግዛት የወረሩዋቸውን አገሮች ሕዝብ በአውሮፕላን የመርዝ ጋዝ እየበተኑ ሲያቃጥሉ፣ በመትረጌስ እየቆሉ ሲፈጁና በመርከብ እያጓጓዙ ወስደው እንደ እቃ ገብያ ላይ አሰልፈው ሲሸጡ አንድ ቀን በሐላፊነት ያስጠይቀን ይሆን? የሚል ስጋት አልነበረባቸውም። ይኸውና ዛሬ ያ ሁሉ እልቂትና ግፍ ከተፈጸመ ከብዙ ዓመታት በኋላ በግፍ የፈጁት ሕዝብ የደም እዳ፣ የዘረፉት ንብረትና የወረሩዋቸው አገሮች የሞራል ካሳ እንዲከፍሉ ከተገደዱበት ዘመን ላይ ደርሰው እያየን ነው። የትግራይ ሕዝብም ከእንደዚህ ያለው አይቀሬ ባለብዙ መልክ እዳ አስቀድሞ አለመማር ደካማነት እንጅ ልዩ ፍጡርነትና የላቀ ጀግንነት አይመስለኝም። ወያኔወች ገነባንለት የሚሉት ልማትም ቢሆን እነሱ መግዛት የማይችሉበት ቀን ሲደርስ እንደ እቅዳቸው አንቀጽ 39ን አፈንድተው ወደ ምሺጋቸው ተጠቃለው ሲመለሱ አጨብጭቦ በመቀበል አደላድሎ እንዲያኖራቸው አቅደው ያደረጉት ነው። ነገር ግን ፣

1. *ፈንጅ ሲፈነዳ ወደ አራቱም አቅጣጫ የመፈነጣጠር ጸባይ ስለአለው* ***በኢትዮጵያ ላይ የተወረወረው ፈንጅ ትግራይን ለይቶ ይተዋታል ማለት ፀሐይን ጋርደን እናስቀራለን እንደማለት የሚቆጠር ስለሆነ*** በእነሱም ላይ የሚወርደውን አደጋ አብረው ያገናዘቡት አይመስሉም:: ሌላው ቢቀር ነጻ አውጭወቹ ለኤርትራ ሕዝብ አስገኘንለት ከሚሉት ነጻነት ይልቅ ነጻነት የሚለውን ቃል እንኳ እስከመጨረሻው ድረስ እንዲረግም ከሚያደርገው ምድራዊ የሲኦል ኑሮ ልምድ መቅሰም ተገቢ ይመስለኛል።

2. እናት አገሩን አጥፍተው የሄዱትን ልጆቹን በጠላትነት አይቶ ይበቀላቸዋል ወይስ የገዳይነት የአንበሳ ጎፈር አልብሶ "ጅጋኑ ጅጋኑ" እያለ በመጨፈር ጀግንነታቸውን ያደምቅላቸዋል ለሚለው ጥያቄም መልሱ የሚጠበቀው ከራሱ ከትግራይ ሕዝብ ነው። በአጠቃላይ እነዚህ ሁሉ በተቀነባበረ መልክ እየተካሄዱ በትግራይ ሕዝብ ዘንድ ጠቃሚና ዘላቂ መስለው እንዲታዩት፣ በኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነቱ ላይ የነበረው እምነትና ፍቅር ግን ፍጹም እየተዳከመ ሄዶ ጨርሶ እንዲከስም ለማድረግ የዛሬውን ብቻ እንጅ የትላንቱ ነገ ሊሆን ከሚችለው ጋር አብረው ማየት በማይችሉ ባለብዙ መልክ እዳ አሸካሚ በሆኑ ልጆቹ በመከሄድ ላይ ያሉ ዘመቻወች ናቸው። ሌላው ቀርቶ እንደሌሎቹ ስለታፈነ ነው የሚሉት ወገኖች እንኳ የእናት አገሩን ጥፋትና የወገኑን እልቂት በዝምታ እንዲያየውና እንደ ታሪካዊ ነበርነቱ ግዴታውን አብሮ እንዳይወጣ የሚያደርግ ሌላው ስንኩል መሰንከያ እንጅ ይጠቅሙኛል ብሎ ወዶ ከተቀበላቸው ኢኮኖሚያዊና ማሕበራዊ አገልግሎት ተጠቃሚነት ውጭ ስለመታፈኑ ትክክለኛ ማረጋገጫ ሊሆኑ የሚችሉ በቂ መረጃወች ያሏቸው አይመስለኝም።

እኔ ግን እነዚህን ሁሉ የተወሳሰበ ባህሪይና ጠጣር ትርጉም ያለባቸውን ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ማሕበራዊና ወታደራዊ ድርጊቶች ለማመላከት የሞከርኩት ለትግራይ ሕዝብ ለምን ተደረገለት የሚል ቅሬታ ኑሮኝ አይደለም። እንዲያውም የአገሪቱ የማድርግ አቅም የሚፈቅድ ቢሆን ኖሮ ከዚህም የበለጠ ቢደረግለት በእጅጉ ደስ በአለኝ ነበር። ነገር ግን ይካሄዳል የሚባለው ግንባታ ሚዛናዊ ሳይሆን የሌላውን መገልገያ እየነቀሉ፣ ከሚጠቀምበት ማእዱ ላይ እያፈናቀሉና የእድገት እድሉን ከማቀጨጭም አልፈው ጨርሰው እያጨለሙ፣ በጠቀምንህ ሺፍን ጉዳትን፣ በአለማንልህ ሺፋን ድህነትን፣ በአስከበርንህ ስምና ሺፋን ምንጊዜም የማይጠፋ ቂምና በቀልን፣ መናቅንና መዋረድን ሊያስከትሉ ለሚችሉ ችግሮች የትግራይ ሕዝብ መዳረግ የለበትም የሚል እምነት ስለአለኝ ብቻ ነው።

***መ. <u>ለአጠቃላይ ችግሩ መባባስ ከፍተኛ አስተዋጸኦ ያደረጉ ቡድኖች (ግለሰቦች)</u>፣***

ቀደም ሲል እንደ ገለጽኩት የትግራይ ሕዝብ እራሱ አይናገር እንጅ በእሱ ስም እየተናገሩ እነዚህን ሁሉ ችግሮች የሚያስተባብሉለት ብዙ ተናጋሪ ግለሰቦችና ቡድኖች አሉት። እነዚያ ሁሉ የትግራይ ሕዝብ ነጻ አውጭ ድርጅት አባሎች ናቸው ባይባልም አንድ አድርጎ አሰልፎ አንድ ቋንቋ እንዲናገሩ የሚያደረጋቸው የቋንቋው ባለሃብቶች በመሆናቸው ሳይሆን የወያኔ መሪወች ያመጡት መዘዘ ብዙ ችግር ውሎ አድሮ ለትግራይ ሕዝብ በጥቅምም ሆነ በጣዕም የማይበጀው መሆኑን ጠንቅቀው ስለሚያውቁ ነው። የኢትዮጵያዊነታቸውን ክብር ሺጠው የበሉትና ማተባቸውን ቆርጠው የጣሉት ከሀዲወች አቋም ይህን ያህል የሚያስደንቅና የሚያስደነግጥ ባይሆንም በኢትዮጵያዊነታቸው ከኢትዮጵያዊነታቸው ጋር ያሉትም



Document Produced by deskPDF Unregistered :: http://www.docudesk.com

ቢሆኑ ስጋታቸውን በሩቁ ለመከላከል የሚፈልጉት እሱም አብሮ እንደ ተቸገረ አድርገው በማቅረብ እንጅ በጋራ ወደሚያገናኘው የመፍትሂ ጎዳና በማምጣት አይደለም። ይህን የሚያደርጉት ደግሞ የችግሩ መፍቻ ውል ጠፍቶባቸው ሳይሆን ወደፊት የሚመጣው ለውጥ እንዳሁኑ በብዙ መልኩ ለእኛም ሆነ ለእሱ አይመቸንም የሚል ስጋት ስለአለባቸው ይምስለኛል። ስለዚህ የተፈረደባት ኢትዮጵያ ጠፋችም ኖረችም በአሁኑ ወቅት በመካሄድ ላይ ያለው እንዳለ እንዲቀጥል ይፈልጋሉ። እንዲህ ያለው አመለካከት ደግሞ የትግራይን ሕዝብ እንጠቅመዋለን ብለው ችግሩን የበለጠ ከማወሳሰብና ምርጫውን ከማሳጣት በአለፈ ሁሉም ሊቀበለው ከሚችል የመፍትሔ መደምደሚያ ላይ የሚያደርስ አይደለም። የሁሉን ባይቻልም የአንዳንዶቹን ቡድኖች ስልታዊ አቀራረብ ለማገናዘቢያ ያህል ጠቅሻለሁ።

## መ.1 <u>የሕዝባዊ ወያኔ ሐርነት ትግራይ አባሎችና በጥቅም የደለቡ ደጋፊዎች፣</u>

በመጀመሪያ የዋነኛውን ኃይል ስብስብ እምነትና አቋም እንመልከት። በዚህ ስብስብ ውስጥ የሚገኙት ግለሰቦች አገር በማጥፋት ክህደት የታወሩ፣ ከራስ ጸጉራቸው እስከ እግር ጥፍራቸው በንጹሀን ደም የተነከሩና (የተበከሉ) እድሜ ሰጥቷቸው 180 ዓመት ቢሠሩ እንኳ ሊያገኙ የማይችሉትን ሐብትና ንብረት በ18 ዓመት አግኝተው የደለቡ ስለሆኑ ለትግራይ ሕዝብ የዘለቄታ መፍትሄውን ነግረው መምጣቱ ከማይቀር የታሪክና የትውልድ እዳ ተጠያቂነት ያድኑታል ብሎ መጠበቅ በሳጥናኤል አንደበት መንፈስ ቅዱስ ይሰበካል ብሎ እንደማመን የሚቆጠር ነው። እንዲያውም የእነሱን የክህደት ሐጢአትና የግፍ ወንጀል በእሱም ላይ ለማራገፍ ስለፈለጉ ሕዝቡ የድርጅቱ ድርጅቱም የሕዝቡ ነው ብለው የደመደሙ ናቸው። ይህም ማለት የወያኔ ጌቶች በአሰለጠኑት ሕዝብ ጨራሽ ጦር እየታገዙ በአገሪቱ ብሔራዊ አንድነትና በሕዝቧ ህይወት፣ ሐብትና ንብረት ላይ ሲያደርሱ የኖሩት ማናጋት፣ እልቂትና ውድመት ሁሉ የትግራይን ሕዝብ ሙሉ ድጋፍ አግኝቶ ሲካሄድ የኖረ ነው ማለታቸው ነው። እነ ዶክ/ር ኪሮስ ስልጣን ደጋግመው ሲያረጋገጡልን የኖሩት ይህንኑ ነው። ይህ ቡድን የትግራይን ሕዝብ ምሽግ አድርጎ እየተከላከለ ሕይወቱን ከማራዘምና በዘረፋ ያካበተውን ንብረት ከመከላከል ባለፈ ምርጫ ስለሌለው ይህን ቢያደርግ አያስደንቅም። የዚህ ቡድን አሰላለፍ በሁለት የተከፈለ ሲሆን የአንደኛው ቡድን አባሎች በአገር ቤት እንደተባይ በሕዝቡ ውስጥ ተሰግስገው መቅመሻና መላወሻ በማሳጣት የሚያምሱት ናቸው። የሁለተኛው ቡድን አባሎች ደግሞ በውጭ አገር ሆነው መርዘኛ ምላሳቸውን እየዘረጉ የሚዋጉ ባለታርጋ ወያኔወች ናቸው። በዚህ ስብስብ ውስጥ የተለያዩ ባለሞያወች ስለአሉበት በየልምድና ችሎታቸው ሥራ ተከፋፍለው እውቀታቸውን፣ ገንዘባቸውንና (ከአገሪቱ ካዝና እየተዘረፈ የሚሰጣቸውን ማለት ነው) ሙሉ ጊዜያቸውን ወዘተ አቀናጅተው በመጠቀም ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን ለማጥፋት ለሚያካሂዱት ዘመቻ የሚያውሉ ናቸው። የዚህ ስብስብ አባሎች እንደ ግንባር ቀደም መሪወቻቸው በብሔራዊ ደረጃ በሚካሄደው ይፋዊ ዘረፋ ሙሉ ተጠቃሚ በመሆናቸው ከሌሎች ኢትዮጵያውያን ጋር የሚያገናኝ እምነትም ሆነ አቀራርቦ የሚያወያይ የጋራ መድረክ ፈጽሞ የላቸውም። እንዲያውም የሚኖሩባቸው አካባቢወች አልፈቅድላቸው እያለ እንጅ እንደእነሱ በውጭ የሚኖሩት ኢትዮጵያውያን በእናት አገራቸውና በወገናቸው ላይ የሚካሄደውን የተቀናጀ ርብርቦሽ በመቃወም ሰላማዊ ሠልፍ በወጡ ቁጥር እንቅፋት ለመፍጠር የማያደርጉት ጥረት የለም። ይኽ ስብስብ በተለይ ባለው የገንዘብ ኃይል በትግራይ ሕዝብ ዘንድ የሚመለክና የሚሰጠው መመሪያም ይሁን ሐሳብ ተቀባይነት ያለው ነው። እንግዲህ ይኽ ሁሉ ለትግራይ ሕዝብ ከአቅሙ በላይ ስለሆነበት ነው የሚያሰኝ ሳይሆን እንዲያውም ይጠቅመኛል ብሎ አምኖበት የተቀበለው ለመሆኑ ማረጋገጫ ነው።

በእምነትም ሆነ በድርጊት ብዙም ባይለዩም በሁለት ስለት ማህል ቁመው የሚታዩት አስቀድመው በማህል አገር ይኖሩ የነመበሩ የወያኔ ቋሚ አባሎችና ደጋፊወች ናቸው። የዚህ ስብስብ አባሎች በብሔረሰባቸው የዚያው አካባቢ ሰወች ቢሆኑም ማህል አገር ተወልደው ያደጉ፤ ከሌላው ጋር ተዋልደው የተዛመዱና ለወግ ለማዕረግ የበቁ፤ ወይም ከዚያ ቢወለዱም ለትምህርትም ይሁን ለሌላ ማህበራዊ አገልግሎት ወደማህል አገር መጥተው የተደላደለ ኑሮ በመኖር ላይ የነበሩ ናቸው። እነዚህ ስብጥሮች በአሁኑ ወቅት በአንድ በኩል ከአብሮነት ጋር አብሮ ከኖረው ትግራይነት ይልቅ ወያኔ ፈጠር ትግራይነቱ ልቆና ደምቆ ስለሚታያቸው አብረው ማጀብጀቡን ቀጥለውበታል። ያልጠበቁት ሐብትና ንብረትም አግኝተውበት ሊሆን ይችላል። እንዲህም ስለሆኑ ቢያንስ በየሚኖሩበት ቀበሌ ጆሮዋቸውን ላክ እያደረጉ በማዳመጥ እገሌና እገሊት እኮ እንዲህ ናቸው እያሉ ስውር ግዴታቸውን የሚወጡና በትግራይ ልማት ስም በሚካሄዱ ስብሰባወች ላይ እየተገኙ ካካበቱት ገንዘብ ላይ እየዘገኑ የሚያበረክቱ ናቸው። በሌላ በኩል ግን በዚያ በአብሮነት ዘመን ያፈሩት ሐብትና ንብረት፤ በወንድማማችነትና በእህትማማችነት መንፈስ እየተሳሰቡ የገነቡት ፍቅር፣ ክፉና በጎውን እየተጋሩ ያሳለፉት መልካም ዘመን ወዘተ በአልጠበቁት ሁኔታ እንደ ሸክላ እቃ ወድቆ በመንኮታኮቱ እንባቸውን ሲያፈሱ በግልጽ የማያሳዩት ሐዘን ሳይሰማቸው እንደማይቀር ግምት ማሳደር ይቻላል። ነገር



Document Produced by deskPDF Unregistered :: http://www.docudesk.com

ግን የሚመጣው ሕዝብ ጠቀም ለውጥ አያቅፈንም ከሚል ስጋታቸው በተጨማሪ አብሮ ሊመጣ ይችላል ብለው የሚገምቱት ችግር ተንቀሳቃሽ ፊልም ሁኖ ህሊናቸውን እያስነበበው ስለሚያልፍ ከሁለቱ አንዱን ለመምረጥ ተቸግረው ስለሚዋልሉ ኑሮዋቸው በከፍተኛ ስጋት የታጀበ ነው። ይኸም ሆኖ ወያኔወችን እየደገፉ መቀጠሉን መርጠው አብረው እየተጓዙ ናቸው። ያ መምጣቱ የማይቀረው ሕዝብ ጠቀም መንግሥት ግን እንደ እነሱ ጌቶች ቂም በቀል አርግዞና የሕገ-መንግሥቱን የማእዘን ድንጋይ የመበቀያ መሳሪያ አድርጎ በጥፋት ላይ ጥፋት የሚያውጅ ሳይሆን እስከ አሁን የተጠፋፋነው ስለሚበቃ ሁላችንም እጅ ለእጅ ተያይዘን በአዲስ የተሐድሶ ጎዳና እንጓዝ የሚል ደወል እያሰማ የሚመጣ መሆኑ ግን አልታያቸውም። **ለእኔ እንደሚገባኝ ከዚህ ይልቅ ለእነሱ ከባድ ፈተና የሚሆንባቸው የተዘረጋላቸውን የሰላም እጅ የሚጨብጡበት ንጹህ እጅና የሚቀበሉበት ጤናማ አዕምሮ አጥተው አፍረው እንዳይመለሱ ነው።** በእርግጥ ችግራቸውን ገልጽኩ እንጅ  አብሮነትን እንደማይመርጡት ይገባኛል። ምክንያቱም በጠላትነት የተፈረጀ በመሆኑ፣ አላቂና ደቃቂ ከሆነ ጊዜያዊ ጥቅም ጋር ስለሚያጋጭና መንደርተኝነት ካወረውና የቋንቋ ማገር ካውገረገረው ጠባብ ጉርጅ (ጉሮኖ) ውስጥ ወጥቶ በሰፊ አድማስ ለማየት ማንነትን የሚጠይቅ ከባድ ፈተና ወዘተ በመሆኑ ነው።

### *መ.2. <u>የአዲስ ምልስ ኢትዮጵያውያን አዲሱ ስልት፣</u>*

ሌላው በአሁኑ ወቅት በመደመጥ ላይ ያለው አፍላ ወሬ የትግራይ ሕዝብ ነፃ አውጭ ድርጅት መስራች አባላትና ከፍተኛ ባለስልጣን የነበሩ ከአለቃቸው መለስ ዜናዊ ጋር በግል ጥቅም ተጋጭተው ከድርጅቱ ስለወጡ አዳምጡን ብለው የጀመሩት የአዲስ ምልስ ኢትዮጵያውን አዲስ ስልታዊ አቀራረብ ነው። ይህን ቃል እነሱ እንደማይወዱልኝ ቢገባኝም የማይወደድ የክህደት ዓላማቸው ዝቅጠትና የእኩይ ግብራቸው ምስክርነት ውጤት ስለሆነ እየመረራቸውም ቢሆን መቀበል ይኖርባቸዋል። በመሠረቱ የሰው ልጅ ከስህተቱ አይማርም፣ በጥፋቱም አይጸጸትም የሚል ጭፍን አመለካከት የለኝም። የመማሩም ሆነ የመጸጸቱ ሁነኛ ማረጋገጫ የሚሆነው ግን የተለየ ደስታና ጥቅም እናገኝበታለን ብለው የፈጸሙት ጥፋትና በቀላሉ እያዩ የቀጠፉት ህይወት ከአንጀት አሳዝኗቸው ሲያስለቅሳቸው፣ እየመረራቸው ውጠው ሲያስምጣቸውና እየከበዳቸው ተሸክመው ሲያጎብጣቸው ነው። በባህላችን ይቅር ለእግዚአብሔር ተባብሎ ሰላም ማውረድ ሲፈለግ በደለኛው ድንጋይ በትከሻው ተሸክሞ ተብዳዩን ተጎንብሶ (ተንበርክኮ) ይቅርታ የሚጠይቀው መጸጸቱን ለመግለጽ እንጅ ድንጋይ መሸከምን ወዶ አይደለም። አለያማ በመትረጌስ መቁላቱና በእስር ቤት አጉሮ ማሰቃየቱ አልበቃ ያለ ይመስል፣ የሰውን ልጅ ያህል ታላቅ ፍጡር እንደጎመን እየቀረደዱ ሲያርዱ፣ እንደመርግ በገደል እየወረወሩ ሲያነጎዱና በእሳት ላይ እየጣሉ ሲያነዱ የኖሩበትን በንጹሐን ደም የሰከረ ሕይዎት አቃልሎ በማየት የትላንቱ ቅሬት እንዳተበተውና የወንጀለኛነት ትምክህቱ እንዳሳበጠው የሁለት ጊዜ ተጠቃሚ ለመሆን የሚደረግ ዙሪያ ከበባና ምክንያት ድርደራ ግን ሆን ብሎ የፈጸሙትን ጥፋት ወይም ወንጀል ክብደት ለመጨመር የሚችል ትዝብት ከማትረፍ በአለፈ የሚያስገኘው ለውጥና ውጤት ይኖራል ብየ አላምንም።

ይህ ማሳሰቢያየ እንደተጠበቀ ሆኖ በግል የጥቅም ግጭት ቢሆንም ቅሉ ከመሸጉበት መንደርና ጎጆ እየወጡ ወደ ሕዝባዊው ጎራ ለመቀላቀል መጣን ያሉትና ወደፊትም የሚሉት በደፈናው ሲታይ ጠቃሚ እንጅ ጎጅ ጎን የለውም ሊባል ይችላል። በግሌም ቢሆን ከዚህ ጋር የተያያዘ ችግር የለብኝም። እንዲያውም በብዙ አጋጣሚወች እንደገልጽኩት ባሁኑ ወቅት የእናት አገር ኢትዮጵያን ብሔራዊ አንድነት ለማናጋት ተጠምዶ ጊዜ ለሚጠብቅ ፈንጅ መክኖ መቅረትና በሕዝቧ ላይ እየተካሄደ ለአለው እልቂት መወገድ አስተዋጽኦ ማድረጉ በትክክል እስከተረጋገጠ ድረስ የተለያየ እምነትና አቋም ካላቸው ኢትዮጵያውያን ቀርቶ ከሳጥናኤልም ጋር ቢሆን ግንባር ፈጥሬ ለመታገል ዝግጁ መሆኔን ደጋግሜ ገልጫለሁ። ዛሬም እንደገና አስምሬበት የማረጋግጠው ቢኖር ያነኑ ነው። እስከዚህ ድረስ አደርጋለሁ የምለው ግን እንደ እነሱ የሳጥናኤል ግበር ወራሽ ሆኘ ፍቅሩ አድሮብኝ ሳይሆን የግብር ተከታዮቹን በሚያውቅባቸው ሰይጣናዊ ተንኮሉ እየወጋ የሚጥላቸው እስከሆነ ድረስ አገሬና ወገኔ ድነው እኔ ልጎዳ የሚል ጽኑዕ ዕምነት ስለአለኝ ነው። የእነሱን ወደ ኢትዮጵያዊነታችን ተመልሰናል ባይነት አጠያያቂ የሚያደርገው ግን የአመጣጣቸው ዓላማና ግብ ያለው ተአማኒነት ወይም ኢተአማኒነት ነው። ከዚህ አንጻር በተመልሰናል ውስጥ ያልመለሱዋቸው አጠያያቂ ነገሮች እንዳሉ ለማየት አመልካች የሚሆኑ አንዳንድ ነጥቦችን ማንሳት አስፈላጊ ይመስለኛል።

- በሕዝብዊ ወያኔ ሐርነት ትግራይና በአረና ትግራይ መካከል ያለው መሠረታዊ ልዩነት ምንድነው?
- ወደኢትዮጵያዊነታችን ተመልስናል ማለትና ትላንት ለኢትዮጵያ ብሔራዊ አንድነት ማናጊያ ይሆነናል ብለው የቀመሙትን ጌዜ ጠብቆ የሚፈነዳ ፈንጅ አንቀጽ 39ን እንደያዛን መቀጠል አለብን ማለት ዛሬም ከዚያው እንዳለን ለዚይው እንደቆምን በዚያው እንቀጥላለን ለማልት ካልሆነ



Document Produced by deskPDF Unregistered :: http://www.docudesk.com

በስተቀር የበደሏቸውን አገርና ሕዝብ ለመካስ መዘጋጀታቸውን የሚያረጋግጥ ይሆናልን?

- የመንግሥትነት ሥልጣን በትጥቅ ትግል ጨብጦ (የመንግሥትነት ሥነ ባህሪይ ባይኖረውም) አገርን እንደፈለገ እየሸነሸነ የሚሸጥ፣ የሕዝብን ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብት ረግጦ ይዞ እንደፈለገ የሚፈልጥና የሚቆርጥ፣ የሰላማዊ ትግልን አማራጮች ሁሉ ገድሎ ቀብሮ እሱ ብቻ እንደ ፈለገ እየናጠጠ መኖረን የሚፈልግ ጠባብ መንደርተኛ ቡድን መኖሩን በአካል አባልነታቸው እያወቁ የትጥቅ ትግልን አማራጭነት መቃወማቸው ማነንን ጠቅሞ ማነንን ሊጎዳ ይችላል የሚል ስጋት አድሮባቸው ነው?

- አገሪቱን በመንግሥትነት ይዘው እየገዙ ለአገሪቱ ብሔራዊ አንድነትና ለሕዝቧ ሰላምና ደህንነት ሲዋደቅ የኖረውን የመከላከያ ኃይል በትነው ከትግራይ ብሔረሰብ ብቻ የተመለመለ ጦር ማደራጀት የአገር ሰወችና የሕዝብ ወገኖች የሚያደርጉት መልካም ሥራ ወይስ ባዕዳን ኃይሎች የሚያደጉት የለየለት የጠላትነት ድርጊት?

- ለዳር ድንበሯ ዘብ ቁሞ ሲዋደቅ የኖረውን ብሔራዊ የመከላከያ ኃይል ለጥፋት የዘመተ ወንጀለኛ አድርጎ በመፈረጅ በአገሪቱ አንድነትና ብሕዝቧ ማህበራዊ ደህንነት ላይ ለዘመተው ፀረ-አንድነት፣ ፀረ-ስላምና ፀረ-እኩልነት ጎጠኛ ጦር ግን ክብርና ሞገስ መስጠትና ሐውልት ማቆም ኢትዮጵያዊ ያሰኛልን?

- የወያኔ መሪወች የኢትዮጵያን የባህር በር አንፈልገውም ብለው ወደው የለቀቁና ፈርመው ያስረከቡ መሆናቸው ሚስጥሩ ይፋ ሆኗል። የዘጉትን በር የመክፈቱ ሐላፊነት የዘጉት ሆኖ ሳለ ጉዳዩን ወደ ኢትዮጵያ ሕዝብ መግፋት ለምን አስፈለገ?

- ወደ ኢትዮጵያዊነታችን ተመልሰናል ሲሉ 30 ዓመታትና ከዚያም በላይ ክፍት ሆኖ ሲጠብቃቸው የኖረና ሲመለሱ ሰተት ብለው የሚገቡበት የገብያ አዳራሽ በር አይደለም። እሱም እንኳ ቢሆን የሚዘጋበት ጊዜ አለው። ስለሆነም ተመለስን ሲሉ ኢትዮጵያን ሽምጥጠው የካዱበትንና ኢትዮጵያዊነትን አምርረው የጠሉበትን መሠረታዊ ምክንያት በግልጽ ሊያሳውቁን ይገባል። አለያ ወደካንሰርነት የተለወጠን ቁስል በፋሻ እንደመሸፈን ይቆጠራል የሚል ስጋት አለኝ። ይህም ብቻ ሳይሆን ሁሉም በእጃችን ሁሉም በደጃችን ሆኖዋል ብለው በሆይ ሆይታ እየጨፈልቋቸው ለመጡት የአቋም ጥያቄወች ከባድ እዳ አለባቸው። ለምሳሌም የኤርትራ የቅኝ ግዛት ጥያቄ፣ የኢትዮጵያ ታሪክና (የአክሱም ሐውልት፣ የ100 ዓመት ታሪክ ወዘተ) የባህር በር ጥያቄ፣ የጎንደር፣ የወሎና የአፋር አስተዳደር ክልል በወረራ መያዝና ሕዝቡን በግድ ትግሬ ካልሆናችሁ ብሎ ማሰቃየት፣ በአጠቃላይም በአገሪቱ የመከላከያ ኃይልና በሕዝቧ ማህበራዊ ደህንነት ላይ በአደረሱት ሁለንተናዊ ማናጋትና እልቂት ጥፋታቸውን አምነው በመቀበል የኢትዮጵያን ሕዝብ ምህረት መጠየቅና ካሳ የመክፈል ግዴታ ያለባቸው መሆኑን አምነው መቀበል አለባቸው።

በስጋ ቆጠራና በቆዳ ቀለም እንጅ በባህሪይ የተወለዳቸው ልጅ ባይተኩም የእምነት ማተባቸው ላልቶ፣ የሞራል ጉልበታቸው ደክሞና ምክራቸው አብሎ የማያውቀው እነዚያ ሰው ሆነው ተፈጥረው ሰው እንደሆኑ ያለፉት ትልቆቹ ሰወች ከገጠመኞቻቸው ጋር እያዛመዱ መጥነው የሚወረውሯቸው ቃሎች እንደ ጸበል እየሰረጹ የሚገቡ ትምህርት ሰጭወች ነበሩ። በአሁኑ ወቅት በአገራችን ነግሶ ከሚታየው አስተዛዛቢ ድርጊት አኳያ ሥዕላዊ መግለጫ ሊሆን የሚችለውን አንዱን ብጠቅስ “**አይመከር ምክር የለ፣ ሰው ገለን አገር ጥለን እንሰደድ ተበሎ ይመከራል**” ያሉት ነበር። ከአባባላቸው ልብ ማድረግ የሚገባን አብይ መልእት ሰውን ያህል በአርአያ ሥላሴ የተፈጠረ ታላቅ ፍጡር ገድለን መተኪያ የሌላትን አገር ጥለን እንሰደድ ብለው ለተግባራዊነቱ መዘጋጀቱ ቀርቶ መጀመሪያውኑ ሐሳቡን የሚያመነጩት እንኳ ምን ዓይነት ጤናማ አዕምሮ ያላቸው ሰወች ቢሆኑ ነው? የሚለውን ነው። የእነአቶ ስየ አብርሐምን የትላንቱን በእጅጉ ሽምጥጠው የሂዱበትን ክህደትና የዛሬውን ተመልሰናል ባይነት የማየው ከዚህ አንጻር ነው። ይኸም ሆኖ የስው ልጅ በተፈጥሮው እራስ ወዳድ በመሆኑ ከመንፈሳዊ ሕይወቱና ከሞራል ግዴታው ይልቅ ሥጋዊ ፍላጎቱ እያቸነፈውና የከፈተለትን ደካማ ጎን እርካብ አድርጎ ተሳፍሮ የሚያሰግረው እርኩስ መንፈስ እናት አገሩንና እናት አገሩ አብራ የወለደችለትን እህቶቹንና ወንድሞቹን ቀርቶ የፈጠረውን አምላክ እንኳ ሲክድ ለህሊናው ቅንጣት ታክል የማይከብደው እጅግ የብዙ ብዙ ነው።

በተለይም በኢትዮጵያ እንደ ኤድስ በሺታ ተስፋፍቶ ብዙዎችን እየበከለ የመጣው የዘመኑ የጎሳ በሺታ



Document Produced by deskPDF Unregistered :: http://www.docudesk.com

የእናት አገሩን ብሔራዊ አንድነት አናግቶ ህልውናዋን ማሳጣት፣ ሕዝቧን አቃቅሮ ደም ማቃባትና በአንድነት ጥላ ስር ተመልሶ እንዳይገናኝ ማድረግ፣ ዓለም ሲደነቅ የኖረበትንና ከእኛም አልፎ ጥቁር ሕዝቦች ሁሉ ሲመኩበት የኖሩበትን አኩሪ ታሪካችንን ተረት ተረትና የጥቂት ገዥ መደቦች ብቻ ታሪክ እንደሆነ አድርጎ ማቅለም፣ (እነዚህ ሁሉ የታሪካዊ ጠላቶቻችን እቅድ አቀፍ ሴራወች ናቸው) ወዘተ እንደ ጠቃሚ ሥራና መንፈሳዊ አገልግሎት ተቆጥረው በሰማይ መንግስተ-ሰማያት ሰተት አድርገው የሚያስገቡ (ክህደት ወደ ሲኦል እንጅ ወደገነት ባያስገባም) በምድር ደግሞ ዘውድ ቀረሽ ንግሥና አንግሠው ዓለማዊ ፍላጎቶች የተሚሉበት የተደላደለ የገነት ኑሮ ያስኖራችኋል ተብሎ የታወጀላቸው ይመስል በሰላም የሚኖረውን ሕዝብ በክሎ ጤና ለማሳጣት የሚያስችል የሴራ መርዝ የሚቀምሙት፣ መርዘኛ የማዋጊያ ምላሳቸውን የሚያሾሉትና ይሁዳዊ ቀሳጢ እጣታቸውን የሚቀስሩት ቁጥር እንዲህ ቀላል አይደለም። ነገር ግን ፈንጅ ዘመድ ስለሌለው ለሠሪውም ቢሆን አያዝንም እንደሚባለው ያ ለሌላው ማጥፊያ የቀመሙት መርዝና የቀመሩት ሴራ እነሱንም አብሮ የሚያጠፉቸው ከሆነ ትርፋችሁ ምንድነው? ብሎ ለሚጠይቃቸው ግን አጥፍቶ መጥፋት ካልሆነ በስተቀር አገር ሳይኖር መንደር፣ ሕዝብ ሳይኖር ብቻችን መኖር እንችላለን ብሎ መጀመር ቀርቶ መታሰቡ እንኳ እራሱ ያው የአእምሮ ጤና ችግር ካልሆነ በስተቀር ከቅዠትም አልፎ እብደትን በይፋ እንደማወጅ የሚቆጠር ነው።

እኔ እንደሚገባኝ አገር ቢከፋኝ ብመለስ እያሉ የሚጫወቱባት የገበጣ መጫወቻ አይደለችም። በተመቸ ጊዜ የስም ካባዋን ደራርበው ለብሰው የሚወድሱባትና የሚኮፈሱባት፣ ችግር አንገላቷት በጎረበጠች ጊዜ ደግሞ አልተመቸችንም ብለው አምርረው የሚጠሏትና ጊዜው አልፎባታል ብለው አውልቀው የሚጥሏት የዘመኑ ፋሺንም አይደለችም። ልምላሜዋ በአስጎመጀና ፍሬዋ በአንዠረገገበት ዘመን እየተሻሙ የሚለቅሚትና ተጠግተው የሚቦጠቡጧት፣ በሰው ሠራሽም ይሁን በተፈጥሮ ችግር ምክንያት ከስታና ጠውልጋ በታየችበት ዘመን ደግሞ መረረችን ብለው አልጎጥጉጠው የሚተፏትና የኔ አይደለችም ብለው የሚክዷትም አይደለችም። በመልካሙ ቀንና ዘመን በፍቅር ተወልደው በእንክብካቤ የሚያድጉባትና ለወግ ለማረግ የሚበቁባት፣ ህልውናዋን የሚፈታተን ፈታኝ ችግር በተጋረጠባትና ከተፈታታኝ ጠላቶች ጋር በተፋጠጠችበት ወቅት ደግሞ አንድም ችግርሺን አያሳየንና ጥሪሺን አያሰማን ብለው ፊታቸውን አዙረው የሚሄዱባት፣ አለያም ለባንዳነት አድረው አብረን አገዳድለን እንቅበራት፣ ወይም አርደን እንቃረጣት ተብላ የሚፈረድባት ወንጀኛ እናትም አይደለችም።

አገር ማለት ግን መተኪያ ነገርና መግለጫ ቃላት የማይገኝላት እጅግ ክቡርና በጣም ውድ የሆነች የሕዝቧ ሕይወት ናት። እጅግ ክቡርና በጣም ውድ የሚያሰኛት ደግሞ የውድ ነገሮች (አልምዝና እንቁ) ወዘተ መገኛ ስለሆነች ሳይሆን እሷንና ከእሷ የሚገኙትን ፍጥረታት ሁሉ እንዲገዛ ከፈጠረው አምላክ ሥልጣን የተሰጠው ታላቅ ፍጡር (የሰው ልጅ) ዘላለማዊ መኖሪያና ቋሚ ሐብቱ በመሆኗ ነው። በአጭር አባባል **አገር ማለት የአገሪቱ ሕዝብ ዘላለማዊ የሁለመናው ሁለመና ማለት ናት።** ይኸም ማለት የሚደሰቱባት ብቻም ሳትሆን የሚከፉባት፣ የሚኖሩባት ብቻም ሳትሆን የማይኖር ስጋን እየገበሩ ሕያው ሆኖ የሚኖር ስምና ታሪክን በአደራ የሚያስቀምጡባት የማታስስ መንበርም ናት። ይህን ሁሉ እያወቁ በእናት አገር ላይ ክህደት መፈጸምና በሕዝቧ ላይ ጥፋት ማወጅ ግን በመንፈሳዊ ሕግ ምህረት የሌለው ከባድ ሐጢአት፣ በዓለማዊ ሕግ ደግም አመክሮ የማያሰጥ ከባድ ወንጀል ነው።

**“ካላዋጣ ይውጣ”** በሚል ርዕስ አሜሪካ ውስጥ የተዘጋጀውን ባለብዙ ገጸ-ባህርይ ድራማ ደጋግሜ ተመልክቸዋለሁ። ድራማው ባለፉት ዓመታት ለአገርና ለሕዝብ መልካም አስተዳደር እናመጣለን በሚል ሽፋን መሆን ቀርቶ መምሰል እንኳ በቅጡ አልሆንላቸው ብሎ ሲንከላወሱ የኖሩት ግለሰቦችና ግለሰብ አቀፍ ድርጅቶች ሁሉ በየጓዳቸው ደብቀው ያኖሩትን ጉዳጉድ ሁሉ ሳይወዱ በግድ እየጎለጎለ በማውጣት እራሳቸውን እንዲያዩበት (የሚያሳይ ህሊና ካላቸው ማለት ነው) የሚያደርግ በመሆኑ ከድርሰቱ ባለቤት ጀምሮ በሞያው ለተካኑት ምርጥ ኢትዮጵያውያን ሁሉ የአለኝ አክብሮትና አድናቆት በእጅጉ ከፍተኛ ነው። አንዱን ዋነኛ መልእክት የወቅቱ መነጋገሪያ ከሆነው አፍላ ወሬ ጋር አዛምጀ ብጠቅስ፣ "**ይቅርታ መጠየቅ ገድሎ ነው፣ ይቅርታ መስጠት ደግሞ ሞቶ ነው**" ያሉትን በከፍተኛ አድናቆት አስታውሰዋለሁ። በአሁኑ ወቅት አገር አጥፊወችና ትውልድ ገዳዮች የመግባቢያ ቋንቋ አድርገው ሲናገሩት የሚደመጠው ይህንኑ ነው። እውን ጌታ ለእነ ታምራት ላይኔ ምህረት አድርጎላቸው ይሆን? ይህ ከሆነ የሕያዋን አምላክ መሆኑን ትቶ የሙታን አምላክ ሆኗል ማለት ነው፣ የእነ አቶ ስየም ድርጊት መታየት ያለበት በዚህ አባባል ስር ነው፣ ያውም የገደልናቸው እንደ ተገደሉ ይቅሩ አሉ እንጅ ባያድኗቸውም እንኳ ይቅርታ እንጠይቃቸው አላሉም።

በአንድ ወቅት የሚያዝን አንጀቱንና አርቆ የሚያስብ ሕሊናውን ወደስሜኑ የአገራችን ክፍል መለስ አድርጎ



Document Produced by deskPDF Unregistered :: http://www.docudesk.com

በእዝነ-ሕሊናው ቢ.ቃኝ በየበረሀውና በየጋራና ሸንተረሩ እየተናነቁ የወደቁት ጀግኖቻችን አጽም እንደፍልጥ ተከምሮና ደማቸው ደግሞ እንደሐይቅ አቁቶ ሳይታየው አይቀርም ማለቴን አስታውሳለሁ። አዎ! ይኽ አባባል የቃላት ቀመር ጉዳይ ሳይሆን የእነዚያ ለእናት አገራቸው አንድነት መጠበቅና ለወገናቸው ክብር ሲሉ ውጊያ በተካሄደባቸው ጎራወች ሁሉ ረግፈው የቀሩት ጀግኖቻቸን አጽም አፍ አውጥቶ የሚናገረውና ንጹህ ቀይ ደማቸው ጽፎ የሚያስነብበው ሐቅ ነው። ያን ሁሉ መቸውንም ቢሆን መረሳት የማይችል ድርብርብና የሚዘገንን መሪር ሐዘን መለስ ብየ ለመጥቀስ የፈለግሁት እንዳለፉት ዘመናት የአገራችንን ዳር ደንበር ሊደፍሩና ነጻነታችንን ሊገፉ ባሕር ማዶ ተሻገረው ከመጡ ባዕዳን ኃይሎች ጋር በተካሄደ ጦርነት ሳይሆን ከኤርትራና ከትግራይ ሕዝብ ቢወለዱም ፊት ለፊት ዘምተው ተዋርደው ለተመለሱትና የሐፍረት ማቅ ለብሰው ለሚኖሩት ጠላቶቻችን የረጅም ጊዜ እቅድ አስፈጻሚ ሆነው በዘመቱብን ቅጥረኛ ከሐዲወች የተፈጸመ ሲያፈራርድ የሚኖር ወንጀል መሆኑን ለማመልከት ስል ነው።

በዚህም ምክንያት በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ ልጆች ያለአባት ማደግ፣ ሴቶች ደግሞ ያለባለቤት መኖር ከጀመሩ ብዙ ዓመታትን አስቆጥረዋል። ሕይወታቸውን መራራና ኑሮአቸውን ከባድ ያደረገው ደግሞ ከተሸከሙት ሐዘን ጋር ተጋግዞ የሚመጣባቸው የችግር ዓይነትና መጠን መብዛቱ ነው። በአጭሩ ግን በዚህ ቀን አቁመውና ከዚህ ወራት በኋላ አውልቀውና ፈትተው ሊጥሉት ይችላሉ ብሎ ለመናገር የማይቻል ጥቁር ልብስ ለብሰውና ጥቁር ማተብ አስረው መሪር ሐዘን እያዘኑ፣ ወርዶ የማያልቅ እንባ እያነቡና ከሕሊናቸው የማይጠፋ የልጅና የባል ሥእል እያነበቡ የሚኖሩትን ባለብዙ ጎን ሐዘንተኞች ቁጥር የወለደ አንጀትና አዙሮ ማየት የሚችል አንገት ይቁጠራቸው ከማለት በስተቀር አሐዙን በትክክል መግለጽ አይቻልም። ወያኔወች አደገኛ ቦዘኔወች ናቸው እያሉ በማሳደድ በየጎዳናው ከሚገድሏቸውና እንደቆሻሻ እየሰበሰቡ በየጉድባው ከሚጥሏቸው የአገሪቱ ዜጎች ውስጥ እነዚያ ያለአባት ያደጉና ምን እንርዳችሁ ብሎ የሚጠይቃቸው ያጡ የዚያ ጀግና ሠራዊ ልጆች መሆናቸውን በሚላወስ አንጀት የማያገናዝብ ያለ አይመስለኝም። ግፉን እጥፍ ድርብና እጅግ መራር የሚያደርገው ደግሞ የታሪክን ፍርድ የማይፈሩትና ለልጆቻቸው የማያዝኑት ወያኔወች ሕያው አድርጎ ለሚያኖር ሕዝባዊ ዓላማ ክቡር መስዋዕትነት የከፈለው ሠራዊት አጽም በየቦታው ረግፎ አፈር እንኳ የሚያለብሰው አጥቶ ፀሐይ እየመታውና አላፊ አግዳሚው እየረገጠው፣ አገር ለማጥፋት ለዘመተው ጀግና ነው ለሚሉት ጦራቸው ግን ሐውልት ማቆማቸው ነው። ይህን ሁሉ ግፍ የሚያውቀው አምላክ ምናልባት አንድ ቀን ተመልሶ የሚዋጋ እሾህና የሚቆርጥ ስለት ሳያደርገው ይቀር ይሆን?

የአቶ ስየ የመንደር ልጆችና የዓላማ አጋሮች በማያዙባቸው ነፃ የብዙሐን መገናኛወች የሰጠውን መግለጫና ቃለ-መጠይቅ ከሞላ ጎደል አዳምጫለሁ። ስለኢትዮጵያ የባህር በር አልባነት ተጠይቆ የሰጠውን መልስ ቃል በቃል ለማስቀመጥ ባልችልም ጥቅል ሐሳቡ ግን በሰላማዊና ዲፕሎማሲያዊ መንገድ ማግኘት ትችላለች የማለት ዓይነት ነው። ይኸም ማለት ትላንት እንደመቃብር አፈር አጣድፈው ሲዘጉትና ተመካክረው በፊርማቸው ሲያጸድቁት ያልሰጡትን የማመልከት እድል ዛሬ ሊጠቀምበት ይችላል ሲል ምን ማለቱ ነው? እሱ ይህን ይበል እንጅ ጓደኛው አቶ ስብሐት ነጋ ደግም በኤርትራ ላይ የመጣ ወዮለት እያለ መዛቱን እንደቀጠለ ነው። ስለዚህ ተመካክረው የዘጉትን የባሕር በር ተመካክረውም ይሁን ተፎካክረው መክፈት ያለባቸው እንሱ እንጅ የኢትዮጵያ ሕዝብ ለአቤቱታም ይሁን ለሁለተኛ ዙር ጦርነት የሚጋበዝበት ምክንያት የለም። ይኸም ሲባል የኢትዮጵያ ሕዝብ በራሱ እቅድ ላይ ተመስርቶ ማድረግ ያለበትን አያደርግም ማለት አይደለም። እነሱ ግን "ሲታረቁ ከሆድ፣ ሲታጠቡ እስከ ክንድ" እንደሚባለው ወደ ኢትዮጵያዊነታቸው የመመለሳቸው ማረጋገጫ የሚሆነው እንደዚህ ያለውን በተጨባጭ የሚታይ እርምጃ ሲወስዱ እንጅ "ውሻ በአጥንት ይጣላል በጅብ ይገጥማል" እንደሚባለው ተጣላን ብለው በፈጥሩት አዲስ የመታገያ ስልት አረና ትግራይ በሚባል አስታራቂ ሺማግሌ (ያውም እንደ እነ ፕሮ/ር ኤፍሬም የውሻ ሺማግሌ ዓይነት ያልሆነ) ከለላ ለውሎ -ገብ የወጣ ተመላሽ ኢትዮጵያዊ መስሎ ብቅ ማለት አይደለም።

አቶ ስየ ትላንት ከፈልግንም ጦርነት መፍጠር እንችላለን እያለ በትቢት እንዳልተናገረ ሁሉ ዛሬ ደግም በአዲሱ የአቀራረብ ስልት የትጥቅ ትግል ምን ሲል ተወስቶ የሚል አቋም ይዞ ነው። ይኸም ወደ ኢትዮጵያዊነቴ ተመልሻለሁ ባይነቱን በጥያቄ ውስጥ እንዲወድቅ አድርጎታል። ምክንያቱም እሱን ጨምሮ ጓደኞቹ ወንድማዊ እርቅንና ሰላማዊ ትግልን ገድለው የቀበሩና ተመልሶ እንዳያንሰራራ እንኳ እድሉን ሁሉ እየዘጉ የመጡ መሆናቸውን ጠንቅቆ እያወቀ ሌላ የመፍትሔ አማራጭ መፈለግ የለበትም ማለት የአለው እንዲቀጥል የመፈለግ ጉዳይ እንጅ የሰላም ጥማት አይመስለኝም። ሌላው ቢቀር ከታሰረበት እንዲፈታ የፈረደችለት ጀግናዋ የሕግ ባለሞያ ብርቱካን ሚደቅሳ ዛሬ ግን ጨለማ ክፍል ውስጥ ብቻዋን ተዘግታ እንድትሰቃይ የተደረገው ጦርነት አውጃ ሳይሆን በሰላም እታገላለሁ ብላ መዝመቷ ወንጀል ሆኖ ስልተገኘባት ነው። ቴዮድሮስ ካሳሁን ደግሞ እስር ቤት ተወርውሮ ስድስት ዓመት እስራትና 18000 ብር ቅጣት



Document Produced by deskPDF Unregistered :: http://www.docudesk.com

የተፈረደበት እውን ሰው ገድሎ ሳይሆን በዜግነቱ ለእናት አገሩ ፍቅሩን በመግለጹ ብቻ ነው። በኢትዮጵያ በመኪና ሰው ገጭቶ መግደል ይህን ያህል የሚያስቀጣ ወጀል ከሆነ ሰው በመግደል የሰለጠኑት ዋነኛወቹ ገዳዮችና አስገዳዮች ምን ሊባሉ እንደሚችሉና ምን ዓይነት ፍርድ እንደሚጠብቃቸው ጊዜ ይግለጠው።

አቶ ስየ ቬኦኤ የአማርኛው አገልግሎት አቅርቦለት ከነበረው መጠይቅ አንዱ ስለይቅርታ መጠየቅ ነበር። ከወያኔ መሪወች እንደበት ሸፍጥ እንጅ የእውነት ቃል ያመልጣቸዋል ብየ ባልጠብቅም የሰጠው መልስ ግን ሁሉም ጥፋተኛ ስለሆነ የእኔም መታየት ያለበት ከዚህ አኳያ ነው የሚለት ዓይነት ነው። ጋዜጠኛው ለምሳሌ እነማን ብሎ ጠይቆት ቢሆን ኖሮ ደርግን ቀድሞ መዋራቱ አይቀሬ ነበር። አዎ! ኢትዮጵያዊው ደርግ ከፖለቲካ ባላንጣዎቹ ጋር በገጠመው ፍጥጫ የኢትዮጵያን ሕዝብ ልጆች ማህል አስገብተው እየተጋገዙ በፈጸሙት እልቂት ለሕዝባዊ ችሎት አስቀርቦ የሚያስፈርድ ወንጀል ካለባቸው ድርጅቶች ውስጥ አንዱ መሆኑ አያጠያይቅም። ነገር ግን እንደ ትግራይ ወያኔዎች ታሪካዊ ክብሩን ክዶና ኢትዮጵያዊ ሰውነቱን አዋርዶ ለታሪካዊ ጠላቶቻችን እራሱን አሳልፎ የሸጠና የዓላማቸው አስፈጻሚ ሆኖ በመዝመት የእናት አገሩን ብሔራዊ አንድነት ያናጋ፣ የባህር በሯን በፈቃዱ አሳልፎ ሰጥቶ የዘጋ፣ ለዘመናት ተሳስቦ የኖረውን ሕዝብ በጎሳ ፖለቲካ አቃቅሮ በቀላሉ የማይለቅ ደም ያቃባ የጥፋት መልእክተኞች ስብስብ አይደለም። በመሠረቱ ደርግ በሞያ መስክ የተሰባሰበ ይሁን እንጅ በብሔረሰባዊ ስብጥሩ ከታየ ደግም አብዛኛወቹን የኢትዮጵያን ብሔረሰቦች የሚወክል ነበርማለት ይቻላል። ወያኔወች ግን የሚወክሉት ከቃል-ኪዳን ጌቶቻቸው ቀጥሎ ቢበዛ የትግራይን ሕዝብና የክህደት ዓላማቸውን ብቻ ነው።

ስለሆነም እኔም በደርግ አባልነቴ አቶ ስየ ደግሞ በወያኔ አባልነቱ የፈጸምነውን ድርጊት በመወከል የምንገደልበትን መሳሪያና የምንሰቀልበትን ገመድ ይዘን ከኢትዮጵያ ሕዝብ ችሎት ብንቀርብ ማነን ገሎ እንደሚያንጠለጥልና ማነን በነፃ እንደሚያሰናብት ፍርዱን ለኢትዮጵያ ሕዝብ እተወዋለሁ። ስለእውነት ለመናገር ሰው የገደለ ደርግንና የሰው ልጅ መፈጠሪያ የሆነችውን የብዙሐን እናት አገር ለማጥፋት አቅዶ የዘመተና ሕዝቧን በብሔረሰባቸው እየመረጠ ሲጨርስና ሲያጫርስ የኖረ ከሐዲ የአረመኔወች ቡድን ጥፋታቸው ከደርግ ጋር እኩል ነው ብሎ መናገር እራሱ በአለፈው ክህደቱና አረመኒያዊ ድርጊቱ አለመጸጸቱን እንጅ ለወንጀለኛነቱ አቻ ጓደኛ ማግኘቱን በፍጹም አያረጋግጥም።

**"ጀሮ ለራሱ ባዕድ ነው"** ይባላል። ወያኔወችማ በባዕዳነት የሚያዩትን ቀርቶ የዘመዶቻቸውን እንኳ የሚያዳምጥ ጀሮ ያላቸው አይመስለኝም። ለአለፉት 18 ዓመታት ለኢትዮጵያ ሕዝብ በየቀኑ ሲናዘዙለት የኖሩት የደርግን መንግሥት ገልብጠው ነፃ ያወጡት መሆናቸውን ነበር። ሌላው ቀርቶ እነሱ የፈጠሩት ውስብስብ ችግር ለአጎሳቆለው ሕይዎቱና በረሐብ ለአደቀቀው ጎኑ ሁሉ ምግብ ሆኖ የሚደግፈው ይመስል ደርግን እያወገዙ ሲያታክቱት ህሊናቸውን አይከብደውም። በአሁኑ ወቅት ወያኔወች ቀርቶ የቋመጥንለትን ሥልጣን ከአፋችን ላይ ነጥቀን ብለው በጠላትነት የፈረጁትን ሁሉ በአገሪቱና በሕዝቡ ላይ ሲፈጽሙ ለኖሩት ከደርግ የበለጠ ወንጀላቸው መከላከያና መሆን ቀርቶ መምሰል አቅቷቸው ሲንከላወሱ ለኖሩበት ድክመታቸው መሸፈኛ አድርገው ሌት ከቀን ሲናዘዙ የሚደመጡት በሁሉም ቸግር ደርግን ተጠያቂ በማድረግ ነው ። ሕዝቡ ግን ""ትሻልን ፈትቸ ትብስን አመጣሁ'" የማለት ዓይነት አድርጎ ሲያያቸው ጊዜ አልወሰደበትም። እንዲያውም እራሳቸውን አጋልጠው እንደሰጠ ከማስጣታቸው በፊት አስቀድሞ ስለአወቃቸው፣

"ፀሐይ በምእራብ ወጣች በምትገባበቱ፣

ሊነጋ ነው ስንል ገና ነው ሌሊቱ" ብሎ ገጥሞባቸው ነበር።

በመሠረቱ ደርግ ለኢትዮጵያ ሕዝብ በብዙ መልኩ የጠቀመው ወገኑ፣ በተወሰነ ጎኑ ደግም ልጆቹን አሳጥቶ ሐዘን ላይ የጣለው ተጠያቂ ወንጀለኛ መሆኑን የእነሱን የጠላትነት ኑዛዜ ሳይፈልግ እራሱ ሕዝቡ ጠንቅቆ ያውቀዋል። ስለዚህ እንደ እነሱ እናት አገሩን አጥፍቶ አገር አልባ ሊያደርገውና ከስሩ ነቅሎ ሊያደርቀው የዘመተበት ደመኛ ጠላቱ ግን አድርጎም አያየውም። ለዚህም ነው ምስክርነቱ የማያብለውና ፍርዱ የማያዳላው የኢትዮጵያ ሕዝብ፣

"አየ! ደርግ አለሜ ምን ምንህ ይረሳል፣

ብርድ ልብስህ አልቆ ኬሻህ ይለበሳል።"

ተብሎ የተገጠመለት፣ የለበሰውን ገፈው እርቃኑን ማስቀረት ብቻም ሳይሆን እናት አገሩን እየቆራረጡ ሸጠው



Document Produced by deskPDF Unregistered :: http://www.docudesk.com

ጨርሰው የመቃብር አፈር እንኳ ሊያሳጡት ለሚረባረቡት ወያኔወች አይደለም። ሕዝባዊ ወገናዊነትንና መልካም ስምና ክብርን አምርረው ለሚጠሉት ወያኔወችማ ምን እንደተገጠመባቸውና ሲገጠምባቸው እንደሚኖር ጊዜ ይናገረው ብየ አልፌዋለሁ፣ **ልብስ ገመና ከታች ነው** እንደሚባለው እስከዚያው ድረስ ግን መለስ ዜናዊና ታጋይ ጳውልስ ባልተለዩበት ሥልጣን ላይ እንዳሉ ሆነው ውዱስና ቅዱስ እየተባባሉ መኖር ይችላሉ። ከባዱ ፈተና ሲቀማጠሉ ብቻም ሳይሆን እየተመካከሩ ሲቀጥፉ የኖሩበት አዳራሽ መጋረጃው ተቀዶና በሩ ወለል ብሎ ተከፍቶ እርቃናቸውን ቁመው እንዲታዩ የሚገደዱባት የፈተናዋ ቀን የመጣች እለት ግን ቅጠል ቀጥፎ ልከለል ቢሉ እንኳ እድል የሚገኙ አይመስለኝም። በዚህ ንዑስ አርስት ስር ውስን ነጥቦችን ብቻ ለአብነት ያህል ለመጥቀስ የሞከርኩት ስምና መልኩን እየለዋወጠ በሚቀርብልን የሴራ መስተንግዶ እስከ መቸ ድረስ ስንታለል እንኖራለን? የሚል ብርቱ ማሳሰቢያ ለመስጠት ፈልጌ ነው። ይህን ስል በአለፈ ጥፋት ተጸጽቶና ከስህተት ተምሮ መመለስን ለማውገዝ ፈልጌ እንዳልሆነ ግንዛቤ ሊያገኝልኝ ይገባል። ከልብ በመጸጸትና በለመዱት ሸፍጥ በመሸወድ፣ ካለፈው በመማርና ያለፈውን በአዲስ ስልታዊ ቅርጽ እንዲቀጥል በማድረግ መካከል ያለውን ሲፈ ልዩነት ለማወቅ ከተፈለገ ሌላ ምስክር ሳያስፈልግ ሰወቹ የሚናገሩትን የድምጽ ቃና ማጣጣም ብቻ በቂ ነው።

አንድ ወታደራዊ ዘመቻ ለማካሄድ ሲታሰብ እቅድ አቀፍ ከሚሆኑት ነጥቦች አንዱ አዛዡና ረዳቶቹ ዘመቻውን መምራት የሚችሉበት ማዘዣ ጣቢያ መምረጥ ነው። ተለዋጭ ማዘዣ ጣቢያም በተጓዳኝ ታሳቢ ይሆናል። እንዲህ ያለው ቦታ የሚመረጠው ዋነኛው ማዘዣ ጣቢያ ለጠላት ጥቃት ቢጋለጥ ወይም ከዚያ እንዳሉ ሆኖ ቀጣዩን ዘመቻ ለመምራት የማያስችሉ ችግሮች ቢያጋጥሙ ፈጥኖ ለውጦ ለመጠቀም እንዲያስችል ነው። አስፈላጊ ሆኖ ማዘዣ ጣቢያው እንዲለወጥ ሲደረግ ግን የዘመቻው እቅድና ግብም አብሮ ይለወጣል ማለት አይደለም። አቶ ስየ ግልጽ አድርጎ አይንገረን እንጅ ለማድረግ ያቀደው ይህነኑ ነው። በውል እንደሚታወቀው የሕዝባዊ ወያኔ ሐርነት ትግራይ በዓላማው የከሰረ፣ ማዘዣ ጣቢያው ደግሞ በሕዝብ ዘንድ በእጅጉ የተጠላና ለምት የተጋለጠ ነው። በዚህም ምክንያት ከዚያ ሆኖ ቀጣዩን የማፍረስ ዘመቻ ለማካሄድ ስልቱ የተበላ ነው። በመሆኑም ሻቢያወች ወያኔወችን በአካልና በአምሳላቸው አስመስለው እንደፈጥሩዋቸው ሁሉ ወያኔወች ደግሞ በአገኙት ልምድ ተደግፈው አንድ ነገር መፍጠር ስለነበረባቸው አረና ትግራይን ፈጥረውልና።፣ ከዚህ ላይ በውል ማጤን የሚገባው ድብብቆሽ ከነባሩ ነጻ አውጭ ድርጅት ጠቅላይ ሡፈር ያለው አቶ ስብሐት ነጋ አንቀጽ 39ን የእናት አገር ማጥፊያ ፈንጅ ይዞ እኛ ካልገዛናት ቦምቡን አፈንድተን እናጠፉታለን እያለ መዛቱን እንደቀጠለ ሆኖ እያለ አቶ ስየ ደግሞ አገር አጥፊ ጓደኞቹን መታገል ያለብን  እነሱን መቋቋም በሚያስችል ተመጣጣኝ የትግል ስልት ሳይሆን በሚስማማቸው ልምምጥ መሆን አለበት ማለቱን ነው። ይኸም ማለት አረና ትግራይ ጠንክሮ እስከሚወጣና ጅምራችንን አሟልተን ከግባችን ላይ እስከምንደርስ ድረስ ጊዜ ስጡን የሚል መፈክር እያሰሙን ይመስለኛል። እነሱ እስከ አሁን የተጠፋፋንበትን የመሳሪያ ትግል አቁመን በሰላማዊ ትግል መቀጠል አለብን የሚሉን ማጥፋት አለብን ብለው የዘመቱበትን ሕዝብ ሲያጠፉትና ብዙ ሰወችን ሲያሳጡት ኑረው አላልቅላቸው ስለአለና ከዚያ አልፎ መቀጠሉ ደግሞ እራሳቸውን ጭምር አብሮ የሚያጠፋ አደጋ እንዳለው በጣም ጠባብ በሆነች ቀዳዳ ዘግይታ ሾልካ የገባች ምልክት ስለታየቻቸው እንጅ እስከ አሁን ሲፈጽሙት በኖሩት ጥፋትና ውድመት ተጸጽተው አይደለም። ገሀድ እውነታው ይህ ከሆነ የአለው አማራጭ አንድም እሺ ብሎ የእነሱን መፈክር አብሮ እያስተጋቡ ማድመቅ፣ አልያም እኛም ለእኛ ለሆነው ዓላማችንና ራዕያችን የሚሆን መፈክርና የሚያስፈክር ወኔ አለን ብሎ መልስ መስጠት የአንድነት ኃይሎች ፈንታ ይመስለኛል።

ለማጥፋት የተረባረቡባት አገር በእግዚአብሔር ኃይል አልጠፋ በማለቷ፣ የሞት ዓይነትና የመግደያ መሳሪያ ሳይመረጥለት በየሚኖርበት አካባቢ በተቀናጀ መልክ እየተጨፈጨፈ እንዲያልቅ የተዘመተበት ደመ- መራር ሕዝብም አላልቅ ብሎ እስከአሁን በመቆየቱ እንጅ እነሱማ ነገር አለሙን ሁሉ አጠናቀው የጨረሱት ይህን ሁሉ ማድረግ የሚያስችላቸውን ሥልጣን ጨብጠው የመግደያና ማስገደያ መሳሪያቸውን (ቻርተር ትብየ) ተጠራርተው ገብተው ያጸደቁና ለሚያጠፏት አገርና ለሚጨርሱት ሕዝብ ዳግማዊ ትንሳኤ የሚሆን የ100 ዓመት ሥራ መስጠታቸውን በይፋ ያወጁ እለት ነበር። ያ! እንዲሆን ያልፈቀደው አምላክ የተመሰገነ ይሁንና የአረመኔወቹን ቋንቋ እንደባቢሎን ሰወች እንዳይገጥምላቸው በማድረጉ ተጠራርተው የገቡት እየተረገጡ ሲባረሩ የፈረዱባቸው አገርና ሕዝብ ግን ይኸውና እስከ አሁን አሉ። ወደፊትም ይኖራሉ። ቀሪወቹም የግፍ ጽዋቸውን እየሞላላቸው ስለሆነ አንድ ቀን እስከ መጨረሻው ጠብታ ድረስ ለመጨለጥ የሚገደዱበት ቀን እሩቅ እንደማይሆን በእርግጠኝነት እናገራለሁ። አፈራራጁ አረመኔያዊ ድርጊታቸው ግን ቋሚ ሆኖ ሲያፈራርድ ይኖራል። ይህ ረጅም ዘመናት በታለፈባት የዓለም ታሪክ መሆን ቀርቶ ሐሳቡ እንኳ ተውጠንጥኖ የማያውቀውን እንደ ሶዶምና ገሞራው የሚቆጠር የጥፋትና የአጥፊወች አዋጅ እንደ “ወልድ” ብቻቸውን ቁመው በመቃወም ኡኡታቸውን ባሰሙት ክቡር ፕሮፌሰር አስራት ወልደየስ ላይ ምን ያህል



Document Produced by deskPDF Unregistered :: http://www.docudesk.com

እንደተደነከረባቸው አፈራራጅ ጊዜን ዳኛ አድርጎ መቃብራቸው ውስጥ ሆኖ ፍርድ በመጠበቅ ላይ ያለው ክቡር አጽማቸው ምስክርነቱን ይስጥበት ብየ ከማልፈው በስተቀር መሪር ሐዘኔን የምገልጽበት ተመጣጣኝ ቃል አላገኘለትም።

**“ቀሪ ልበኛ ነው”** እንደሚባለው ሆኖ ዛሬ የአገሪቱን የመከላከያ ኃይል በትነው ያን ሁሉ ግፍ ሲፈጽሙ ከኖሩት፣ አገሪቱን ለዘመናት ጸንቶ ከኖረው መሠረቷ ካናጉት፣ ሕዝቧን ደግሞ በቀላሉ መውጣት ከማይችልበት የችግር አዘቅት ውስጥ ከጣሉ፣ በአጠቃላይም ጠላትነትን ያለምንም አማራጭ ካቀረቡልን ጠላቶች ጋር ተቻችለን መኖር አለብን ስንል የእነዚያን ሁሉ ክቡር ሰወችና ጀግኖች አጽም አብረን እየረገጥን፣ በንጹህ ደማቸው አብረን እየዋኘንና በታሪካቸው እየተሳለቅን አብረን ብንኖር ምን አለበት እንደማለት የሚቆጠር ነው። ከዚያም አልፎ መተኪያ የሌላት ውድ ሕይወታቸውን የሰውለትንና አካላቸውን የገበሩለትን ሕዝባዊ ዓላማ ዋጋና ተርጉም አሳጥተን እነሱ እንደፈለጉ እያደረጉን እንኑር ማለት መሆኑን አብረን ያገናዘብነው አይመስለኝም። አለያማ እነ አቶ ስየ አረና ትግራይ የተባለ ተለዋጭ የትግራይ ነጻ አውጭ ድርጅት አቋቁመው እየተደራጁ፣ (ለስልታዊ ጠቀሜታ ማለት ነው) አንቀጽ 39ን እንዳለ ተቀብለው አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ ለመጠቀም እያደቡ፣ ወያኔውችን (በተለዋጭ ስማቸው ኢሕአዴግ) በሰላማዊ ትግል እንጅ የትጥቅ ትግል ምን ሲል ተነስቶ እያሉ ወደ ኢትዮጵያዊነታችን ተመልሰናል ማለት እርስ በርሱ ተላትሞ የሚፈረካከስ ገል እንጅ አምሮና ሰምሮ ለውጤት የሚበቃ ቁም ነገር ይወጣዋል ብየ አላምንም። የአገራችን ጀግኖች እንዲህ መሰሉን ለህሊናቸው የሚጎረብጥ አጥያያቂ ጉዳይ የሚገልጹበት አባባል አላቸው፣

> “ወዲያ ማዶ ሆኖ አንድ ሰው ተጣራ፣ ወዲህ ማዶ ሆኖ አንድ ሰው ወይ አለው፣
>
> ባይገባን ነው እንጅ ይህ ነገር ለእኛ ነው።”

ብለው ይገልጹታል። ስለዚህ ነገሩ በእስራተጅካዊ ግንዛቤ ሲታይ በማን ላይ እንዳነጣጠረ ሊገባን የሚገባው ሊገባን ይገባል።

**<u>መ. 3. የትግራይ ሕዝብ ታፍኖዋል የሚል አቋም ያላቸውን በሚመለከት፣</u>**

ሦስተኛው ቡድን የትግራይ ሕዝብ እንደማህል አገሩ ሕዝብ (እንዲያውም በባሰ ሁኔታ) ታፍኖዋል የሚል አቋም ያላቸው ናቸው። ከመታገል መች ተገታ የሚሉም አሉ። የዚህ ቡድን አባሎች ወያኔወች በአገሪቱም ሆነ በማህል አገሩ ሕዝብ ለይ የሚፈጽሙትን ግፍና በደል አይደግፉም። እንዲያውም የአገሪቱን ሉአላዊነት ያስደፈሩና ብሔራዊ ጥቅሟን አሳልፈው የሰጡ ተጠያቂ ወንጀለኞች ናቸው የሚል ብርቱ ተቃውሞ ያላቸው ሁሉ ያሉበት ስብስብ ነው። ነገር ግን ከዚህ ጋር ተያይዞ በትግራይ ሕዝብ ላይ ሊያመጣ ይችላል ብለው የሚሰጉትን በብዙ መልኩ የተወሳሰበ ችግር መከላከል የሚፈልጉት የተፈጸመው ግፍና በደል ሁሉ የትግራይንም ሕዝብ አብሮ እንደጎዳው አድርገው በማቅረብ ነው። በእርግጥም የወያኔወችን አገር የማጥፋት ተልእኮ በመቃወማቸው የተገደሉ፣ ታስረው የተሰቃዩ፣ ንብረታቸውን ተወርሰው ለከፋ ማህበራዊ ችግር የተዳረጉ ብዙ የአካባቢው ሰወች ሊኖሩ ይችላሉ፣ አሉም። ነገር ግን በትግራይነታቸው የተገደሉ ቀርቶ ታስረው የተንገላቱ አንድም እንኳ ለማስረጃ ያህል አይገኝም። እንዲያውም የትግራይ ሕዝብ ልጆቹ እንደፈለጉ የሚናጥጡበት የኛ መንግሥት ነው የሚያሰኝ የሥነ-ልቦና ጉልበት ስለአለው ማህበራዊ ደህንነቱ የተረጋጋ ነው። ሌላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ግን እንዲህ ያለውን ነጻነት ተገፎ ከአጣ 18 ዓመታትን አስቆጥሮዋል። በረጅም ዘመናት ታሪኩ ያለመንግሥት የኖረበት ወቅት ቢኖር ዘመነ ወያኔ ነው። በፋሺት ኢጣሊያ ወረራ ዘመን እንኳ በስደት የሚወክለው መንግሥት ነበረው። አገሪቱ እራሷም ብትሆን በአሁኑ ወቅት የምትታየው ሉአላዊነቷ እንደተከበረላት ሕብረ-ብሔር አገር ሳይሆን በታላቋ የትግራይ ሪፐብሊክ መንግሥት ስር እንደምትገዛ አንዲት ክ/ሐገር ነው ቢባል ተጋንኖ የቀረበ ነው አያሰኝም። እንዲያውም እነመለስ በኤርትራዊነታቸው የዘመናት ታሪክን ክደው ከእናት አገሯ የገነጠሏትን ኤርትሪያን በቅኝ ግዛት ገዝታብናለች የሚሉበትን እጅግ የመረረ ጥላቻና የለየለት የደመኛ ጠላትነት አቋም መሠረት አድርገው እስከ አሁን ሲወስዷቸው ከኖሩት እርምጃወች ጋር ከተገናዘበ እኛም ኢትዮጵያን በቅኝ ግዛት ለመግዛት የምንችልበት አጋጣሚ ስለተፈጠረልን በቀላችንን መወጣት አለብን ብለው የሚያካሂዱት መሆኑ ሊያጠራጥረን አይገባም። ሌላው ቢቀር እጁን በሰጠው ሠራዊትና ከዚያ ይኖሩ በነበሩት ኢትዮጵያውያን ላይ የተፈጸመውን ዘግናኝ እልቂት **"ሲያንሳቸው ነው"** ማለታቸው የጠላትነታቸው ማረጋገጫ እንጅ ከቶ ሌላ ሊሆን አይችልም።

ስለዚህ በጠላትነት የፈረጇቸው እንጅ በመንግሥትነት የማይወክላቸው ጠላታቸው በአማራነታቸው፣ በኦሮሞነታቸው፣ በአፋርነታቸው፣ በአኙዋክነታቸው፣ በሱማሌነታቸው (ኢትዮጵያዊ ሱማሌወች) የፈጃቸውን



Document Produced by deskPDF Unregistered :: http://www.docudesk.com

ግን በብዙ መቶወች ብቻም ሳይሆን በብዙ ሺህወች መቁጠር ይቻላል። በተናጠል አረመኔያዊ ግድያ ሲፈጸምባቸው የኖሩትን ስይጨምር በአርባ ጉጉ፣ በበደኖ፣ በጋምቤላ፣ በኦጋዴን፣ ወዘተ የተካሄደውን ጅምላ ጭፍጨፋ መጥቀሱ ብቻ በቂ ማረጋገጫ ነው። ከዚህም በተጨማሪ በትግራይ ውስጥ በየትኛው ቤተ-ክርስቲያን የተሰበሰቡ ምእመናን ናቸው እንደ ጎንደር አደባባይ ኢየሱስ በመትረጌስ የተቆሉ? እንደእነ ነብይ አለማየሁ ያሉ ሕጻናትና እንደእነ ወ/ሮ እቴነሽ ይማምን የመሰሉ እናቶች በሰለጠኑ ሰው ገዳይ መተሬ ተኳሾች ግንባር ግንባራቸውን እየተፈለጡ ጎዳና ላይ የተጣሉት? ተስፋሁን ወርቁን ጨምሮ ሌሎችም የዩኒቨርስቲ ተማሪወች አገራቸውን ለማጥፋት ሥራየ ብሎ የዘመተውን የፈርኦን አምባሳደር (ፒተርስ ፒትሮስ ጋሊን) ጉብኝት  በስላማዊ ሰልፍ ለመቃወም በመዘጋጀታቸው ብቻ ተቀልቦ በፈረጠመ ክንድ በተሰነዘረ ሳንጃ የተተለተሉትና በጥይት የተቆሉት? ሽብሬ ደሳለኝና ሌሎችም የቅንጅት ደጋፊወች ናቸው ተብለው የአገሪቱ ዜጎች የተጨፈጨፉት ወዘተ በየትኛው የትግራይ ከተማና ዩኒቨርስቲ በራፍ ላይ ነው? ሌላው ቢቀር በጥይት እንድንገላቸው የተገደድነው የአድማ መበተኛ መሳሪያ መግዣ የሚሆን የውጭ ምንዛሬ ስለሌለን ነው ተብሎ የተዘበተባቸው ይረሳልን?

እንደ ሲኦል በሚቆጠሩ ማጎሪያ እስር ቤቶች ታፍነው የቁም ስቃይ እየዩ የሚያልቁትና በደረቅ ምላጭ እየተላጩ አይምሬ ገዳይ በሺታ እንዲጋሩ የተደረጉት በየትኛው የትግራይ ማጎሪያ እስር ቤት ነው? ወዘተ ለሚሉት አፈራራጅ ጥያቄወች ግን እዚህ ቦታና እነገሌ ብለው ስም በመጥራት ተጨባጭ መረጃወችን የሚጠቅሱልን አይመስለኝም። ቀደም ሲል እንዳመለከትኩት እንዲህ ያለው ከጋራ መፍትሄው ጎዳና በጣም የወጣ መከላከል በሁለቱም ጎን ጉዳት ያለው ነው። በአንድ በኩል የትግራይን ሕዝብ ትክክለኛ ምርጫውን ጋርዶ በጀመረው አጥፊወችን የማጀብና የማጥፊያ መሳሪያ ሆኖ የማገልገል ዘመቻውን እንዲገፋበት የሚያደርግ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ የኢትዮጵያ ሕዝብ በትግራይ ሕዝብ ላይ ያለውን እርሾ አሚጦ እንዲደፋና የአንድ ጎራ ሰውች አድርጎ እንዲያያቸው የሚያደርግ መሆኑ በውል ሊታወቅ ይገባል።

### *<u>መ.4. ጥያቄው ለወያኔወች ፕሮፓጋንዳ ፍጆታ ያመቻል የሚል ስጋት ያለባቸው ቢኖሩ፣</u>*

ጥያቄው በአንድነት ሐይሎችም ሠፈር በግለሰብ ደረጃ የተለየ አስተያየት ያላቸው ሊኖሩ ይችላሉ የሚል ግምት አለኝ። ይኸም ወያኔወች ጥያቄውን ለፕሮፓጋንዳ ፍጆታ ቢጠቀምበት የትግራይ ሕዝብ ተጠቃሎ ገብቶ የወያኔወችን ሠፈር የሚያጠናክር ይሆናል የሚል ስጋት ያለባቸው ሊሆኑ ይችላሉ። **"እስከ አሁን የትና ከማን ጋር ነበር?"** ለሚለው ተዛማጅ ጥያቄ ግን ሁነኛ መልስ ያላቸው አይመስለኝም። እኔ ግን ለማንም ሳይሆን ለራሱ ሲል የራሱን የውስጥ ችግር እንዲመረምርና አሰላለፉን እንዲያስተካክል የሚጠይቅ እንጅ ተጠቃሎ እንዲሄድ የሚገፋፋ አይደለም። እንዲያውም በዚህ እጅግ ወሳኝ በሆነ ወቅት የእሱ ሚና በግልጽ መታወቅ የእሱም ጭምር በሆነችው እናት አገሩ ህልውና ብቻም ሳይሆን በወደፊቱ አብሮነትም ላይ የሚኖረው ገንቢ አስተዋጽኦ ልጆቹ ሊያቃቡት የፈለጉትን በቀላሉ ሊጠራ የማይችል የጥቁር ደም እዳ እንደ ጲላጦስ እኔን አልቀባኝም ብሎ እራሱን ነጻና ንጹህ አድርጎ ማሳየት የሚችልበት መልካም አጋጣሚ ነው ብየ አምናለሁ።

በመሠረቱ ወያኔወች ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን ገድለው ለመቅበር አቅደው የተነሱና ተዘጋጅተው የዘመቱ ደመኛ ጠላቶች መሆናቸውን በራሳቸው እምነትና ድርጊት ካረጋገጡ ይኸውና 18 ዓመታትን አስቆጥረዋል። በጫካ ኑሮዋቸውም ቢሆን ለዚህ እየተዘጋጁ መሆናቸው ሚስጥር አልነበረም። እንዲህ ያሉም በመሆናቸው ባለፉት ዓመታት በኢትዮጵያ ከሕዝብ፣ በሕዝብ፣ ለሕዝብ የቆመ መንግሥት ነበር ወይ? አሁንስ አለ ወይ? የሚያሰኝ ጥያቄ ዘግይቶም ቢሆን የሚያስነሳ ሆኖዋል። አጭርና ግልጽ የሆነው መልስ የለም ነው። ይህን ስል ግን ኳኩለው ባሳመሩዋቸውና አደላድለው ባስቀመጡዋቸው የቃል ኪዳን ጌቶቻቸው እውቅና አግኝተው አገሪቱን እንደፈለጉ የሚያብጠለጥሉና ሕዝቧን እያመሱ የቁም ስቃይ የሚያሳዩ መንግሥት ተብየ የአገርና የሕዝብ ጠላቶች ስብስብ የለም ማለት አይደለም። ነገር ግን የፖለቲካ ቋንቋንና ገሀድ እውነታን በቀኝና በግራ አቁሞ ለሚፋረድ ወገን የሚደርስበት መደምደሚያ እንደእኔው የለም የሚል እንደሚሆን እርግጠኛ ነኝ። እንዲያውም ከኢትዮጵያ የረጅም ዘመናት የመንግሥትነት ታሪክ አኳያ ከተገናዘበ ለአገራቸው ዳር ደንበር መከበር እራሳቸውን አሳልፈው እየሰጡ ያለፉ ባለህያው ታሪኮች እንጅ አገራቸውን አሳልፈው የሰጡና እንደ ዳቦ እየቆረሱ የሸጡ መንግሥታት ፈጽሞ አልነበሩም። በአገሪቱ ብሔራዊ አንድነትም ሆነ በሕዝቧ ማህበራዊ ደህንነት ተወዳዳሪ የሌለው ማናጋት፣ የሐብት ውድመትና የሕዝብ እልቂት የደረሰበት እጅግ አስከፊ ዘመን ቢኖር ከዮዲት ጉዲት፣ ከህመድ ግራኛና ከፋሺስት ኢጣሊያ ወረራ ቀጥሎ በአሁኖቹ ቅጥረኛ የወንበዴወች ዘመን ነው። ስለሆነም አገርን ለማጥፋትና የአንዲት እናት አገርን ሕዝብ እርስ በርሱ በማጫረስ በአንድነት ጥላ ስር ተመልሶ እንዳይገናኝ ለማድረግ ግባቸው አድርገው



Document Produced by deskPDF Unregistered :: http://www.docudesk.com

ለዘመቱ የጥፋት መልእክተኞች ስብስብ የብሔራዊ መንግሥትነት ሥነ-ባህሪይ አላቸው ብሎ እውቅና መስጠት ከመጀመሪያው ጀምሮ የተፈጸመ ከፍተኛ ስህተት ነው። የክህደት ዓላማቸውንና የአገርና የሕዝብ ጠላትነታቸውን ለመጋረድ ሲሉ እራሳቸውን መልሰው በሚጠሩበት የቀለም ስማቸው ኢ.ሕአዴግ እያሉ መጥራትም እራሱ በሥነ-ልቦና መሰለብና ለጥፋት ዓላማቸው ምርኮኛ ሆኖ መንበርከክ ነው።

በአጠቃላይ ይህን ያሚላሉ የማይባሉት የጫካ ሰው ግብረ-አራዊት መንግሥት ናቸው ከተባሉ "**መንግሥት**" ለሚለው ቃል ትርጉም (ፍች) የሰጡት የቋንቋ ባለሞያወች ***የአንድን አገር ሉአላዊነት የሚያስከብር ብቻም ሳይሆን አሳልፎ መስጠትን፣ እየቆረሰ መሸጥንና ጨርሶ ማጥፋትንም ያጠቃልላል የሚል ቃል መጨመር አለባቸው ማለት ነው።*** አለያማ በግብራቸው ቀርቶ በቅርጻቸው እንኳ መንግሥት የሚለው ቃል እራሱ በመንግሥትነት አያውቃቸውም። ስለዚህ የትግራይ ሕዝብ አንድም ለኢትዮጵያ ሕዝብ ባይሆኑም የእኔ መንግሥት ናቸው ይል እንደሁ አቋሙን እንዲያሳውቅ፣ አለያም የእኔም አይደሉም የሚል ከሆነ ደግሞ ከኢትዮጵያውያን ወገኖቹ ጋር ግንባር ፈጥሮ እንዲታገል ማሳወቅ ወቅቱ የማያልፈው አስገዳጅ ጥያቄ ሆኖ የቀረበለት መሆኑን ማወቅ አለበት።

ቀደም ስል እንደገለጽኩት የኢትዮጵያ ሕልውና በውድ ልጆቿ ክቡር መስዋእትነትና በአጽማቸው አጥርነት ተከብሮ የኖረና ወደፊትም የሚኖር ነው። ልዩነቱ የዛሬዋም ሆነች የወደፊቷ ኢትዮጵያ እንዳለፈው ጊዜ ገዳይ ባንዳወች ገንነው የሞተልሺ ሳለ የገደለሺ በላ የሚባልባት ሳትሆን የገደሏት በአካል ብቻም ሳይሆን በሞራልና በታሪክም ሲገደሉ የሚኖሩባትና እዳ ወራሺ ቤተሰቦቻቸው ሁሉ እያፈሩ የሚኖሩባት፣ የተሰውላት ጀግኖች ደግሞ ታሪካቸው በክቡር ማህድር ላይ በወርቅ ቀለም ትጽፎ እንደገድል ሲነገር የሚኖርባትና ታሪክ ወራሺ ቤተሰቦቻቸው ደግሞ እንደ ብርቅ እየታዩ ሲከበሩ የሚኖሩባት አገር የምትሆን መሆኗ ነው። የእኔ ጥያቄ የትግራይ ሕዝብ ይህን ሁሉ አስቦበት እንዲወስንና የልጅነት ግዴታውን ለእናት አገሩ እንዲወጣ የሚጠይቅ በመሆኑ በተቃራኒው ሊተረጉም አይገባም፣

የትግራይን ሕዝብ ከኢትዮጵያዊነቱ ለማቆራረጥና ከኢትዮጵያውያን ወገኖቹ ጋር ለማባባድ በመካሄድ ላይ ያለውን ርብርቦሺ ቀደም ሲል በፊደል "ለ" አመልክቻለሁ። ወያኔወች ያን ሁሉ የሚያደርጉት እውነታው የት እንዳለ ጠፍቶባቸው ሳይሆን በቀን የፀሐይ ብርሀን አይታየንም የማለትን ያህል የኢትዮጵያዊነት ክብራቸውን ሺጠው የበሉና ሕሊናቸውን አውረው የሚደናበሩ ሞራለ-ቢሶች በመሆናቸው ነው። ስለዚህ እንደ እነዚህ ያሉ ለራሳቸው እንኳ የማይሆኑ የእውነት ጠላቶችና የሞራል ድሐወች መሆናቸው እየታወቀ በብዙሐን የመወያያ መድረኮች (paltalk) ከእነሱ ጋር ውርክብ መግጠም እራሳቸውን ማወቅ ላቅታቸው ህሊና ቢሶች እውቅና መስጠትና አቅደው የዘመቱበትን የጥፋት ዓላማ ለማስፈጸም የሚረዳ የመረጃ ምንጭ ሆኖ ከማገልገል ባለፈ ለኢትዮጵያ የሚበጅ ፍሬ ይዘገንበታል ብየ አላምንም። ለምሳሌ በእምነትም ሆነ በግብር አምባሳደር ሆኖ የሚወክላቸውን ሆርንን ለማስረጃ ያህል እንውሰድ። በመጀመሪያ እምነታቸው ሁሉ ባእዳዊ ስለሆነ ሆርን የሚለው የባእድ ቋንቋ ቀንድ ማለት ይመስለኛል። ቀንድ ደግሞ ከደምና ከስጋ ጋር ከነበረው ትስስር እያመነቀለ ሄዶ እራሱን ወደ ባዕዳነትና በድንነት የለወጠ  ህይወት የለሺ ግዑዝ አካል ነው። በዚህም ድህነቱ ምክንያት ሥጋ የማይቆነጥጠውና ሥጋን የሚሰማው ሁሉ የማይሰማው በድን ተለጣፊ አካል ነው። ቀንድ ያለችው አንዲት ሥራ መዋጋት ወይም ማዋጋት ብቻ ነው። በእርግጥ በእሳት እያቀለጡ ለሌላም አገልግሎት ማዋል ይቻላል። ከዚህ ውጭ  በተፈጥሮ ያልታደለውን በረከት እኛ እያስታመምን ህይወት እንዲዘራ በማድረግ አድነን የኛ አካል እናደርገዋለን ማለት እራስን ወደ እሱ እየለወጡ ሄዶ እሱን ለመሆን ካልሆነ በስተቀር ሌላ ለውጥና ውጤት የሚገኝበት አይሆንም። የአንድነት ኃይሎች ኢትዮጵያውያን ሁሉ ከአነሳሳቸው ጀምሮ አሁንም ድረስ በአደባባይ አውጀው እየነገሩን (በዚህስ ሊመሰገኑ ይገባል) የመጡ በመሆናቸው ለምን ሊረዷቸው እንዳልቻሉ አልገባኝም። እነሱ እኮ ኢትዮጵያዊነታቸውን ሺጠው በልተው የጨረሱትና የሚያዛምዳቸውን እትብት ቆርጠው የጣሉት ከብዙ ዓመት በፊት ጀምሮ  በመሆኑ በግዚአብሔር ኃይል ኢትዮጵያ ድና አብረን እንኑር ቢባል እንኳ በየትኛው የኢትዮጵያዊነት እርሾ አብረውን ሊኖሩ እንደሚችሉ ለእኔ ግልጽ አይደለም። ከዚህ ጋር አዛምጀ አንድ እምነትና ግብራቸውን አጣምሮ መግለጽ የሚችል ምሳሌያዊ አባባል መጥቀስ እፈልጋለሁ፣

የዱር አራዊትና የቤት እንሣት የቁንጅና ውድድር ለማድረግ ፈልገው ይሰበሰባሉ። ከዚያም ሁሉም በቅደም ተከል እየተነሱ ስለየራሳቸው የቁንጅና ውበት ሲናገሩ ከቆዩ በኋል በግዙፍነቷ የመጨረሻ ተናጋሪ እንድትሆን የተመረጠችው ግመል እንድትናገር ትጋበዛለች። እሷም እንደ ማማ ከላይ ሰቅሎ ለማሳየት በሚያስችላት መለሎ አንገቷ ለቅማ ብትቃኝ ሁሉም ከእሷ የተሻለ መልክና ውበት ያላቸው መሆናቸውን ስለአረጋገጠች ተፈጥሮአዊ ሐቁን ሳትክድ "**እሁን ከእኔ ምን ዓይነት ቁንጅና ትጠብቃላችሁ**" ብላ ደመደመች ይባላል።



Document Produced by deskPDF Unregistered :: http://www.docudesk.com

ስለዚህ ከወያኔወች ምን የሚጠቅም መልካም ነገር አላቸው ተብሎ ይጠበቃል? የሚናገሩት ክህደት እንጅ እውነት፣ የሚጠበቀው ጥፋት እንጅ ልማት፣ የሚሰሩት የሚመርና የሚጎመዝዝ እንጅ የሚጥምና የሚጠቅም በእነሱ ዘንድ ፈጽሞ የለም። እነሱ በጠላትነት የፈረጁት ሰው ቀርቶ ጌታ ኢየሱስ በአካል ወርዶ ቢነግራቸው እንኳ እኛ የምንፈልገው ስለሕገ-መንግሥታችንና 12% እያደገ ስለመጣው የኢኮኖሚ ግንባታችን እንጅ ስለአንተ ወንጌል አይደለም ብለው ይመልሱታል እንጅ የሚቀበሉት አይመስለኝም። ወደውም ሳይሆን ክፍ ሥራ መቸም ይሁን የት በየሄዱበት እንደጥላ እየተከተለ የሚከስ፣ የሕግ ምስክር ሆኖ ቁሞ የሚመሰክርና ዳኛ ሆኖ የሚፈርድ ክፉ ጠላት በመሆኑ ያን ሁሉ ባሰቡ ቁጥር የሚበረግጉ ግብረ-አራዊት እንጅ ከጥፋታቸው የሚማሩ ሰወች ባለመሆናቸው ነው።

የትግራይ ሕዝብ ከእኛ ተወልዳችሁ የእኛን እናት አገር ስታጠፋዋት ዝም ብለን አናያችሁም ብሎ በአገር አጥፊ ልጆቹ ላይ ተጽእኖ ማሳደር የሚያስችል ኃይልና ጉልበት ያለው መሆኑ በራሱ ልጆች ምስክርነት የተረጋገጠ ሐቅ ሆኖዋል። እሱ ግን ከዚህ በተቃራኒው እሰየው የኛ ጀግኖች ብሎ ማበረታታቱንና በጅምራችሁ ቀጥሉበት ብሎ መደገፋን ማረጋገጥ የሚያስችሉ ብዙ መረጃወችን መጥቀስ ይቻላል። ከእነዚህም አንዱ ወያኔወችን ከመቃብር ውስጥ ፈንቅሎ አውጥቶ ከዚህ ደረጃ ላይ መድረስ ያስቻለ በደብረ ታቦር አካባቢ የተካሄደው የውጊያ ታሪክ ነው። በደብረታቦር አካባቢ በተለይም በዓለም ሳጋ ግንባር በተካሄደው ውጊያ የወያኔወች ጦር በጀግናው የኢትዮጵያ አብዮታዊ ሠራዊት ያልጠበቀው ከባድ ምት በመመታቱ ያልጠበቁት እልቂትና ውድቀት ደርሶባቸው ነበር። በዚያም ምክንያት መሳሪያና ትጥቃቸውን በየቦታው እየጣሉ ጀሌያቸውን ያለእዝና ቁጥጥር ተበታትነው ወደ ትውልድ አካባቢያቸው ይጎርፉ ነበር። ተራው ተዋጊ ጦር ቀርቶ አዛገሮቹ እንኳ የውጊያ እቅድ ካርታቸውን፣ የውጊያ ትእዛዛቸውንና ወታደራዊ የሚስጥር ቃል መጠቀሚያ ሰነዳቸውን ወዘተ እንኳ ማዘዣ ጣቢያ አድርገው ይጠቀሙበት ከነበረው ቦታ አንስተው ለመሸሽ ፋታና ወኔ ስለአጡ እንዳለ ትተውት እግሬ ነፍሴን አውጭልኝ ብለው እንደፈረጠጡ በታሪክ ማህደር ተመዝግቦ የተቀመጠ በመሆኑ ነገ የእነሱን ተራራ ያንቀጠቀጠ ትውልድነትና እውነተኛውን የውጊያ ታሪክ የሚያፈራርድ ጊዜ ሲመጣ የሕግ ምስክር ሆኖ የሚቀርብ ይሆናል። በዚያን ወቅት ተራራውን ሁሉ የሚያንቀጠቅጥ ቀርቶ ትግራይን እንኳ በአሰተማማኝ ሁኔታ ለመከላከል የሚችል በቂ ልምድና የሞራል ብቃት ያለው ጦር አልነበራቸውም። ወያኔወች ከእንደዚያ ያለው ውድቀት ድነው ኢትዮጵያን በሙሉ ለመቆጣጠርና ይህን ሁሉ ጥፋትና እልቂት ለማድረስ የቻሉት ብዙ አፍራሺ ገጠመኞች ተገጣጥመው ስለረዷቸው ነው። ከዚህ ውጭ እነሱ እንደሚሉት ሌላ ታምርና ታሪክ የለውም። ተጋግዘው የረዷቸውን ገጠመኞች ሁሉ በዚህ ላይ መዘርዘር ባይቻልም ከአርስቱ ጋር በበለጠ የሚቀራረቡትን አራት ነጥቦች ብቻ እጠቅሳለሁ፣

1 በጀግናው አብዮታዊ ሠራዊታችን የተገኘውን እንደዚያ ያለውን ብዙ ጠቀሜታ ያለው ከፍተኛ ድል ማጠናከር የሚያስችል የማሳደድ ውጊያ ሽምጥጦ ይሮጥ በነበረው የወያኔወች ጦር ላይ ማካሄድ ሲቻል ከሀዲ ባንዳው የጦሩ አዛዥ ግን የተገዛበትን ውለታ ለመመለስ ሲል እንደ ግራምጣ በአልኮል እየተነከረ ኢየሱስ ተራራ ላይ ተቀምጦ በቂ የመልሶ መቋቋሚያ ጊዜ ስለሰጣቸው ነው። ስለእውነት ለመናገር እንደዚያ በብዙ መልኩ ተጠቅቶ በተራቆተው (በሞራል፣ በድርጅት፣ በመገናኛና የቅርብ አመራር እጦት፣ በአካባቢው ባይተዋርነት) ወዘተ ጦር ላይ የማሳደድ ውጊያው ቀጥሎ ቢሆን ኖሮ ማህል አገር ቀርቶ ትግራይ ውስጥ እንኳ መልሶ የመቋቋም እድላቸው እጅግ በጣም ያነሰ ነበር።

2 ግንባሩን ተመትቶ የተበታተነው ጦር ከትግራይ ውጭ አንዋጋም ብሎ ወደ ትግራይ በመመለሱ የወያኔ መሪወች የቀን ጨለማ ውጧቸውና የጣእር ሞት አንቋቸው ይንፈራገጡ ነበር። ያ ሁኔታ እንዲለወጥና ጦራቸው ከተበታተነበት ተሰባስቦ ነፍስ እንዲዘራበት ያደረገው ከትግራይ ሕዝብ ጫማ ስር ወድቀው አንዋጋም ያለውን ጦር እንቢታ ወደ እሺታ እንዲለውጥላቸው በመማጸናቸው ነው። ሕዝቡም ጥያቄያቸውን ተቀብሎ በየቦታው የተበታተነውን ጦሩ እያንዳንዱ የራሱን ልጆች (ከ5-6 አሰልፏልና) በአጠቃላይ ደግሞ ጦሩን አሰባስቦ ለውጦላቸው ተመልሷል። ከሁለቱ አንዱ ሥራ ላይ ውሎ ቢሆን ኖሮ ወያኔወች አለቀላቸው ማለት ነበር።

3 በብዙ ችግር ተወጥረውና የሚያደርጉትን ለይቶ ማወቅ አቅቷቸው እየዋለሉ እሳቸው ብቻ የሚያውቋትን ቀን ሲጠባበቁ የነበሩት የአገሪቱ ፕሬዚደንት ትግራይን በነጻ እንደለቀቁላቸው ሁሉ የውያኔወችን ቅስም አንኮታኩቶ ሰብሮ ያን ለመሰለ ድል መገኘት ከፍተኛ ተጋድሎ ያደረገውን 15ኛ ነብሮ ክ/ጦርን ከደብረታቦር ግንባር አንሰተው አዲስ አበባ በቀላሉ ለመግባት የሚያስችላቸውን በር ወለል አድርገው ስለከፈቱላቸው ነው።



Document Produced by deskPDF Unregistered :: http://www.docudesk.com

4 ጦርነቱ ፊት ለፊት ዘምተው ድባቅ ተመተው የተመለሱት ታሪካዊ ጠላቶቻችን በአዲስ ስልትና ቅንብር ጥቁር ቅጥረኛ ወታደሮቻቸውን አዝምተው ሁለንተናዊ ድጋፍ እየሰጡ የሚያካሂዱት ጦርነት ስለነበር ነው። በአሁኑ ወቅት ግን እነዚህን ብቻም ሳይሆን ሰው መሆናቸውን እንኳ ረስተው ክህዋው የመጣን ልዩ ፍጡር ነን ሊሉን ምንም ያህል አልቀራቸውም። ያን የጭንቀት ምጥ አርግዘው እያማጡ ያለፉበትን ገሀድ እውነታ ሸምጥጠው ክደው ተራራ ያንቀጠቀጥን ትውልድና ልዩ ጀግኖች ነን እያሉ ቢያወሩ የእራሳቸውን ሚዛን የለሺ ጭንቅላት ከሚያታልሉ በስተቀር ሌላው ግን ከትዝብት ባለፈ እውነት ነው ብሎ የሚቀበላቸው እንደማይኖር እርግጠኛ ነኝ።

የነጥቡ መደምደሚይ የትግራይ ሕዝብ በዚያን ወቅት በጀመሩት ውጊያ እንዲገፉበት ግንባር ድረስ ሄዶ የበረታታቸው ምናልባት ደርግን ለማስወገድ ነው ተብሎ ተነግሮት ሊሆን ይችላል። ዛሬ ግን ዓላማና ግባቸው በማን ላይ እንዳነጣጠረ በራሱ ቋንቋ እየተነገረውና በገሀድ እያየው ነው። ይኸም ሆኖ ትላንት ቀጥሉ ያለበትን አንደበትና የተፈራበትን ጉልበት ዛሬስ መረን ስለለቀቃችሁ በቃችሁ አቁሙ ለማለት አልፈለገም። ስለሆነም የትግራይን ሕዝብ ችግር እንጋራለን የሚሉ ኢትዮጵያዊያን ሁሉ መረባረብ ያለባቸው ከወያኔወች የማጥፊያ መሳሪያነት ለማላቀቅ እንጅ ከዚያ እንዲላቀቅ ብንነግረው ጠቅሎ ሊሄድ ይችላል የሚል ስጋት ማሳደር በትግራይ ሕዝብ ብቻም ሳይሆን በኢትዮጵያ የወደፊት ህልውናና አብሮነት ላያ አብሮ እንደማሴር የሚቆጠር ነው። እንዲያውም ይህን ጥያቄ ገና ከጅምሩ አቅርበንለት ቢሆን ኖሮ ደፍርሶ የሚጠራበትና ከሁለቱ አንዱን ሆኖ የምናይበት ሁኔት መፈጠሩ አይቀሬ ነበር።

በአሁኑ ወቅት የትግራይን ሕዝብ በማናቸውም መልኩ የሚጠቀሙበት ወያኔወች ናቸው። የትግራ ሕዝብ ለሕዝባዊ ወያኔ አንድ ብቻም ሳይሆን 5 እና 6 ልጆቹን አሳልፎ እንደሰጠ በየአደባባዩ በኩራት የሚያወሩት ነው። ይኸም እራሱ ወያኔ ማለት የትግራይ ሕዝብ ማለት ነው የተባለውን ያረጋግጣል። ገሀድ እውነታው ይህ ከሆነ የትግራይን ሕዝብ ከወያኔወች መሳሪያነት ከማላቀቅ ውጭ የሚካሄደው ምክንያት ድርደራና የሚደረገው አጉል የመከላከል ዙሪያ ከበባ ችግሩ የበለጠ እየተወሳሰበ እንዲሄድ እድል መስጠትና የጨርሶ መጥፊያ ጊዜን ተቀምጦ እንደመጠበቅ የሚቆጠር ነው።

__ሠ. የትግራይ ሕዝብ ሆይ!__

ባለፉት ገጾች ለማመልከት የሞከርኩት ለጥያቄየ ማገናዘቢያ ሊሆኑኝ የሚችሉ ተጨባጭ መረጃወችን ነው። በዚህ የማጠቃለያ ጽሁፌ ለመግለጽ የምሞክረው ግን የተመለከቱት ገሐድ እውነታወች ከሁለቱ ለአነዱ የሚያመጡት ጠቃሚ ውጤትና ለሌላው ደግሞ የሚያስከትሉት ጉዳት ምን ሊሆን እንድሚችል ማመላከት ነው። የጥያቄየ መሠረታዊ ዓላማ ብዙ የጠቀሙህ መስለው በብዙ ሊጎዱህ የሚረባረቡት ልጆችህ ካከማቹብህ ባለብዙ መልክ የችግር እዳ ነጻ ማውጣት መሆኑን በጽሁፌ መግቢያ ገልጫለሁ። እዳ ሲባል ደግሞ በቀላል ትርጉሙ ተሠርቶ የሚገኝና ተቆጥሮ የሚከፈል ገንዘብ ብቻ ማለት አይደለም። ክቡር የሆነውን ታላቅ ፍጡር መግደልና የእግዚአብሔርን ህንጻ ማፍረስ በቁጥር አስልቶና በኪሎ ለክቶ ሊገልጹት የማይቻል ከባድ እዳ ነው። በተለይም ከአንዲት እናት አገር ተወልዶ አፈር እየፈጩና ውሀ እየተራጩ አድገው፣ በአንድ ማእድ እየተጓረሱና ክፉና በጎውን እየተጋሩ አብረውት ከኖሩት ወገን ጋር በቀላሉ የማይነቀል ቂም በቀል መታከልና ጥቁር ደም መቃባት ብዙ መዘዝ ያለው ከባድ እዳ ነው።

የብዙሐኑን እናት አገር ገና ሁኔታው አመችቶናል ብሎ ለማጥፋት መረባረብ የጊዜ እርዝመት የማይሺረውና የትውልድ ጥልቀት የማይረሳው ከባድ እዳ ነው። በተለይም የተወለዱባትን እናት አገር ክዶ ለጠላት አሳልፎ መስጠትም ይሁን መሸጥ በእምነትም ሆነ በግብር እንሱን መሆን ስለሆነ በእነሱ ዓይን የሚያሳይና በእነሱ ላይ የሆነው ሁሉ እንዲደገም የሚያስገድድ ከዳወቹ ሁሉ የበለጠ ከባድ እዳ ነው። እነዚህ ሁሉ ያለምንም ምክንያት በአንተ ልጆች የተፈጸሙ አፈራራጅ ወንጀሎች ናቸው። የተፈጸሙት ግን ባንተ ስምና መሳሪያነት ነው። ሊያራግፉብህ ካከማቹት ባለብዙ መልክ እዳ እራስህን ነጻ ማውጣት አለብህ ብየ የምወተውትህም በዚህ ምክንያት ነው። ልጆችህ ሐገረ ብዙ አገር የለሾችና ባለብዙ ሐብት አገር ሻጮች በመሆናቸው አንድ ቀን አዙሯቸው ወይም አድጧቸው ቢወድቁ አምልጠው ሄደው የተደላደለ ኑሮ ለመኖር የሚችሉበትን ቅድመ ሁኔታ አመቻችተው ቀናቸውን ብቻ በመጠበቅ ላይ ያሉ ናቸው። መኖሪያ ቤታቸውን አደራጅተዋል። የዘረፉትን ገንዘብ በተለያዩ የውጭ አገር ባንኮች አጭቀዋል። ቤተሰቦቻቸውንም ወደ አዘጋጁት የመመሸጊያ አገርና ከተማ ማጓጓዝ ጀምረዋል። እነዚህ ሁሉ ዝግጅቶች የሚያረጋግጥልህ ሐቅ ቢኖር ወያኔወች ከአንተ ጋር የሚቆዩት የአንተ መሳሪያነት እስከቀጠለ ድረስ ብቻ ነው። ከዚያ በኋላ ግን ከአንተ ማህል በጽናት



Document Produced by deskPDF Unregistered :: http://www.docudesk.com

ቁመው የአንተን ችግር እየተጋሩ አብረውህ የሚኖሩ አይደሉም። አትርፌውልህ የሚሄዱት ቀሪ ሐብት ቢኖር ከወገንህ ጋር ያቃቡህን በቀላሉ ታጥቦ የማይጠራ ጥቁር ደም ብቻ ነው።

በአንተ ልጆች ምክንያት የስንት ኢትዮጵያውያን ቤት እንደፈረሰ፣ የስንቱ ልጆች ያለአባትና ስንቶቹ የቤት እመቤቶች ያለባለቤት እንደሚኖሩ ቀደም ሲል ገልጨዋለሁ፣ ይኸን መቸውንም ቢሆን ከህሊና የማይጠፉ ዘግናኝ ድርጊት የጠቀስኩት ያለፈ ቁስል ቀርፍቸ እንዲያመረቅዝ ለማድረግ ፈልጌ ሳይሆን በሺታውን የፈጠሩት በሺተኞወቹ ልጆችህ የሁልጊዜም ታማሚወች እንድንሆን አቅደው የብከላ ዘመቻቸውን የቀጠሉ በመሆናቸው ነው። ስለእውነት ለመመስከር እነዚያ ጀግኖች በየበረሀው ረግፈው የቀሩት እንደ አንተ ልጆች የሚወሸቁበት መንደር አጥተው ሳይሆን ለብሔራዊ አንድነታቸውና ለኢትዮጵያዊ ክብራቸው ብለው መሆኑ ሊያጠራጥርህ ባልተገባም ነበር። ዛሬ አጽማቸው እንደ ቀላል ነገር በየቦታው ወድቆ ስለሚታይ፣ ከቁጥር ያልጎደሉት ደግሞ በህይወት እንዳሉ ቢቆጠሩም ለልመና ተዳርገው በአካል ረግፈው ስለሚታዩ ነገረ-ዓለሙ ሁሉ እንዳለቀለት ተድርጎ ሊያስመካ ይችላል ይሆናል። ግን አይምሰልህ ታሪክ የማያዳላ ሚዛናዊ ዳኛ በመሆኑ ሲፈርድብህ ይኖራል። ከማናቸውም በላይ የእውነት አምላክ እንዳያብል አድርጎ የፈጠረው የራስህ ህሊናም በየበራፍህ የወደቀውን አጽም ባየህ ቁጥር ሲወቅስህ፣ እሾህ ሆኖ ሲወጋህና ዳኛም ሆኖ ሲፈርድብህ ይኖራል። የህሊናን ፍርድ የቃላት ክህደትና የምላስ ስለት ተከላክሎ የሚያስቀረው አይደለም። አንተ ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን ለማጥፋት ለዘመቱ ልጆችህ የጀግኖች ሐውልት አቁመህላቸዋል። የኢትዮጵያ ሕዝብ ግን ለኢትዮጵያና ለኢትዮጵያዊነታቸው በጽናት ቁመው እንዲዋደቁ አዝምቷቸው በየበረሀው ረግፈው የቀሩትን ልጆቹን አጽም ሰብስቦ አፈር ለማልበስ እንኳ እድል አላገኘም። ታዲያ እንዲህ ያለው ግፍ ሲያፈራርድ አይኖርም ብለህ ትገምታለህ? ይኸን ሁሉ አፈራራጅ ድርጊት የሚያውቀው አምልክስ ከእነዚያ ሁሉ የደም እንባ እያለቀሱ ከሚኖሩት ሐዘንተኞች እንደ ራሔል ጩሆቷ የሚሰማላታና እንባዋ የሚደርስላት አንዲት ኢትዮጵያዊት አትኖርም ብለህ ታስባለህ? አንድስ እንደዳዊት አናት በጥብጣ የምትጥለዋን አለት ድንጋይ ከመለስ እራስ ላይ አሳርፎ የኢትዮጵያን ሕዝብ የሚገላግል ወንድ አይወለድለትም (አይባረክለትም) ብለህ ታስባለህ? ስለዚህ ነጻ እናውጣህ ስል ከእነዚህ ሁሉ ፍርድ ከሚጠብቁ እዳወች ተጠይቂነት ማለቴ ነው።

በዘመነ ወያኔ እየገደሉ አድነነዋል፣ እየስራቡ አጥግበነዋል፣ እያፈረሱ ገንብተናታል፣ እያደረቁ አልምተናታል፣ ወዘተ ማለት ዘወትር የሚደመጥ ክላሲካል ሙዚቃ ነው። በኢትዮጵያ ሕዝብ ዘንድ በውል የሚታወቀው የትግራይ ሕዝብ ሐይማኖተ ጽኑ ባለማተብ ሕዝብ መሆንክን ነበር። የአንተን የእምነት ማተብ ሳያስሩና የአንተን ባህሪይ ሳይወርሱ ከአንተ ተውልደናል የሚሉት የእንግዴ ልጆች ግን ተሳስቷቸው እንኳ የእውነት ቃል የማያመልጣቸውና ይሉኝታ የሚባል ነገር የማያውቃቸው በመሆናቸው *"በትግራይ ሕዝብ ዘንድ እውነት የሚባል ቃልና የሉኝታ የሚባል ነገር አይታወቅም እንዴ?"* በሚያሰኝ ትዝብት ውስጥ እንድትወድቅ አድርገውህ እየታየ ነው። የእኔ ጥያቄ ግን የጥፋትና የአጥፌወች ሞዴል የሆኑት ልጆችህ ያልነበረህን ስምና ግብር እያሰጡህ ስለሆነ እባክህ የአገርህንና የወገንህን ጉዳይ በጥንቃቄ እያቸው የሚል ተማጽኖ ያለበት ነው።

ይህን አባባል በማጠቃለያነት የገለጽኩልህ እናት አገርህን አጥፍተውና ከወገንህ ጋር በብዙ መልኩ አቋስለው ሊያቆራርጡህ ሥራየ ብለው ለዘመቱት የልጅ ጠላቶች ምን ያህል የመገልገያ እቃና የመግደያ መሳሪይ ሆነህ እንዳገለገልካቸው እንዲታይህ ለማድረግ ነው። እኔ የታሪክ ባለሞያ አይደለሁም። ይህን ስል ግን በኢትዮጵያዊነቴ ለኢትዮጵያዊነቴ ትኩረት ለምሰጣቸው ጉዳዮች ግንዛቤ የለኝም ማለት አይደለም። ከዚህ አንጻር የረጅም ዘመናት ታሪክ አልህ ሲባል ከተሟላ ተርጉሙ ጋር ከተገናዘበ ለዘመናት ያከማቸኸው ባህል፣ የአብሮነት ልምድና ሁሉንም ማየትና ማሳየት የሚችል ሰፊ የአመለካከት አድማስ አለህ ማለት ይመስለኛል። በአሁኑ ወቅት የሚታይብህ ሁኔታ ግን በተቃራኒው ግራ ኋላ ዞሮ እየወረዱ በመሄድ መንደር ውስጥ እንደመሸጎጥ የሚቆጠር ነው። እንዲህ ያለው ጎጅ ጅምር ደግሞ ለዘመናት ለብሰኸው የኖርከውን ስምና ክብር ገፎ እርቃንህን የሚያስቀምና እየገነባህ የመጣኸውን ታሪክ እንድባቢሎን ሰወች ግንብ በአንድ ጊዜ ንዶ ማእከል የለሽ የሚያደርግህ ነው። ባህረ ነጋሽ ሲካድና ዮሐንስና አሉላ ቅኝ ገዥወች ናቸው ሲባል፣ በሌላ በኩል ደግሞ የአክሱም ሐውልት ለሌላው ምኑ ነው ከተባለ የአንተን የአንድነት መሠረትነትና የሥልጣኔ ምንጭነት ጥያቄ ውስጥ ይጥለዋል የሚል ስጋት አለኝ። ሌላው ቢቀር ትዝብትን የማይፈሩት ሕሊና ቢሶች ልዩ አውሮፕላን ስለነበራት በአየር ላይ በርራ ነው ካላሉ በስተቀር ንግሥት ሳባ በየት አድርጋ እየሩሳሌም ደርሳ ተመለሰች ተብለው ቢጠየቁ ምን ሊሉ እንድሚችሉ አላውቅም። የእሷና የተከታዮቿ ንግሥናም ቀይ ባህርን ሳያይና ተከዜን ሳይሻገር ከዚያው አክሱም ተፈጥሮ አክሱም ከስሞ ቀረ እንደማለት የሚቆጠር ነው።

ልጆችህ በእናት አገርህ ላይ ከሚያቀነባብሩት የቅጥረኝነት ሴራና የማጥፈት ርብርቦሽ ሁሉንም ባይቻል ለዋቢነት የሚሆኑኝን ዋና ዋና ነጥቦች ቀድም ሲል ጠቅሸልሀለሁ። ይህን ያደረግሁት አታውቃቸውም ብየ



Document Produced by deskPDF Unregistered :: http://www.docudesk.com

ሳይሆን ይህን ሁሉ ጥፋትና እልቂት እያወቀ ዝም ብሎ ለማየት እንዴት አስቻለው? ለአሰኘው የሁሉም ኢትዮጵያውያን ጥያቄ መልስ የመስጠት ግዴታ ስለአለብህ ነው።

በሁለመናዋ ስትጠቀምባት የኖረችውን እናት አገርህን ምን ያህል እየጎዳሀት እንደመጣህ አንድ ትምህርት ሰጭ አባባል ልጠቅስልህ እፈልጋለሁ። ከእናቷ ቤት አጠገብ ጎጆ ቀልሳ የጎደላትን ሁሉ በእናቷ ጓዳ እየተደጎመች የምትኖር አንዲት ሰው ከእለታት በአንዱ ቀን ገመና ከታቿ እናቷ ይሞታሉ። ይኸን ሁሉ የሚያውቀው ወንድሟ በእናታቸው ሞት ምርር ብላ ታለቅሳለች ብሎ ሲጠብቃት በተፈጥሮዋ አንጀተ ደንዳናነትም ይሁን ወይም የሟች እናቷን ቤትና ማጀት ጨርሸ ወርሸ ሐብታም እሆናለሁ በሚል ተስፋ ተጽናንታ ሊሆንም ይችላል እንደልቅሶ ደራሾቹ ባይተዋር ሆና ስትገማጠጥ ስለአያት ድርጊቷ አስገርሞት፣

“እኔስ የገረመኝ የእማዋይ ዝምታ፣

የእህል መሸመቻ ገብያዋ ሲፈታ” ብሎ በማስለቀስ ትዝብት ላይ ጣላት ይባላል።

ስለእውነት እናት አገር ኢትዮጵያ ለአንተ ብቻ ክፉ ናትን? እንግዲያው ሌሎቹማ ተዋደቁላት እንጅ እንድትጠፋ ፈርደው ልጆቻቸውን አላዘመቱባትም። የሞት ዓይነትና የመግደያ መሳሪያ ሳይመረጥላቸው እየተጨፈጨፉ የደም እንባ አለቀሱላት እንጅ አልተዘባበቱባትም። የእነ ፐ/ር አስራት ወልደየስ፣ የእነሎሬት ጸጋየ ገ/መድህ፣ የእነ ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ፣ የእነ ቴዮድሮስ ካሳሁን፣ የብዙ ብዙ እልፍ አእላፋት ጭንቀት፣ ህልፈትና የቁም ስቃይ የእናት አገር ህልዎና አደጋ ላይ መውደቅ ያስከፈለው መስዋእትነት እንጅ የመንደር ወይም የግል ጥቅም ጉዳይ አይደለም። መቸም አንተም ብትሆን ጨክነህ አወ!እናት አገሬ ለእኔ ክፉ ናት ብለህ ትመሰክርባታለህ ብየ አልገምትም። እምነትህ ይህ ከሆነ ታዲያ የቃል ኪዳን ምልክት፤ የአንድነት ማተብና የነጻነት ሰንደቅ ሆና የኖረችውን ክቡርና ብርቅ ሰንደቅ ዓላማችንን ተራ ጨርቅ ናት ከማለት ጀምሮ፣ 60000 አስገንጣይ ጦር ወደ ኤርትራ ሌላው ደግሞ ወደ ማህል አገር አውካክተው ዘምተው **አንድነቷን ሲንዱትና መሠረቷን ሲያናጓት፤ የባህር በሯን ዘግተው ግዞተኛ አገር ሲያደርጓትና ማህልና ዳር ሳይለዩ እየሸነሸኑ ሲሸጧት** በገሀድ እያየህ ጥፋቷ የማያሳዝንህና ጉዳቷ የማይጎዳህ ሆኖ የሚታይህ በምን ምክንያት ነው? ወያኔያዊ ልጆችህ የሚናገሩት እውነት፣ የሚሠሩት ሁሉ ለዘለቄታ ውጤት የሚበቃ ይሆናል ብለህ ታምናለህን? ይኸ ሁሉ ዳንኪራና ትምክህት ከክህደት፣ ቅጥፈትና ጭካኔ በስተቀር ሌላ መደገፊያ የሌለው የጥሬወች ጥሬ ካብ በመሆኑ ፍርስርሱ ወጥቶ ሲናድ ጊዜ እንደማይወስድ እርግጠኛ ነኝ። ምክንያቱም እነዳግማዊ ይሁዳ አገር ሻጮች ቀርቶ ልበ-አምላክነት የነበራቸው እነቅዱስ ዳዊት እንኳ የኖሩት ውስን ጊዜ ነው። መለስማ የኢትዮጵያ ሕዝብ ባይዋጋው እንኳ የራሱ የውስጥ ቁንቁን መቅኑን መጦ በቁሙ ሲያደርቀው፣ አለያም በቀን ሲፈርስና ሲሠራ እንዲውል የሚያደርገው አዙሪት እንደጣለ ሲያስቀረው ነገር ዓለሙ ሁሉ ያከትማል። እሱ አራግፎብህ የሚሄደው ባለብዙ መልክ ችግር ግን አንተን ሲያቆስል፣ ሲያሳፍርና አንገትህን ሲያስደፋ የሚኖር ይሆናል ብየ በእጅጉ እሰጋለሁ። ለምሳሌም የአንተ ሰላማዊ ልጆች በኢትዮጵያዊነታቸው ኮርተው በማንኛውም የአገሪቱ ክፍል እየሠሩ ይኖራሉ። መሆንም ያለበት ይኸው ነው። በትግራይ የአስተዳደር ክልል ግን ወላይታው፣ ጋምቤላው፣ ሲዳማው ሱማሌው ወዘተ ቀርቶ ተጎራብቶህ የሚኖረው የአማራው ሕዝብ እንኳ (በግድ ትግሬ መሆን አለባችሁ ተብለው በግዞት የተያዙትን ሳይጨምር ማለት ነው) አይኖሩበትም። በግራ እጃቸው የኢትዮጵያን የአንድነት መሠረት ለማፈራረስ ያስችለናል ያሉትን አንቀጽ 39 የተባለ ፈንጅ፣ በቀኝ እጃቸው ደግሞ በጠላትነት የፈረጇቸው ግለሰቦችና ሕዝብ መግደያ የሚሆን መሳሪያ ይዘው፣ መልካም ነገር በማይወጣው መርዘኛ ምላሳቸው ደግም "የአክሱም ሐውልት ለወላይታው ምኑ ነው"? ብለው በይፋ ካወጁ ሥልጣነ-ዘመናቸውን አስቆጥሮዋል። የአንተ ብቻ ያልሆነውን የክሱም ሐውልት የአንተ ብቻ ነው ሲሉ የበለጠ የሰጡህ መስለው አንተ ከሌሎቹ ጋር የምትጋራቸውን ብዙ ነገሮች ሊያሳጡህ ወይም የአንተ አይደሉም ሊሉህ ፈልገው እንደሆነ በትትክል የገባህ አልመሰለኝም። አለያማ የአክሱም ሐውልት የኛም ጭምር ካልሆነ የእኛም ሁሉ የአንተ አይሆንም ለሚሉህ ምን መልስ እንደሚሰጡልህ አላውቅም። ስለሆነም ከቤትህ ለተጫረው የችግር እሳት አንተው የማጥፊያ መፍትሄ ካልፈለግህለት በስተቀር ተዳፍኖ ውስጥ ውስጡን እየጋመ የመፈንጃ ቀኑን በመጠበቅ ላይ ስለሆነ ፈንድቶ የተቀጣጠለ እለት አንተኑ ተመልሶ የሚፈታተን ችግር መሆኑ አይቀሬ ነው። ያን ጊዜ ተጎጅው አንተ ብቻ ትሆናለህ ባልልም በአንተ ምክንያት ሁሉም ጉዳት ላይ መውደቃቸው ግን የአንተን ጉዳት እጥፍ ድርብ ሊያደርገው ይችላል።

ወያኔወች እንደ በግ ግልገል ከጉሮኖ ውስጥ ባልወጣ አስተሳሰብ የኢትዮጵያን የባህር በር አንፈልገውም ብለው ለፈጣሪያቸው ለሻቢያ ሲያስረክቡ በአንድ በኩል በጠላትነት ፈርጀው የዘመቱበትን ሕዝብ ጉሮሮውን አንቀው መተንፈሻና መላወሻ በማሳጣት አንበርክከው ሲገዙ ለመኖር፣ በሌላ በኩል ደግሞ ተራራ ያንቀጠቀጠ



Document Produced by deskPDF Unregistered :: http://www.docudesk.com

ትውልድ የተባለለት ጦራቸው እየቆራረጠ ማስገባት የጀመረውን የአፋር አስተዳደር ክልል አጠቃሎ ወርሮ የአሰብ ጌታ ሆኖ ለመናጠጥ አቅደው ነበር። በአለመታደል ለእነመለስ ዜናዊ ያልጠበቁት መርዶ ሆነባቸውና፣

1 ከሻቢያ ጋር የነበራቸው መሐላ ፈርሶ በ100000 ለሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን እልቂት (ወያኔወችን ባያሳዝንም) ምክንያት ሆነ። ይኸም ሆኖ ችግሩ እንደተረገዘ ነው።

2 የአሰብ እስትራተጂካዊ ተስፈኝነትም ለወያኔወች ቀርቶ ለሻቢያወች እንኳ በቀላሉ መልሰው ለማግኘት በማይችሉበት ሁኔታ ተላልፎ መሰጠቱን በይፋ እያየን ነው። ይህን በዋቢነት የጠቀስኩት ድርጊቱ በኢትዮጵያውያን ዘንድ እንደ መልካም ብስራት አይተው ይደሰቱበታል ብየ ሳይሆን አርቆ ማሰብና ተገላምጦ ማየት የማይችሉት ልጆችህ የሚሠሩት ሥራ ሁሉ እንደዚህ በቀውስ የታጀበ መሆኑን እንድትረዳው ብየ ነው።

በዚህም ምክንያት የአህያ ሥጋ ከአልጋ ላይ ተቀመጥ ቢሉት አልተመቸኝም ብሎ ከአመድ ላይ ወርዶ ተንከባለለ እንደሚባለው የራሳቸውን ለራሳቸው አድርገው ለመጠቀም ያልታደሉት ሁለንተናዊ ድሐወች ለጅቡቲ የባህር ወደብ ኪራይ በየዓመቱ 722 ሚልየን ዶላር እየገበሩና የአበባ ጉንጉን እያነጠፉ ቢጎናበሱም አልሳካላቸው ስለአለ የሌሎች አገሮች ባለስልጣኖችን ጫማ እየሳሙና ባሕሪያቸውን እያሚሹ የሚኖሩብት ልምዳቸውን ቀጥለውበት እያየን ነው። አንግዲህ ስለልጆችህ ድርጊት ማወቅ ከፈልግህ  ሥራና አሠራራቸው ሁሉ ከዚህ ያልተለየ መሆኑን ይህን በሞዴልነት ወስደህ ሁሉንም ልትገመግምበትና ልትማርበት ይገባል እላለሁ።

በአካባቢህ ብዙ ፋብሪካውች ተቋቁመዋል፣ ከፍተኛ ሐይል ተሸካሚ የሆኑ ረጅም የኤሌክትሪክ መስመሮችም ተዘርግተዋል። ጥሬ እቃቸውና የሐይል ማመንጫ ምንጫቸው ግን የሚገኘው በሌሎች አካባቢወች ነው። በመሠረቱ እነዚህና ሌሎችም የሚያስፈልጉህ ሁሉ ቢሟሉልህ የምደሰት እንጅ የምቃወም አይደለሁም። ነገር ግን አንተን መሳሪያ አድርጎ ለመገልገል ሲባል ሌላውን እያጨለሙ፣ የሌላውን እድገት እያቀጨጩና የመልማት እድሉን እየዘጉ ለአንተ አካባቢ ብቻ ማድረግ ግን ለጊዜያዊ ጠቀሜታ ሲባል የረጅም ጊዜ ጠላትነት መግዛት ማለት ነው። **በአጠቃለይ ልጆችህ አስፍቶ የማየት ችግር ያለባቸውና ኢትዮጵያዊ ሐላፊነትን መሸከም ያቃታቸው ደካሞች ናቸው። የደካማነታቸው ዋነኛ ምክንያት ደግሞ ኢትዮጵያዊነታቸውን ሸጠው የበሉ ክብረ-ቢሶችና በራሳቸው የማያዙ ቅጥረኞች በመሆናቸው** ነው። ከዚህ አንጻር የ18 ዓመት ድርጊታቸውን የሕግ ምስክር አድርገህ በማቆም፣ እራስህን ህሊና ዳኛ አድርገህ በመሰየም ፍርድ የምትሰጥበት አንድ መሠረታዊ ጥያቄ ላቀርብልህ እፈልጋለሁ። በኢትዮጵያ የረጅም ዘመናት የመንግሥትነት ታሪክ ከ2545 ዓ.ዓ ጀምሮ እስከ1983 ዓ.ም. 202 መንግሥታት እንዳስተዳደሩዋት የታሪክ ማህደሮችና የመስኩ ባለሞያወች ይናገራሉ። ከእነዚህ ውስጥ የአንተን ልጆች መንግሥት ነን ባይነት ከየትኛወቹ ጋር ታመሳስላቸዋለህ? በእውን ኢትዮጵያን ለማስተዳደር ዙር ተራው ደርሷቸው ሥልጣን ላይ የወጡ ኢትዮጵያውያን ናቸው? ወይስ የታሪካዊ ጠላቶቻችንን እቅድ ለማስፈጸም በኢትዮጵያና በኢትዮጵያዊነት ላይ የዘመቱ ቅጥረኞች? እንደዚህ ያለ የረጅም ዘመናት ታሪክ ለአላትና እነዚያን ሁሉ ነገሥታት ስታስተናግድ ለኖረች ታሪካዊት አገር የሚመጥን የመንግሥትነት ሥነ-ባህሪይና የሞራል ብቃት አላቸው ብለህ ታምናለህ? አላቸው ካልክ  ደግሞ ከእነማን ጋር አወዳድረሀቸው ነው? ቤተ-መንግሥታቸውን የረር ጋራ ላይ መሥርተው ኢትዮጵያን በፍጹም ወንድማማች ፍቅር ሲያስተዳድሯት ከነበሩት አብርሐና አጽባሐ፣ ከእነ ዮሐንስና አሉላ? ወይስ ከእነዮዲት ጉዲትና አህመድ ግራኝ? ወይስ ለአጭር ጊዜም ቢሆን ኢትዮጵያን ወራት ከነበረችው ፋሺስት ኢጣሊያ? ከዚህ በኋላ ፍርዱን ለአንተው ትቸዋለሁ።

ልጆችህ ለመልካም ስምና ሥራ ያልታደሉ ሁለንተናዊ ድሐወች መሆናቸውን ደጋግሜ ገልጫለሁ። ይህን ያደረግሁት በአንድ በኩል ሐቅ ስለሆነ በሌላ በኩል ደግሞ ክፉ ሥራቸው እንድናገር ስለገፋፋኝ እንጅ ተፈጥሮአዊ ህሊናየ ፈቅዶልኝ አይደለም። እነሱ ግን ጠቃሚ ሥራ ሠርቶ ከመመስገን ይልቅ ክፉ ሥራ ሠርቶ መረገምን የሚመርጡ መርገምቶች በመሆናቸው በአንደበታቸው መልካም ቃል በእጃቸው ደግሞ ጠቃሚ ነገር ላለመስራት ምለው የተወለዱ ይመስላል። **የሰው ልጅ እርጥብ ፍጡር ነው** እየተባለ ሲነገር እሰማ ነበር። ከራሴ የህይወት ገጠመኝ ጋር እንኳ ሳገናዝበው በእርግጥም ሊባል የተገባው ነው። አንጀትን አሳርረው የሚያኮማትሩ፣ ህሊናን አቁስለው የሚያደሙ፣ በአጠቃላይም ሰው ሆኖ መፈጠርን የሚያስጠሉ እጅግ አሳዛኝ  ሁኔታወች በተፈጠሩ ቁጥር በሆድ ውስጥ ጭሶ ሊቀጣጠል የሚቃጣውን፣ በአእምሮ  ውስጥ ታምቆ ሊፈነዳ የሚተናነቀውን  በተፈጥሮ እርጥብነቱ እያበረደ ባይከላከለው ኑሮ እጅግ ብዙ ምስጉን ሰወች ከራሳቸው ውስጥ በሚቀጣጠል እሳት እራሳቸውን በቁማቸው እያቃጠሉ ባለቁ ነበር።



Document Produced by deskPDF Unregistered :: http://www.docudesk.com

ይህን አባባል እንድጠቅስ የተገደድኩት በአሁኑ ወቅት ከ14 ሚሊየን በላይ የሆነ ሕዝብ ለረሐብ አደጋ ተጋልጦ የእለት ደራሺ ምግብ በሚፈልግበት፣ ሠርቶ መኖርና እራሳቸውን ማስተዳደር የሚችሉ እጅግ ብዙ የአገሪቱ ዜጎች ለሥራ አጥነት ተዳርገው ከከፋ ማህበራዊ ችግር ውስጥ በመውደቃቸው የህይወት ክራቸውን እያራዘሙ ውለው ለማደር ሲሉ በጣት ተቆንጥሮ በሚሸጥ ጉርሻ አንጀታቸውን አጥፈው በሚኖሩት አገር፣ የምግብ እህል ገዝቶ ለመጠቀም እንኳ ገብያ ላይ ጠፍቶ እንደ ሞት መድሐኒት እየተፈለገ እህሉን ሳይሆን ገንዘቡን እንደ መብላት በሚያስቆጥር እጅግ ውድ በሆነ ዋጋ በሚሸጥባት አገር፣ ኸረ ስንቱ ተዘርዝሮ ያልቃል? እነዚህ ሁሉ ማህበራዊ ቀውሶች በሰፈኑባት አገር በኢትዮጵያ ለም መሬት የተመረተ የመጀመሪያው የእሸት ምርት ለሳውዲ አረቢያ ንጉሥ ተበረከተላቸው ተብሎ ሲነገር፣ በረሀብ ጦር የተወጋውና በችገር የሚማቅቀው ብቻም ሳይሆን ገብያ ወጥቶ የሚገዛው አጥቶ የተመለሰው ኢትዮጵያዊ ሁሉ ምን ሊሰማው እንደቻለ እራሱን መርምሮ ፍርድ ይስጥበት። እውን የሳውዲ አረቢያ ሕዝብ የጤፍ እንጀራ አምሮት ነው የጤፍ አምራች የሆነችው አገር ሕዝብ ገብያ ላይ ያጣው ጤፍ እየተሚጠጠ የሚጓጓዝለት? አዎ! ሰውን እርጥብነቱ ካልተከላከለለት በስተቀር በቁሙ እንዲቃጠል የሚያደርገውም እንዲህ ያለው እንደ ሐውልት ተተክሎ አፋርደን ተብሎ ሲጠየቅ የሚኖርና እስከወዲያኛው ድረስ የማይረሳ የጠላትነት ድርጊት ነው። የትግራይን ሕዝብ አስቀድመህ እራስህን ነጻ አውጣ የምለውም እነዚህ ሁሉ የማይረሱ የጠላትነት ድርጊቶች በተወሱ ቁጥር ስታፍርና ስትሸማቀቅ እንዳትኖር በማሰብ መሆኑን በቅን ህሊና ተረዳልኝ።

ከቃል ኪዳን ጌቶቻቸው የተሰጣቸውን ትእዛዝ ለማስፈጸም ሲሉ የሱማሌን ሕዝብ ወርረው ቁጥራቸው በውል ያልታወቀ ብዙ ኢትዮጵያውያን ለእልቂትና ውርደት ከመዳረጋቸውም አልፎ በቀላሉ የማይታይ ጠላትነትንም ገዝተውብናል። የዚህ ዳፋ በቀል እውን አንተን ብቻ ከልሎ ነጻ የሚያደርግህ ይመስል? ለምን ዓላማና በማን አዝማችነት እንደ ተዘመተባቸው ሱማሌውች ውስጠ-ሚስጥሩን የማያውቁ ሞኞች መስለው ታይተውህ እንደሁ ተሳስተሀል። ስለሆነም ልጆችህ ጠቀምነህ ብለው በየቦታው የተከሉብህ እሾህና ያስቀመጡብህ እንቅፋት እስከ አሁን በነጻነት ኮርተህ የኖርክበትን ኢትዮጵያዊ ሰውነት እየተጠራጠርክ እንድታየውና በየሄድክበት ሁሉ የሚያደናቅፍ እንቅፋትና የሚዋጋ እሾህ እንዲገጥምህ የሚያደርግ ነው። በእርግጠኝነት የምገልጽልህ ቢኖር ሐገረ- እግዚአብሔር ኢትዮጵያ በቅጥረኛ ጥቁር ሹምባሾች ቀርቶ በጌቶቻቸው እንኳ ያልፈረሰችና ወደፊትም የማትፈርስ መሆኗን ነው። ማልካ-ምድራዊ አቀማመጧ፣ የተፈጥሮ ሐብቷና የረጅም  ዘመናት የተጋድሎ ታሪኳ የገዛባት ጠላቶቿ ብዙ ጊዜ ሞክረው ነበር። ነገር ግን በጀግኖች ልጆቿ (አንተን ጨምሮ) ተጋድሎ ድባቅ ተመተው ከመመለስና የውርደት ማቅ ለብሰው ከመኖር በስተቀር ተሳክቶላቸው አያውቅም። ዛሬም ቅጥረኛ ባንዳወችን የሚጠብቃቸው እድል ይኸው መሆኑ አይጠራጥርም። የወደፊቷ ኢትዮጵያ ሊገድሏት ግንባር ፈጥረው ለዘመቱባት ቀርቶ እየተወጋች ስትቆስልና ስትደማ ቁመው ለተመለከቷት እንኳ የሚያዝን አንጀት፣ የምታጠባው ጡትና የምትዘረጋላቸው እጅ አይኖራትም። ስለዚህ እናት አገርህን ከታደጓት ሌሎች ወገኖችህ ጎን የሚያሰልፍ እምነት፣ ጠንክረህ እንድትቆም የሚያደርግ የሞራል ጉልበትና የማይተሳሰር አንደበት እንዲኖርህ ከፈለግህ በጉዳዩ በብርቱ አስብበት። አንተ እንዴት እንደምታየው ባላውቅም እንደ እኔ ግምጋሜ ግን የወያኔ መሪወች ብዙ ነገር የሚያሳጡህ ጠላቶችህ እንጅ ብዙ መልካም ነገር የሚያመጡልህና የሚሰጡህ እውነተኛ ልጆችህ አይመስሉኝም። **ከዘመናት ኢትዮጵያዊነትህ  ይልቅ ወያኔ በካበልኝ ትግራይነቴ ብዙ ተጠቅሜያለሁ የሚል እምነት ካለህ ተሳስተሀል። ምክንያቱም በትግራይ-ነትህ እስከ አሁን ብቻህን ካገኘኸው ይልቅ ኢትዮጵያዊነትህን በማጣትህ ወደፊት የምታጣው በዓይነትም ሆነ በመጠን በእጅጉ የበዛ ነው። ለእኔ ኢትዮጵያዊነትን ማጣት ማለት ሁለመናን ማጣት ማለት ነው።** ማጣት ሲባል ደግሞ ሐብት ብቻ ማለት አይደለም። አገርንና ታሪክን፣ ፍቅርንና የአንድነት ኃይልን፣ መንፈሳዊ ሕይወትንና የሞራል ሐብትን፣ መተሳሰብንና የጋራ ችግርን በጋራ መወጣትን፣ ኸረ ስንቱ! እነዚህን ሁሉ ማጣት ማለት በቀላሉ መልሰው የማያገኙት ከባድ ድህነት ነው።

**ብቻውን የበላ ብቻውኝ ይሞታል** የሚባል ተግባራዊ ማረጋገጫ ያለው ትምህርት ሰጭ አባባል አለ። ጥበትን፣ ትምክህትን፣ እራስ ወዳድነትን (ግለኝነትን) ወዘተ በአጠቃላይ ለማህበራዊ ኑሮ ጠንክ የሆኑትን እምነቶችና ድርጊቶች ሁሉ የሚኮንን አመለካከት ነው። ለመልካም ሥራ ካልታደሉና  በህይወት ሳሉ የማህበራዊ  ኑሮ ግዴታወችን በአግባቡ ካልተወጡ የማይቀረው ሞት ቀኑን ጠብቆ የመጣ እለት በድን እሬሳን አንስቶ አፈር የሚያለብስ  ዘመድ አዝማድ እስከ ማጣት የሚያደርስ ከባድ ፈተና እንዳለበትም የሚያመለክት ነው። አባባሉ በሰፊ ትርጉሙ ከተገናዘበ በአንተ አካባቢ በመካሄድ ላይ ያሉትን ይሉኝታን ጨርሰው ያጡ ድርጊቶችን ሁሉ አጠቃሎ የሚያሳይ ነው።

እኔ እንደማውቀው የኢትዮጵያ ሕዝብ ለአንተ ክፉ አይደለም። በተፈጥሮ ችግር ተጠቅተህ ህይወትህ እንደቅጠል ሊረግፍ በተቃረበበት ወቅት በአለችው ጎኑ ያበሰለውን ምግብ ብቻም ሳይሆን ከዓይኖቹ



Document Produced by deskPDF Unregistered :: http://www.docudesk.com

እየጨመቀ ያወረደውን እንባ አብሮ ያቀረበልህ የልብ ዘመድህና የአንጀት ወገንህ ነበር። አንተ ግን የትላንቱን ብቻም ሳይሆን የትላንቶቹን ሁሉ የዘነጋህቸው ይመስላል። በዚያ የፈተና ዘመን በብዙ ተጨንቀህ ስታለቅስ አብሮህ ያለቀሰው ወገንህ ዛሬ ግን በአንተ ልጆች ምክንያት ሐዘንተኛ ሆኖ ሲያለቅስ እያየኸው እንደእሱ አብረህ እያለቀስክ ልቅሶውን ማስቆም ቀርቶ ልቅሶ እንኳ ልትደርሰው አልፈልግህም። ይኸም እምነተ-ቢሶቹ ልጆችህ የተከሉብህን የባእዳን አምልኮት አምነህ እንደተቀበልከው የሚያስቆጥር ሆኖዋል። ለማንም ይሁን መቸም ከኢትዮጵያና ከኢትዮጵያዊነት የተለየ ህይወት ከባህር ወጥቶ በየብስ ላይ መኖር እችላለሁ ብሎ እንደሚያምን አሳ የሚቆጠር ይመስለኛል። ስለዚህ ደግመህ ደጋግመህ አስብበት። ማሰብ የሚገባህ ደግሞ ለአሁኖቹ መርዘኞች ለበከሏቸው የማይድኑ በሺተኞች ሳይሆን ለነገወቹ ንጹህ ተተኪ ልጆችህ መሆን አለበት። **ማሰብ ሲባል ደግሞ በጎ ማስብ ብቻ ሳይሆን ሳያሳስባቸው መኖር የሚችሉበት መልካም ስም ማትረፍና ንጹህ ሥራ ሠርቶ ማለፍ ነው።**

እኔ እንደሚገባኝ ስጋትህ ወያኔወች በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ያደረሱበትን ግፍና በደል በእኔ ላይ ሊወጣ ይችላል የሚል ሊሆን ይችላል። እንዲህ ያለውን ስጋት ሊፈጥሩብህ የሚችሉት የወያኔ መሪወች በጭንቀት ተወጥረው እየባነኑ የሚኖሩበትን የተስፋ ቢስነት እድሜ ለማራዘም ሲሉ አንተን እንደ ጉሉኮስ መድህኒት አድርገው የተጠቀሙበት ስልት እንጅ ልበ-ሰፊው የኢትዮጵይ ሕዝብ ይህን የሚያደርግ አረመኔ ሆኖ አይደለም። እንደሚታወቀው ሻቢያወች የኤርትራን ሕዝብ በተሳሳተ ጎዳና እየመሩ በኢትዮጵያ ሕዝብ ልጆች ላይ ቃላት ሊገልጸው ከሚችለው በላይ የሆነ ከፍተኛ እልቂት እንደፈጸሙባቸው የኢትዮጵያ ሕዝብ ጠንቅቆ ያውቃል። መለስ ዜናዊ ከሻቢያወች ጋር በተማማሉበት ኢትዮጵያን በጋራ የማጥፋት መሐላ ተካክደው ጦርነት በገጠሙበት ወቅት የዓይናችሁ ቀለም አላማረኝም ያላቸውን ኢትዮጵያዊ ኤርትራውያንን ሁሉ ከተደላደለ ኑሮዋቸው እያፈናቀለ ሲያባርራቸው ነግ በኔንም የሚያስበው የኢትዮጵያ ሕዝብ ግን በአደራ የሰጡትን እቃ እየተቀበለ አኖረላቸውና እያለቀሰ ሸኛቸው እንጅ እሰየ እንኳን ነቀለልን ብሎ አብሮ አላዋከባቸውም። ስለዚህ አንተም ከዚህ ትምህርት ልታገኝ ይገባል።

አንተን የሚፈልጉህ የቅጥረኝነት ግዳጃቸውን ለማስፈጸም የሚያስችል መሳሪያ እንድትሆናቸው ብቻ ነው። ለአንተ ስንል ሞተናል፣ ቆስለናል፣ ደምተናል ወዘተ የዘወትር አደንቋሪ ዋይታቸው ነው። የዚያ ሁሉ ዓላማና ግብ ምን እንደነበር ግን በአሁኑ ወቅት ይፋ ሆኖዋል። በመሳሪያነትህ ለመገልገል ወደኋላ እንደማይሉ የበለጠ ለማወቅ ከፈልግህ ስለሐውዚን የተቀነባበረ እልቂት በ1981-82 አቶ አብርሐም ያየህ የሰጠውን መግለጫ፣ በስምህ ለምነው ያገኙትን እርዳታ ሁሉ በእጅ አዙር ሺጠው የተጠቀሙበት መሆናቸውን አቶ ገብረ መድህን አራያን ጠይቀህ ማረጋገጥ ትችላለህ። ካሁን በኋላ ግን እናት አገርህን ለማጥፋትም ሆነ ወገንህን ለመጨፍጨፍ የአንተን መሳሪያ ሆኖ ማገልገል እንደ ጠቃሚ ሥራ ካየኸው ምርጫው የአንተ ነው። ይህን ሁሉ እያደረግህ ኢትዮጵያዊነቴን የሚያሳጣኝ የለም የሚል እምነት ካለህም ሁለተኛ ስህተት ነው። ምክንያቱም ስትዋደቅላት የኖርክላትን እናት አገርህን ገድለው ለመቅበር የዘመቱባትን የአገርና የሕዝብ ጠላቶች አቅፈህ ይዘህ በኢትዮጵያዊነቴ ከኢትዮጵያውያን ጋር አብሬ እኖራለሁ ማለት የበለጠ መቆሳሰልን እንጅ እንዳለፈው ተፋቅሮና ተደጋግፎ መኖርን  ፈጽሞ አያመጣም። ሌሎቹ ልጆቿ ግን የአንተ ልጆች የደገኑባቸውን መሳሪያ ተጋፍጠውና የጠየቀውን መስዋእትነት ከፍለው በሚያድኗት አገር  አብሬ እኖራለሁ ካልክ ከወገኖችህ ጎን በእምነትም ሆነ በተግባር አብረህ ሁነህ እነሱ የሚጋፈጡትን ችግር መጋፈጥ፣ እነሱ የሚከፍሉትን መስዋእትነት መጋራትና በዚያ ላይ የሚያብበውን የድል ችቦ አብሮ ለማብራት መቻል ነው። አብሮ የሚያሰልፍ እምነት፣ ጠክሮ መቆም የሚያስችል የሞራል ጉልበትና በልበ ሙሉነት ሊያናግር የሚችል አንደበት ሊኖርህ ይገባል የምለውም ለዚህ ነው።

ወያኔወች ታላቋን የትግራይ ሪፐብሊክ በሁሉም መስክ እራሷን ለማስቻል ብቻም ሳይሆን ግንባታቸው አስተማማኝ የሆነ ዘላቂነት እንደማይኖረው ስለሚያውቁ በዚህ ላይ ተመስርቶ ሊመጣ የሚችለውን ወታደራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ችግሮች ሁሉ በሩቁ ለመከላከል የሚያስችል በቂ ዝግጅት ማድረጋቸው የአደባባይ ሚስጥር ነው። በወታደራዊ መስክ የአገሪቱ የመሳሪያና የጥይት ፋብሪካወች ተነቅለው ተወስደው ትግራይ ውስጥ ተተክለዋል። ተዋጊ ጀቶችም ከነመሳሪያቸው ተወስደው ወታደራዊ መሬት ይዘው እንዲቀመጡ ተደርገዋል። የትግራይ ሕዝብ ወደፊት ሊገጥመው ለሚችል ምናልባታዊ ጦርነት በምግብ እህል፣ በልብስ፣ በመገናኛና በሕክምና አገልግሎት ወዘተ እንዳይቸገር እነዚህን ፍጆታወች የሚያመርቱ ፋብሪካወች በአካባቢው ከማቋቋማቸው በተጨማሪ ኢፈርት በተባለው የመዝረፊያ ድርጅታቸው አማካይነት ከማህል አገር እያግበሰበሱ ወስደው አከማችተዋል። በአጭሩ በአሁኑ ወቅት በትግራይ በክምችት ያልተሞላ መጋዘን፣ ጎተራና ዋሻ የለም ማለት ይቻላል።



Document Produced by deskPDF Unregistered :: http://www.docudesk.com

በአጠቃላይ በማድረግ ላይ ያሉት ሁለንተናዊ ዝግጅታቸው በዚህ ጊዜ ሊያቆም ይችላል ብሎ ለመገመት ከማይቻል ዓይነትና መጠኑ ጋር ተዳምሮ ሲገናዘብ እንደ ሕዝብ ያልቆጠሩትና ይህን ሊያደርግ ይችላል የሚል ግምትያልሰጡት የኢትዮጵያ ሕዝብ ቀርቶ ልዑል እግዚአብሔር ቅ/ሚካኤልና ቅ/ገብረኤል ሠራዊቶቻቸውን ይዘው እንዲዘምቱ ቢያደርግ እንኳ ሊደፍሩን አይችሉም በሚያሰኝ ትምክህት ውስጥ የመሸጉ መስለው እየታዩ ናቸው። ክምችትን በሚመለከት አብሮ ለማገናዘብ የሚረዳ አንድ በታሪክ የተመዘገበ ማስረጃ ልጥቀስልህ። አፄ ቴዎድሮስ ወደ ስሜን ዘምተው እያንበቡ አስቸግረዋቸው የነበሩትን ደጃች ውቤን ድል አድርገው ይኖሩበት የነበረው ቤተ-መንግስት በወታደሮቻቸው ሲፈተሺ ከመጠን ያለፈ ክምችት ይገኝበታል፡፤ ድርጊቱ ያስገረማቸው አፄ ቴዎድሮስ ምን ሊያደርግላቸው ነው ይህን ሁሉ ያከማቹት? ብለው ከደጃች ውቤ ሹሞች አንዱን ይጠይቋቸዋል። ተጠያቂው ሹምም አንድ ቀን ለሚመጣ ችግር ይሆናል ብለው መሆኑን ይመልሳሉ። አይበገሬ ወኔያቸውን እንጅ ቅራቅንምቦ መቃረምን ያልለመዱት ወንድ ሆነው ተወልደው ወንድ እንደሆኑ ያለፉት አንድ ለእናቱ "አየ! በደህና ጊዜ ያስቀመጡትን በችግር ጊዜ ጠቀም ከተቻለማ ምን የችግር ቀን አለ ታዲያ!" አሉ ይባላል።

አዎ! አጠያያቂ ጥያቄውም ይኸው ነው። ያች ፍርድ የተሰጠባት ቀን ስትደርስና የግፍ ጽዋው ሞልቶ ሲፈስ አደርጋለሁ ያሉትን አዞ ማስደረግ ቀርቶ እራስን እንኳ ማዘዝ እንደማይቻል በብዙወች ማን ይነካን ባይ እውር ትምክህተኞች ላይ ደጋግሞ ውሎ የታየ ሐቅ ነው። ትላንት ግዛታችን ፀሐይ የማይጠልቅበት፣ ሥልጣናችን ደግሞ ገደብ የሌለበት ነው ይሉ የነበሩት ሁሉ ዛሬ ግን ለራሳቸው እንኳ መሆን እያቃታቸው ምን ያህልተወጥረው እንደሚኖሩ በገሀድ እያየን ነው። ሌላው ቀርቶ ከመሬትም አልፎ ሌላውን ያልታወቀ ዓለም አስሳለሁ የምትለው አሜሪካ ፔንታጎንን ከፈንጅ ነጎዳ ማዳን ካልቻለችበት ታሪክ መማር ይገባል። ግማሺ አውሮፓን የወረረና ዓለምን ያንቀጠቀጠ ተፈሪነት የነበረው የሂትለር ጦር በየተሰማራበት ግንባር ብትንትኑ ሲወጣ ጊዜ አልወሰደበትም። ለጀርመን ሕዝብ ያተረፈለት ቢኖር ግን ንጹህ የጀርመን ሕዝብ (የአርያን ዘር) የሚሉትን (እንደኛወቹ ወርቅ ሕዝብ ባዮች ማለት ነው) ተስፋፍቶና ገኖ እንዲኖር እናደርገዋለን ብለው በሌሎች ንጹሐን ሕዝቦች ላይ የፈጸመት እጅግ ዘግናኝ አረመኔያዊ ድርጊት በተነሳ ቁጥር ሲሸማቀቅና አንገቱን ሲደፋ መኖርን ነው። እኔ እንደሚገባኝ ለሰው ልጅ የማይበገር ጠንካራው የመከላከያው ምሺግ የሰላም ሰው ሆኖ የሰላም አጥር ማጠር እንጅ በሰላም የሚኖረውን ሕዝብ በጦርነት ጨርሸ እኔ ብቻ ሰላም አግኝቸ እኖራለሁ ማለት **የሥራ ለሠሪውንና የእሾህ ለአጣሪውን ዳፋ በውል አለመረዳት ነው።**

**ልዑል እግዚአብሔር፥**

-በጥላቻ ለውጥን አውልቀን የጣልነውን የፍቅር ልብስ መልሶ እንዲያላብሰን የቅዱስ ፈቃዱ ይሁንልን!

-የከዱትንና ለማጥፋት የዘመቱባትን ጠላቶቿን ሁሉ ጸጋና በረከቱን ይግፈፋቸው!

-ጠላቶች የበዙባትን የብዙሐን እናት አገር ለዘላለም ይጠብቅልን! አሜን!



Document Produced by deskPDF Unregistered :: http://www.docudesk.com